አማርኛ

የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል

ኪጋሥሂ

ቱሃሄመ ንሐሥሃ

ቁጥሂ ፋ9

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

አማርኛ

የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

የጥንቃቄ መልዕክት

ተማሪዎች!

ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ሥዕሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

<u>ማሳሰቢያ</u>፤ እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

አማርኛ

የተማሪ መጽሐፍ

6ኛ ክፍል

አዘጋጆች

ነጅም ፈጅር መሀመድ

ፀጋዬ ግርማ አብርሃ

አርታኢዎች

አለማየሁ ፀጋዬ ተገኘ

ትንሳኤ ብርሀኔ ላቀው

ሰዓሊ

ከበደ አለሙ

ዲዛይነር

አትርሳው ጥግይሁን ወረቀት

የቡድን መሪ

ዶር. ማረው አለሙ ተሰማ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

የምሁራን መማክርት ጉባዔ

ማውጫ

ጠቃሚ ምክር ለተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ iv

ምዕራፍ 1 ባህላዊ አለባበስ 1

ምዕራፍ 2 ታዋቂ አትሌቶች 21

ምዕራፍ 3 ቃላዊ ግጥሞች 44

ምዕራፍ 4 ዘመናዊ ግብርና 69

ምዕራፍ 5 ጉብኝት 90

ምዕራፍ 6 ፀረሱስ 110

ምዕራፍ 7 የጥላቻ ንግግር 128

ምዕራፍ 8 ኤች አይ ቪ/ኤድስ 145

ምዕራፍ 9 ባህላዊ ልማዶች 163

ምዕራፍ 10 ሴቶችን ማብቃት 180

ዋቢ ምንጮች 197

ጠቃሚ ምክር ለተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ

ይህ የተማሪ መጽሐፍ በፍኖተካርታውና በአገርአቀፍ ምዘናዎች ምክረሐሳቦች መሠረት በ2013 ዓ.ም በተደረገው የሥርዐተትምህርት ለውጥ መነሻነት የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም በመጽሐፉ ዝግጅት የሚከተሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፤

1. የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ፣ የመተንተን፣ የማጠቃለል፣ የመጠየቅ፣ ችግር የመፍታት፣ የመወሰን፣ የመግባባትና የመገምገም ክህሎት የሚያሳድጉ ዓይነተብዙ ተግባራት ተካትተዋል፤

2. የተማሪዎችን አቀላጥፎ የማንበብ፣ የማዳመጥ፣ የመናገርና የመጻፍ ችሎታ የሚያጎለብቱ ታሪኮችና ተዛማጅ ተግባራት እንዲኖሩ ተደርጓል፤

3. የትምህርቱ አቀራረብ ከይዘትተኮር ይልቅ ወደተግባርተኮር እንዲያመዝን ሆኗል፤

4. አገርበቀል እውቀቶች እንደአስፈላጊነታቸው በታሪኮች፣ በምንባቦችና በተዛማጅ ተግባራት ውስጥ ተካትተዋል፤

5. የባሕላዊ ማንነትንና የአርበኝነትን ፋይዳዎች የሚያስገነዝቡ ታሪኮች፣ ምንባቦች፣ ሥነግጥሞችና ሥዕሎች እንደአስፈላጊነታቸው ተካትተዋል፤

6. ተማሪዎች በአብዛኛው በትብብር የሚማሩባቸው እድሎች ተመቻችተዋል፤

7. ለመማር የመማር ክህሎትን ለማጎልበት ሲባል፣ ተማሪዎች በየምዕራፎቹ አራቱን ክሂሎችና ሰዋስዋዊ ይዘቶች የሚማሩባቸው ዓይነተብዙ ብልሀቶች ተካትተዋል፤

8. የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማጎልበት ሲባል ቋንቋውን ፈጥረው የሚጠቀሙባቸው በርካታ እድሎች ተመቻችተዋል፤

9. ሥርዐተፆታንና አካቶ ትምህርትን ከግምት ለማስገባት በታሪኮች፣ በምንባቦች፣ በሥዕሎችና በተዛማጅ ተግባራት እንዲሁም በቋንቋው ትምህርት የይዘት አቀራረቦች ላይ ጥንቃቄ ተደርጓል።

የተማሪ መጽሐፉ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በጥልቀት ማሰብን፣ ማንበብን፣ መጻፍን፣ ማዳመጥንና መናገርን እንዲማሩበት የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ዝግጅት፣ ተማሪዎች እንዴት ማሰብ፣ ማንበብና መጻፍ እንደሚችሉ፣ መማር እንዴት ፈጠራዊና አስደሳች እንደሚሆን፣ የትምህርትቤትና የቤት ውስጥ ተግባራት እንዴት መማርን እንደሚያግዙና እንደሚያጐለብቱ በተደረጉ የምርምር ግኝቶች ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም ተማሪዎችና የተማሪ ወላጆች በትምህርትቤት የተከናወኑ ተግባራትን ይበልጥ ለማዳበር በቤት ውስጥ በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

የትምህርት ይዘቶቹ በአስር ምዕራፎች የተደራጁ ናቸው፤ የመጀመሪያዎቹ ዐምስት ምዕራፎች የትምህርት ይዘቶች በመጀመሪያው መንፈቀዓመት፣ ቀሪዎቹ ዐምስት ምዕራፎች ደግሞ በኹለተኛው መንፈቀዓመት እንዲጠናቀቁ ሆነው የቀረቡ ናቸው። የአንድ ምዕራፍ የትምህርት ይዘቶች ደግሞ በሦስት ሳምንታት እንዲጠናቀቁ ታስበው ነው የተደራጁት። የየምዕራፎቹ የትምህርት ይዘቶች በአንድ ነጥብ በተለዩ ሦስት ቁጥሮች የተወከሉ ናቸው፤ የመጀመሪያው ቁጥር ምዕራፍን፣ ኹለተኛው ቁጥር ሳምንትንና ሦስተኛው ቁጥር ቀንን የሚወክሉ ናቸው። ለምሳሌ፣ 1.1.1 የሚሉ ቁጥሮች ምዕራፍ አንድን፣ ሳምንት አንድንና ቀን አንድን በቅደምተከተል ይወክላሉ፤ እንዲሁም 10.2.3 የሚሉ ቁጥሮች ምዕራፍ አስርን፣ ሳምንት ኹለትንና ቀን ሦስትን በቅደምተከተል ይወክላሉ።

የመጽሐፉ መሠረታዊ መርሖች የሚከተሉት ናቸው፤

- ተማሪዎች ለማኅበረሰብ አስፈላጊ ስለሆኑ ርዕሰጉዳዮች ይማራሉ፤ እያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ ዋና የምንባብ ጭብጥንና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮችን ይሸፍናል፤
- ተማሪዎች ስለእያንዳንዱ ምንባብ ጭብጥና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡና ካነበቡ በኋላ፣ ባዳመጡትና ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመሥርተው ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም፤
- የእያንዳንዱ ምዕራፍ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በምዕራፉ ጭብጥና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች መሠረት ከተጻፉ ምንባቦች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፤
- ተማሪዎች በርካታ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተግባራቱን በቀላሉ በተገቢ ሁኔታ ለማከናወንና ራሳቸውንም በቋንቋው በትክክል ለመግለጽ እንዳይቸገሩ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሠሩ ተማሪዎች ጋር በትብብር ይማራሉ፤

- ተማሪዎች በምዕራፎቹ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች ላይ ተመሥርተው የቀረቡ ምንባቦችን በሚያዳምጡበት፣ በሚያነቡበትና አዳዲስ ቃላትን በሚተዋወቁበት ጊዜ የቃላቱን ፍቺዎች ይማራሉ፤ ይረዳሉ፤ ይጠቀሙባቸዋልም። እነዚህን አዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜም የበለጠ ይረዷቸዋል፤ የቋንቋ ችሎታቸውንም የበለጠ ያበለጽጋሉ።

በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የሚማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች የበለጠ ለማጠናከር በቤታቸው ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጅ/አሳዳጊ ከነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆችዎ ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል፤

1. ወላጅ/አሳዳጊ የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰጉዳይ ልጆችዎን በመጠየቅ ይርዱ፤

2. በትምህርትቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይህንንም ልጆች ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤

3. ልጆችዎን የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ስለምንባቡ ያወያዩ፤

    - ምንባቡ ምን ዓይነት የምንባብ ይዘት ይሸፍናል?
    - በምን ዓይነት ርዕሰጉዳይ ላይ ያተኩራል?
    - ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው?
    - ስለርዕሰጉዳዩ በተጨማሪ ምን እናውቃለን? ስለርዕሰጉዳዩ በዜና ወይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ የሰማነው ምንድን ነው? ስለርዕሰጉዳዩ በሌላ ቦታ ምን አንብበናል?
    - ስለርዕሰጉዳዩ ወይም ርዕሰጉዳዩ በምንባቡ ውስጥ በቀረበበት መንገድ ላይ በግል ያለን አስተያየት ምንድን ነው?
    - በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ስለርዕሰጉዳዩ ምን ማወቅ እንፈልጋለን?
    - ስለርዕሰጉዳዩ በተለየ ሁኔታ ምን ለመሥራት እንፈልጋለን

4. በምንባቡ ውስጥ ስላጋጠሚችሁ ቃላት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩ፤

   - የዚህ ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
   - ቃሉስ ምንባቡን ለመረዳት ረድቶኛል?
   - በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ውሏል?
   - እንዴትስ በሕይወቴ ውስጥ ልጠቀምበት እችላለሁ?

5. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሑፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ፤

6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ ያበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ይወያዩ፤

7. ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ፤

8. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ፤

   - ትምህርቱ ከባድ ነው/ነበር?
   - ትምህርቱ ቀላል ነው/ነበር?
   - ለቋንቋ ትምህርቱ ጠቃሚ ነው/ነበር?
   - ልጆቹ ቀጥሎ ምን መማር ይፈልጋሉ?

9. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆችዎን ይጠይቋቸው፤ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ተሰድረዋል? በዓረፍተነገሮች ውስጥና/ወይም መካከል ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል? ወዘተ.

10. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።

11. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።

የመጽሐፉ ይዘቶች አደረጃጀት

ትምህርቶች

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የትምህርት ይዘቶች በአስር ምዕራፎች የተደራጁ ናቸው። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች የሚደመጡና የሚነበቡ ምንባቦች አሉት። የምንባብ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋው አቀላጥፈው ለመናገር፣ ለማዳመጥ፣ ለማንበብና ለመጻፍ እንዲረዷቸው ሆነው የተሰናዱ ናቸው።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሚያዳብሯቸው ክሂሎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ምናልባት ስለነዚህ ክሂሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ ልጆቻችሁን ወይም መምህሮቻቸውን ጠይቃችሁ ማብራሪያ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁን እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ከመምህራን ጋር እንድትወያዩ ይጠበቃል።

ማዳመጥና መናገር

ተማሪዎች በሚያነቡትና በሚያዳምጡት ምንባብ ላይ ትኩረት ማድረግንና መረዳትን ይማራሉ። በተጨማሪም በሚያዳምጡትም ሆነ በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ በተመሠረቱ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። የሚሠሯቸውም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የማዳመጡ ምንባብ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማዳመጥ በፊት መገመት፣
- ቁልፍ ቃላትን መማርና ስለነሱ መነጋገር፣
- የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደትና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- በማዳመጥ ምንባቡ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር በክፍል ውስጥ መወያየት፣

- ስለማዳመጥ ምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለማዳመጥ ምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስላዳመጡት ምንባብ መናገር፣ የግል ሐሳብን ማቅረብ፣
- በማዳመጥ ምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን መከወን።

አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ምንባቦችን ለደረጃቸው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማለትም የምንባቡን መልዕክት በሚገልጽ ስሜት ደረጃ ድምፅ በማሰማት አቀላጥፈው ያነባሉ።

አንብቦ መረዳት

ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ እንዴት ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና እንደሚረዱ ይማራሉ። በተጨማሪም ባነበቡት ምንባብ ላይ ተመሥርተው በሚዘጋጁ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። ተግባራቱም የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ምንባቡ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማንበብ በፊት መገመት፣
- አስፈላጊ ቃላትን መማርና ስለነሱ መነጋገር፣
- የቅድመንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- በምንባቡ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስለምንባቡ እንዲናገሩ፣ የግል ሀሳባቸውንም እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- በምንባቦቹ ጭብጦች ወይም በንኡሳን ርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ የተውኔት ጽሑፎችን በትወና እንዲያቀርቡ ማድረግ።

ቃላት

ተማሪዎች በሚያነቧቸውና በሚያዳምጧቸው ምንባቦች ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተምረው ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፦

- የቃላትን ንበት፣ ፍቺና የተለያየ አጠቃቀም ይማራሉ፤
- ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላት ይማራሉ፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (ለምሳሌ በቤት ወይም በማኅበረሰብ አካባቢ) በሚፈጸሙ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ቃላቱን ይጠቀማሉ።

ሰዋስው

ተማሪዎች የቋንቋውን የተወሰኑ መዋቅራዊ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ነጠላና ብዙ ቍጥር ስሞችን፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜ ግሶችን፣ ቅጽሎችን፣ ተውሳከግሶችን፣ ነጠላና ድብልቅ ዓረፍተነገሮችንና አጠቃቀማቸውን ይማራሉ።

መጻፍ

ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው የምንባብ ጭብጦችና ንኡሳን ርዕሰጉዳዮች በግል ወይም በቡድን ይጽፋሉ። የሚጽፏቸውም ጽሑፎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶችን፣ ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭና አወዳዳሪ ወይም አነፃፃሪ ጽሑፎችን መጻፍ፣
- ሀሳባቸውን እንዲጽፉ፣ እንዲከልሱና ለኅትመት ዝግጁ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የጽሑፍን የተለያዩ ቁምነገሮች፣ ለምሳሌ በቃላት ውስጥ ፊደላትን በአግባቡና በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣ አጥረው የተጻፉ ቃላትን ወዘተ መረዳት።

ምዕራፍ 1 ባህላዊ አለባበስ

1.1.1 ማዳመጥ — ሙሽሮቹ

ቅድመማዳመጥ

1. በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

ባህላዊ አልባሳት	የተንቆጠቆጠ	ጫጉላ	ማዕድ

2. ሥዕሉን በማስተዋል የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሙሽሮች አይታችሁ ታውቃላችሁ? ከሌሎች ሰዎች (ከታዳሚዎች) በምን ይለያሉ?

ለ. ሙሽሮቹ የትኛዎቹ ይመስሏችኋል? እንዴት አወቃችሁ?



ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ጫጉላቤቱ የተሠራው ከምን ከምን ነው?

ለ. ሙሽራዋ የለበሰችው ነጠላ ጥለቱ ምን ዓይነት ነው?

ሐ. ታሪኩ የተፈጸመበት ቦታና ጊዜ የትና መቼ ይመስላችኋል?

መ. የሙሽራዋን አለባበስ የሚያደንቁ አገላለጾች የትኞቹ ናቸው?

ሠ. የሙሽራዎች አለባበስ ከሌሎች ሰዎች አለባበስ በምን የሚለይ ይመስላችኋል?

ቃላት

ባዳመጣችሁት ታሪክ መሠረት ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ጥለት	ማርዳ	ካባ	ጥልፍ

1.1.2 አንብቦ መረዳት

ልብሴን ኖር በሉት!

ቅድመንባብ

1. ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?
2. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. የክት ለ. እድምተኛ ሐ. አጋፋሪ መ. ኖር

ልብሴን ኖር በሉት!

ከእለታት አንድ ቀን በሀገሩ ታዋቂ የሆነ አንድ ሀብታም ባለሥልጣን ልጁን ለመዳር ደገሰ። በድግሱ ላይ እንዲገኙ የአካባቢውን ሰዎች ጠራ። ሁሉም ጥሪውን አክብረው፣ በክት ልብሳቸው አምረውና ተውበው በተጠሩበት የሠርግ አዳራሽ ተገኙ። የሠርጉ አጋፋሪም እድምተኞችን እንደየማእረጋቸው የሚገባቸውን ቦታ ሰጣቸው። ወንድ እድምተኞች በአንድ በኩል፣ ሴት እድምተኞች ደግሞ በሌላ በኩል ተቀመጡ። እድምተኛው ከምግቡ ቀድሞ የቀረበለትን መጠጥ መጎንጨት ጀምሯል፤ ወሬውም ደርቷል።

በዚህ ሁሉ መሃል ግን አንድ ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ። ከእድምተኞች መካከል አዳፋና የነተበ ልብስ የለበሰ ሰው ነበር። ሁሉም ሰው አንገቱን አስግጎና ዐይኑን አፍጥጦ ሰውየውን በአግራሞት መመልከት ጀመረ። ወደርሱ ሊጠጋ የፈለገ አንድም ሰው አልነበረም። ተጸየፉት። ሁላቸውም ከመካከላቸው ተለይቶ የሠርጉን አዳራሽ ለቆላቸው እንዲወጣ ፈለጉ። የሠርጉ አጋፋሪም ድንገት መጣና ሰውየውን እየገፈተረ ከአዳራሹ አስወጣው።

ሰውየውም በድርጊቱ በእጅጉ ደነገጠ። አጋፋሪው ለምን ገፍትሮ እንዳስወጣው አላወቀም። ድንጋጤው ሲያልፍለት ግን ምክንያቱን መመርመር ጀመረ። "አሃ!" አለና አንገቱን ነቀነቀ። ወዲያውም የብስጭትና የንዴት ስሜቱን አምቆ ወደቤቱ ገሰገሰ።

ከቤቱ እንደደረሰ ቶሎ ብሎ የልብስ ማስቀመጫውን ሳጥን ከፈተና የተሻለውን ልብስ መምረጥ ጀመረ። አሮጌ ልብሱን አውልቆ ጣለና ከሌላው ሰው የበለጠ አምሮ እንዲታይ የሚያደርገውን ያማረ የክት ልብሱን ለብሶ ከሠርጉ አዳራሽ ከተፍ አለ። ከእድምተኛው እስከአጋፋሪው ግርማሞገሱን አይተው በአድናቆት አፋቸውን ከፍተው ተመለከቱት። አቤት ክብር! ያላደረጉለት እንክብካቤ የለም። አጋፋሪውም ከወገቡ ጎንበስ ብሎ እጅ ከነሳው በኋላ ከፍ ያለ የክብር ቦታ ሰጠው። የምግብና የመጠጥ መዓት ከፊቱ ተደረደረ።

ሰውየው ግን የቀረበለትን ምግብ በመመገብ ፈንታ በረጃጅም ጣቶቹ ምግቡን እየለወሰ ልብሱን መቀባት ጀመረ። የሠርጉ አጋፋሪና እድምተኛው ግራ በመጋባት ስሜት የሚያደርገውን ሁሉ ይከታተሉ ነበር። አጠገቡ ያለ አንድ እድምተኛ "ምነው ጌታው! እህሉን እንዲህ ማድረግ ነውር አይደለም እንዴ!" አለው። እርሱ ግን መልስ ሳይሰጥ በምግቡ ልብሱን መለቅለቁን ቀጠለ። ጥያቄዎች መግተልተል ሲቀጥሉ ግን ሰውየው ቀና ብሎ የአዳራሹን ሰዎች በትዝብት ዐይን ተመለከተና እንዲህ ሲል ተናገረ። "ቅድም አዳፋ ልብስ በመልበሴ ገፍትራችሁ ያስወጣችሁኝ አሁን ደግሞ ያማረ ልብስ ስለብስ ያከበራችሁኝ ያው እኔ ነኝ። ነገርግን የተከበረው ልብሴ እንጂ እኔ ስላልሆንኩ ምግቡን መብላት ያለበት ልብሴ ነው። ልብሴን ኖር በሉት!" አላቸውና በምግብ የተለወሰ ልብሱን እንደለበሰ አዳራሹን ለቆላቸው ወጣ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በቅድመንባብ ጊዜ ስለታሪኩ የገመታችሁትን ነገር ስታነቡ ትክክል ሆኖ አገኛችሁት?

ለ. የሠርጉ አጋፋሪ አዳፋ ልብስ የለበሰውን እድምተኛ እየገፈተረ ያስወጣው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. "ልብሴን ኖር በሉት!" የሚለው አገላለጽ ለምን ዓላማ የተነገረ ይመስላችኋል?

መ. የባለታሪኩን ድርጊት ትደግፋላችሁ? ለምን?

ሠ. ከታሪኩ ምን ተማራችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

አዳፋ	የነተበ	አምቆ	አፋቸውን ከፍተው	ገፈተረ	ከተፍ አለ

መጻፍ

“ልብሴን ኖር በሉት!” የሚለውን ምንባብ ሐሳብ አሳጥራችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

1.1.3 ማዳመጥ

ሙሽሮቹ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ጊዜ ያዳመጣችሁትን “ሙሽሮቹ” የሚለውን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

1. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ካሟላችሁ በኋላ ስለሙሽሮቹ አለባበስ በቃል ግለጹ።



2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።
   ሀ. ሙሽሪትንና ሙሽራውን ማየት የሚቻለው እንዴት ነው?
   ለ. የሙሽራውና የሙሽሪት አለባበስ እናንተ ከምታውቁት የሙሽራ አለባበስ ይለያል? በምን?

ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. በባህላዊ አለባበስ የተዋበችው ሙሽራ ተመልካችን ታማልላለች።

ለ. ቁርጭምጭሚቷን ተንተርሰው የተቀመጡት አልቦዎች ውበት አላብሰዋታል።

ሐ. በቀጭኑ በተፈተለ የሀር ክር ያሰረችው መስቀል ከደረቷ ላይ ይፈልቃል።

መ. ከግራ ወደቀኝ ስዞር ዐይኔን በሙሽራው ላይ አሳረፍኩ።

ረ. የቀረበልኝን ተመግቤ “ውለዱ! ክበዱ!” በማለት መርቄ ወጣሁ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ልብሴን ኖር በሉት!” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብ ተለማመዱ።

1.1.4 አንብቦ መረዳት

የሰው ወርቅ አያደምቅ

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “የሰው ወርቅ አያደምቅ” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በሥዕሉ ላይ የምትመለከቱት ሰው ምን የሚሠራ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

ሐ. ርዕሱንና ሥዕሉን በማስተዋል ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።

የሰው ወርቅ አያደምቅ



ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ከእንስሳት ቆዳና ከተክል ቅጠሎች የተሠሩ ልብሶችን ያደርጉ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ስልጣኔ ሲመጣ ደግሞ የሃር ፈትል ተጠቅመው ደርባባ ልብሶችን ለንጉሣዊያን ቤተሰቦች የሚያዘጋጁ የእደጥበብ ባለሙያዎች ነበሩ። በድንቅ ጥበብ የተሠሩ እጀጠባቦች፣ ቡልኮና ካባዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ይዘጋጁ ነበር። ለዚህ ደግሞ በኦሮሚያ የወለጋ ሙዚየምን

ሲጎበኙ የንጉሥ ኩምሳ ሞረዳን አልባሳት፤ በጎንደር የንጉሣዊያኑን ልብሶች፤ በጅማ የአባጅፋርንና የነዋሪዎችን አለባበስ አሻራዎች፤ በደቡብ ደግሞ የጋሞዎችን ጥንታዊ አልባሳት ያለበትን ሙዚየም መመልከት በቂ ማስረጃ ይሆናል።

የኋላ ኋላ የአገራዊው አለባበስ በምዕራባውያኑ ሱፍና ካፖርት መቀየሩ ደግሞ በኢትዮጵያዊያን አለባበስ ባህል ላይ ሌላ ምዕራፍ እንደከፈተ ይታመናል። የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ የሚያደርጉትን ጉዞ ከማጠናከራቸው ጋር ተያይዞ እንደሱፍና ሌሎች የስፌት ልብሶች የመተዋወቃቸው ጉዳይ ከአንድ ምዕተዓመት በላይ ታሪክ አለው። አሁን ላይ ወደሥራ ሲሄዱ በመንገድ ላይ ከሚያገኙት ሰው በግምት 90 በመቶው ከባህላዊ ውጪ የሆኑ አልባሳትን እንደሚጠቀም መታዘብ ይቻላል።

የቅርቡን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ በፋሽኑ ኢንዱስትሪ በቀደመው ባህላዊ ልብሶች ላይ ተመርኩዞ ነጮችን የሚያስደንቅ ዲዛይን የመሥራት አካሄድ እየተለመደ ነው። ወትሮም የራስ ቢያስከብር እንጂ እንደማያዋርድ የተገነዘቡ ባለሙያዎች በዓለም አቀፍ መድረክ ጭምር ታዋቂ ያደረጋቸውን የኢትዮጵያዊያንን ባህላዊ አልባሳት በዘመናዊ መልክ በማቅረብ ላይ ናቸው። ጎብረተሰቡ ግን ባህላዊ አልባሳቱን በበዓላት ወቅትና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ላይ ካልሆነ በቀር እምብዛም ጥቅም ላይ ሲያውላቸው አይታይም። ከዚህ ባለፈም እነዚህ ባህላዊ ልብሶች እንዴት እንደሚሠሩ ለሚያውቀውና በተግባርም ሠርቶ ለሚያቀርበው ጥበበኛ የሸማ ሠራተኛ (ሸማኔ) የሚሰጡት ክብርም የሚገባውን ያህል አይደለም።

በተለይም በወጣቶች ላይ የሚታየው የምእራባውያንን የማድነቅና የራስን የማሳነስ አስተሳሰብ ሊስተካከል የሚገባው ነው። የውጭ የፋብሪካ ልብሶችን መልበስ የስልጣኔ ምልክት፣ የአገራቸውን የሸመና ውጤቶችን መልበስ ደግሞ የኋላቀርነት መለያ አድርጎ መውሰድ የብዙ ወጣቶቻችን ድክመት ነው።

እዚህ ላይ የጃፓናዊያንን ተሞክሮ ማንሳት ይገባል። ሩቅ ምሥራቆቹ ስለራሳቸው ሲናገሩ “አንድ ጃፓናዊ እስከ ሠላሳ ዓመት ዕድሜው ድረስ በአውሮፓ ባህልና አለባበስ እንዲሁም ሙዚቃዎች ላይ ይንጠለጠላል። ከሠላሳ ዓመቱ ሲያልፍ ግን የሀገሩን ባህል መያዙ አይቀርም“ የሚል አባባል አላቸው። ኢትዮጵያዊያን ወጣቶችም በሙዚቃው ረገድ እንደጃፓናውያኑ ሁሉ የአውሮፓና አሜሪካን ቢመኙም ዕድሜያቸው ሲጨምር ግን የሀገር ውስጥ ሙዚቃዎች ላይ ትኩረት የማድረግ ዝንባሌ እንዳላቸው ይስተዋላል። ይህ ልምድ አለባበሱ ላይም ቢደገም አያሌ የዕደጥበብ ውጤቶችን ወደገቢ መለወጥ ብቻ ሳይሆን ባህሉን የጠበቀ ትውልድ ማፍራት ያስችላል፤ የሰው ወርቅ አያደምቅ ነውና።

[ምንጭ፤ አዲስ ዘመን፤ (ዕለተ ሰንበት፤ ረቡዕ፤ ህዳር 7፣ 2018)፤ ለወጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ምንባቡን ስታነቡ የቅድመንባብ ግምታችሁ ትክክል ሆኖ አገኛችሁት? እንዴት?

ለ. በመንገድ ላይ ከሚያገኙት ሰው በግምት 90 በመቶው ከባህላዊ ውጪ የሆኑ አልባሳት እንደሚጠቀም መታዘብ ይቻላል፤ በሚለው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. አብዛኛው የጎብረተሰብ ክፍል ባህላዊ ልብሶቻችንን ከበዓላት ውጪ የማይለብሰው ለምን ይመስላችኋል?

መ. ከታሪኩ ያስደነቃችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን?

ሠ. ባህላዊ ልብሶቻችን ተገቢውን ክብር እንዲያገኙና በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ቃላት

መምህራችሁ ሰሌዳ ላይ ቃላት ይጽፉላችኋል። ቡድኑን ወክለው ፊትለፊት ለሚቀመጡት የቡድን ጓደኞቻችሁ የቃላቱን ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ በመንገር፣ በሥዕል ወይም በድርጊት በማሳየት ቃሉ ምን እንደሆነ እንዲገምቱ አድርጉ።

መጻፍ

የተሠመረባቸው ቃላት/ሐረግ ያለባቸውን ግድፈት በማስተካከል አንቀጹን እንደገና ጻፉ።

የአውሮኘላኑ በር ከፈተ። ጭንቀቱ ጀመረ። በአጠገቤ የነበረው አስተናጋጅ ችግሬን ነገርኩ። ጎርነን ባለና በቁጣ ቃና ልመከረኝ ሞከረ። መሳሳቴ ገባኝ። ምክር መጠየቅ የነበረብኝ ሴት አስተናገጁን ነበር።

1.1.5 ክለሳ

ቃላት

“ልብሴን ኖር በሉት” ከሚለው ምንባብ ውስጥ አስር ስም የሆኑ ቃላትን ለይታችሁ ጻፉና በዐምስቱ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የሰው ወርቅ አያደምቅ” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብ ተለማመዱ።

1.2.1 መጻፍ

1. የቃላቱን ቦታ በማስተካከል ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

   ሀ. ፈታይ ናት ጎበዝ እናቴ።

   ለ. በባህላዊ ደምቋል ዘፈንና ጭፈራ ዳሱ።

   ሐ. ተገዝቶለታል አዲስ ልብስ ጓደኛዬ ለአውድዓመት።

   መ. ዓይነት ለብሰዋል አንድ ሚዜዎቹ ልብስ የባህል።

   ሠ. በሚዜዎቻቸው ሙሽሮቹ ወጡ ከሴቷ ቤት ታጅበው።

2. ከሚከተሉት ሥርዓተነጥቦች መርጣችሁ ጽሑፉን አስተካክላችሁ ጻፉ።

፣ ። “ ” ? !

ደምሌና በሪሁን ከብት ጠባቂዎች ናቸው _____ ለቡሄ የተገዛላቸውን ቁምጣና በቁልፍ ያጌጠ ሸሚዝ ለብሰው _____ አዲሱን “በረባሷቸውን“ አድርገው _____ ትኩስ ሙልሙል ዳቧቸውን በአገልግል ይዘውና ጅራፋቸውን በትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ከብቶቻቸውን ወደዱር እየነዱ ነው _____

በጣም አምሮብሃል በል _____ መቼ ነው የተገዛልህ _____ አለ ደምሌ በሪሁንን በጎን እያየ። _____ ትናንትና ነው ከማክሰኞ ገበያ የተገዛልኝ _____ ሲል በሪሁን መለሰ።

_____ እስኪ ሙልመልህን አሳየኝ _____ አለ ደምሌ ወደበሪሁን አገልግል እያየ።

በሪሁን አገልግሉን ከፍቶ ሲያሳየው፣ _____ ያንተ ሙልሙል ደሞ እንዴት ያስጎመጃል ጃል _____ አለና አንዱን ላፍ አደረገው። _____

ተው መልስልኝ _____ አለ በሪሁን የልቅሶ ቃና በተጫነው ድምፅ።

1.2.2 አንብቦ መረዳት

አውደዓመትና የሀገር ባህል ልብሶች

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. በበዓላት የሚለበሱ የባህል ልብሶች ምን ምን ናቸው?

ለ. በበዓላት ጊዜ የባህል ልብስ ለምን ይለበሳል?

አውደዓመትና የሀገር ባህል ልብሶች

የአካባቢው ወጣቶች ለአውደዓመቱ መሰናዶ የጀመሩት በዋዜማው ነበር። ወጣት ሴቶችና ወንዶች ይህችን ቀን በጉጉት ሲጠብቋት ነበር። ለዚህም ነው በዓሉን ባማረና በደመቀ ሁኔታ ለማሳለፍ በፉክክር መንፈስ ተፍ ተፍ የሚሉት። በዓሉ የሚከበርበትን ቦታ አጽድተዋል። አካባቢውን በሰንደቅ ዓላማና ልዩ ልዩ መልእክቶች ባሏቸው ጽሑፎች አስውበዋል። የበዓሉ ተሳታፊዎች ወደበዓሉ ማክበሪያ ቦታ የሚመጡበትን መንገድ በመደልደልና በማስተካከል ምቹ አድርገዋል። ለታዳሚዎች ማረፊያ ዳስ ጥለዋል፤ መቀመጫ ወንበሮችንም አሟልተዋል። ምግብና መጠጡም በዓይነት በዓይነት ተዘጋጅቷል።

በዋናው የበአል ቀን ወጣቶቹ በአብዛኛው ተመሳሳይ የሀገር ባህል ልብስ ለብሰው ከሁሉም ቀድመው በቦታው ተገኝተዋል። ቀስበቀስ የበአሉ ማክበሪያ ቦታ በታዳሚዎች ተሞላ። በአውደዓመቱ ጎልተው የታዩት በርካታ አዳዲስ የሀገር ባህል ልብስ ዓይነቶችና አለባበሶች ትኩረት ሳቢ ናቸው። በፋብሪካ በተሠራ ካናቴራ ላይ ጥለት አሰፍተው የለበሱና በካናቴራው ላይ ጥበብ ያለው ሰደርያ የደረቡም ነበሩ። አንድ ዓይነት ጥበብ የለበሱ ሴት ጓደኛሞች እዚህም እዚያም ይታያሉ። በርግጥ ያንዳንዶቹ ጥለቱ ተመሳሳይ ሆኖ አሠራሩ ግን መጠነኛ ልዩነት አለው።

“ለአውደዓመት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ”፤ የሚለው ዕድሜ ጠገብ ብሂል በዕውን ታይቷል ማለት ይቻላል። በዘንድሮው አውድዓመት ለየት ብሎ የታየው ነገር በአሠራር ከተለመደው ወጣ ያሉ ያገር ባህል ልብሶች መበራከታቸው ነው። በእውቅ ዲዛይነሮች የተዘጋጁ የሀገር ባህል የጥበብ ልብሶች በብዛት በበዓሉ ታዳሚዎች ተለብሰዋል። ከፋብሪካ በተሠሩ ጨርቆች ላይ ጥበብ የተለጠፈባቸው ያገር ባህል ልብሶችም ተስተውለዋል።

ለአውደዓመቱ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ከቀረበ በኋላ ጭፈራ ተጀመረ። በመጀመሪያ ሴቶችና ወንዶች ለብቻቸው ከዘፈኑ በኋላ ጭፈራው እየደመቀ ሲሄድ ግን አንድ ላይ መጨፈር ጀመሩ። በተለይ ተመሳሳይ የባህል ልብስ የለበሱ ወጣቶች አንድ ላይ በሚጨፍሩበት ጊዜ የሚታየው ትእይንት አፍን የሚያስከፍት ነበር። አውደዓመት ሁሉም በአቅሙ አምሮና ደምቆ የሚታይበት በዓል ስለሆነ ሁሉም የወደደውን ለብሶ ሲታይ በጣም ደስ ይላል።

[ምንጭ:- ምሕረተሥላሴ መኮንን፣ (ጥር 14/ 2011 ዓ.ም)፤ ሪፖርተር ጋዜጣ፤ ፣ ለወጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ወጣቶቹ የአውደዓመቱን ዝግጅት የጀመሩት መቼ ነበር?

ለ. በአውደዓመቱ ጎልቶ የታየው ምን ነበር? ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. "ለአውደዓመት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ"፤ ማለት ምን ማለት ነው?

መ. የዘንድሮውን አውደዓመት ልዩ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?

ሠ. ከምንባቡ ውስጥ የማረካችሁን አለባበስ በሥዕል አሳዩ።

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ዋዜማ	ሰደርያ	በእውን	ሰንደቅዓላማ	አውደዓመት

መጻፍ

የቃላቱን ቦታ በማስተካከል ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. እንደተመለሰ ኡስማን ቀየረ ከትምህርትቤት ልብሱን።

ለ. ተጨናንቋል በመኪኖች መንገዱ በእግረኞችና።

ሐ. በሥነተዋልዶና ጤና ማርቆስ ክበብ ይሳተፋል።

መ. አበቦችና በልዩ ልዩ ዛፎች ትምህርትቤታችን ነው ያማረ።

ሠ. አንደኛ በመውጣቷ ተሸለመች መጽሐፍ አርሴማዊት ከክፍሏ ተማሪዎች።

1.2.3 ሰዋስው

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በወል ስምና በተጸውኦ ስም መድባችሁ ጻፉ።

ደም	መምህር	ዛፍ	ተራራ	ራስደጀን	ጣና
ተክዜ	ጎንደር	ማህሌት	ሰው	ሀገር	ፍየል

ለ. በወል ስም ምድብ በጻፋችኋቸው ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“አውደዓመትና የሀገር ባህል ልብሶች” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብ ተለማመዱ።

1.2.4 አንብቦ መረዳት — ጥንግድርብ

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ጥንግድርብ ምን ዓይነት ልብስ ይመስላችኋል?

ለ. ጥንግድርብ የት አካባቢ የሚለበስ ልብስ ይመስላችኋል?

ጥንግድርብ



ከጐጃም ማኅበረሰብ መገለጫ አልባሳት መካከል ጥንግድርብ በመባል የሚታወቀው የልብስ ዓይነት አንዱ ነው። ይህ የባህላዊ ልብስ ዓይነት በተለይም በቤተክህነት ትምህርታቸው ከፍተኛ ማዕረግ በደረሱ የሃይማኖት አባቶች ይለበሳል። ቀደም ባለው ጊዜ ደግሞ የተለያየ ማዕረግ ባላቸው የቤተ-መንግሥት መኮንኖች፣ ግራዝማኞች፣ ቀኛዝማኞች፣ ፊታውራሪዎችና የመኳንንት ሚስቶች ብቻ የሚለበስ የክብርና የታላቅነት መገለጫ ልብስ ነበር። ልብሱ በተለያዩ ክብረ በዓሎችና ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ጊዜ ይዘወተራል።

ጥንግድርብ፣ በሌላ ስሙ ባለሦስት ፈርጅ ስፌት በመባል የሚታወቅ ነው። ይህ ስያሜ የተሰጠበት ምክንያትም ሦስት ጋቢዎች አንድ ላይ ተሰፍተው ጥንግድርብን የሚፈጥሩ በመሆናቸው ነው። ጥንግድርብ የሦስት ጋቢዎች ውጤት ነው ማለት ነው። ሶስቱ ጋቢዎች በቁመታቸው ቁልቁል ተዘቅዝቀው ይሰፉና በቁመታቸው ተዘቅዝቀው ይለበሳሉ።

ጥንግድርብ ወይም ባለሦስት ፈርጅ ጋቢ ከሌላው የጋቢ ዓይነት ይልቅ በመጠኑ በጣም ትልቅ ነው። በተለይ ወርዱ ከተራው ጋቢ በጣም የበለጠ ነው። ከአካባቢው ጥሬዕቃ (ጥጥ) የተለያዩ የፈትልና የስፌት ደረጃዎችን አልፎ የሚዘጋጅ ነው።

የጥንግድርብ አሰራር ከሌሎች ጋቢዎች ይለያል።ጋቢው ዘሃ በዘሃ በማጠላለፍ ብቻ ይሰራል፤ እንዲሁም በጠርዙ ላይ ትንሽ፣ ወደመሃል ገባ ብሎ ደግሞ በጣም ሰፋ ያለ ጥለት ይጣልበታል። በጥለቱም ላይ የተለያዩ ዓይነት ጥልፎች ይጠለፉበታል። ጥለቱ ጐልቶ እንዲወጣና እንዲታይ ተብሎ ህዳግ ወይም ክፍተት እንዲኖረው ይደረጋል። የተተወው ህዳግ ልብሱ ውበትና ድምቀት እንዲኖረውና ከሌሎች ተራ ጋቢዎች እንዲለይ ያደርገዋል። ምክንያቱም ጥንግድርብ የክብርና የታላቅነት መገለጫ ስለሆነ።

[ምንጭ:- ምሥራቅ ጎጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም፣ ድረገጽ፤ (2008ዓ.ም)]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ጥንግድርብን የሚለብሱት እነማን ናቸው?

ለ. ጥንግድርብን የሚለብሱት ምን ዓይነት ሴቶች ናቸው?

ሐ. ሰዎች ጥንግድርብን የሚለብሱት መቼ መቼ ነው?

መ. ጥንግድርብ የክብርና ታላቅነት መገለጫ የሆነው እንዴት ነው?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፦ ህዳግ = ክፍተት

መገለጫ	ጥሬዕቃ	ቁልቁል	ዘሃ	ማዕረግ

መጻፍ

የሚከተሉትን ጅምር ዓረፍተነገሮች አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. ከጓደኞቼ ጋር _____።

ለ. _____ ከትምህርትቤት ቀረሁ።

ሐ. በጣም የምወደው ጨዋታ _____።

መ. _____ ደስ ብሎኛል።

ሠ. ጠንክሮ የሠራ _____።

1.2.5 ክለሳ

አቀላጥፎ ማንበብ

"ጥንግድርብ" በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብ ተለማመዱ።

ሰዋሰው

1. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት በትክክል ጻፉ።

ምሳሌ፡-	በላ	በላሁ	በላህ	በላሽ	በላች	በላን	በላችሁ	በሉ

መጣ	ሠራ	ለበሰ	ደረሰ	ዘመረ	አነበበ

2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሣሌ፡- አረጋሽ የፈሰሰውን እህል <u>አፈሰች</u>።

ሀ. አፈሰች

ለ. ጠረገ

ሐ. አጠቡ

መ. ፈለጠ

ሠ. አሸነፈች

1.3.1 ማዳመጥ

በርኖስ

ቅድመማዳመጥ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ከሥዕሉ ምን ትገነዘባላችሁ?

ለ. በርኖስ ምን ዓይነት ልብስ ይመስላችኋል?

ሐ. በርኖስ ከምን የሚሠራ ይመስላችኋል?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በርኖስ ለምን ዓይነት ማኅበራዊ ሁኔታዎች አገልግሎት ላይ ይውላል?

ለ. “ሁሉም የበግ ፀጉር ለበርኖስ ሥራ ያገለግላል።” በዚህ ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. የበጎቹ ፀጉር ቁርበት ላይ ተደርጎ የሚሸለተው ለምንድን ነው?

መ. ለበርኖስ ሥራ የሚያገለግሉት በጎች ባለረጃጅም ፀጉር መሆን ያለባቸው ለምንድን ነው?

ሠ. በአንደኛው ትከሻ በኩል ወጣ ያለው የበርኖስ ቅርጽ አገልግሎት ምን ይመስላችኋል?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሐዘን	ጠንካራ	ቆሻሻ
ለስላሳ	ብርድ	ነጣጥሎ

ውቧ ያገሬ ልጅ

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ከርዕሱ በመነሳት ግጥሙ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. የውበት መግለጫ ቃላት ምን ዓይነት ይመስሏችኋል?

ውቧ ያገሬ ልጅ

ያገሬ ልጅ ውበት ጎልቶ ይነበባል፣
እንደበላይ አልቢን በሩቁ ይጥላል፣
ሹሩባ አሰራርሽ አሸንክታብ ጌጥሽ፣
ባለትፍትፍ ቀሚስ ውቡ መቀነትሽ፣
ተዋህዶ አንድ ላይ ከተክለቁመናሽ፣
አንቺ ልጅ በርግጥም ድንቅ ኢትዮጵያዊ ነሽ።

አንቺ ኢትዮጵያዊት የውበት ሰገነት፣
ታንጸሽ አድገሻል በውብ ባህል እምነት።
እኔ ውበት ማድነቅ ቅኔ መች አውቅና፣
ስደልዝ ስሰርዝ ስጽፍ እንደገና፣
ቀናቶች አለፉ በላንባ ጭላንጭል፣
ወረቅት ዘርግቼ ቃላት ሳንከባልል።
እናም ባይሰምርልኝ ስንኙ ቢንጋደድ፣
ቤት መምታቱ ቢያቅተኝ ሐሳብን ማዋደድ፣
አድንቄ ለራሴ በውስጤ ልቅበረው፣
ሐበሻዊት መሆን በራሱ በቂ ነው!

[ምንጭ፤ ስንታየሁ ሐብታሙ። (2017)። የግጥም ተሰጥኦ፤ ከማሻሻያ ጋር የተወሰደ]

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከበላይ አልቢን ጋር የተነፃፀረው ምንድን ነው?

ለ. የውበት ሰገነት የተባለችው ማን ናት?

ሐ. ገጣሚው ስለጻፈላት ሴት ምን ዓይነት ስሜት አለው? እንዴት አወቃችሁ?

መ. እናታችሁን ወይም አባታችሁን የሚያመሰግን አጭር ግጥም ጻፉ።

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በግጥሙ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሰገነት	ተክለቁመና	ሳንከባልል	ማዋደድ
አሸንክታብ	ታንፀሸ	ቢንጋደድ	ልቅበረው

መጻፍ

ባለፈው ክፍለጊዜ ያዘጋጃችሁትን የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር በመጠቀም ስለበርኖስ አሠራር አጭር አንቀጽ ጻፉ።

1.3.3 ማዳመጥ — በርኖስ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "በርኖስ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ዋና ሐሳቦች በማስታወስ ተናገሩ።

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. አንድ በርኖስ ለመሥራት የስንት በጎች ፀጉር ያስፈልጋል?

ለ. በተደጋጋሚ የተሸለቱ በጎች ፀጉራቸው ለበርኖስ ሥራ የማያገለግለው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. አንድ በርኖስ ወደልብስነት ሲቀየር ለስንት ሰው ይሆናል?

መ. በርኖስ የት አካባቢ የሚለበስ ይመስላችኋል? ለምን?

ሠ. ለበርኖስ ሥራ ጥቁር በጎች የሚመረጡት ለምን ይመስላችኋል?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ይሸለታል	ተጎሳቆለ	እስኪልም	መፍተል
ይኮሰኩሳል	ቁርበት	አመልማሎ	ማድራት

አቀላጥፎ ማንበብ

“ውቧ ያገሬ ልጅ” በሚለው ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብ ተለማመዱ።

1.3.4 አንብቦ መረዳት

ውበት

ቅድመንባብ

“ውበት” በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ውበት

ውበት ዓይነት ዓይነት አለው። ውጫዊ ውበት አለ፤ ውስጣዊ ውበት አለ። የመልክ፣ የተክለሰውነት፣ የቀለም፣ ወዘተ ውበቶች ውጫዊ ውበቶች ናቸው። ከውጫዊው የሚበልጠውና ጎልቶ እንዲታይ የሚፈለገው ደግሞ ውስጣዊው ውበት ነው። ውስጣዊ ውበት ጥሩ ባህርይ፣ መልካም ሥነምግባር፣ ደግነት፣ ታማኝነትና የመሳሰሉትን ያካትታል። የሰዎችን ውጫዊ ውበት አጉልተው ከሚያሳዩ ነገሮች መካከል ዋነኞቹ የባህል ልብሶች ናቸው።

የባህል ልብሶቻችን ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የማንነታችን መገለጫዎቻችን ናቸው። አለባበሳችን ከሌሎች የዓለም ሕዝቦች የተለየን ያደርገናል። የትም ብንሄድ ባህላዊ አለባበሳችን ኢትዮጵያዊነታችንን ይገልፃል። የምንለብሰው የባህል ልብስ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከወሎ፣ ከሸዋ ወይም ከሌላው የኢትዮጵያ አካባቢ እንደመጣን የሚገልጽ መታወቂያችንና መዋቢያችን ነው። የባህል ልብስ መገለጫነቱ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገራትም ጭምር ነው። በየትኛውም የዓለም ክፍል ብንሄድ ከሌላው ሰው ተለይተን እንድንታይ የሚያደርገን ምልክታችን ነው። በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በኤስያ ወዘተ የሚኖርን ኢትዮጵያዊ የእኛ ሰው መሆኑን በቀላሉ የለበሰውን ባህላዊ ልብስ በማየት መለየት እንችላለን።

እነዚህ ባህላዊ ልብሶች የራሳችን የእደጥበብ ውጤቶች ናቸው። ጥሬ እቃዎቹም ሆነ ወደልብስነት ቀያሪዎቹ ጥበበኞች የኛው ናቸው። ዓይነተብዙነታቸውም የሸማ ሠሪዎችን ጥበበኛነት አጉልተው ያሳያሉ። በልብሶቹ ላይ የሚታዩት ጥልፎች፣ ጌጣጌጦችና ጥበቦች ህብር ፈጥረው ቀልብ የሚስቡት በእኛው ጥበበኞች ተሠርተው ነው። በእኛው ተሠርተው ለእኛው ስለሚቀርቡ በራስ መተማመናችንን ከፍ ያደርጋሉ።

አብዛኞቹ ወደሀገራችን የሚመጡ ቱሪስቶች ልብሶቻችንን ይገዛሉ፤ ይለብሳሉ። የዚህም ምክንያቱ ከተፈጥሯዊ ጥጥ በቀጥታ የሚዘጋጁ ከመሆናቸውም በላይ ውበትና ምቾት ስላላቸውም ነው። በተጨማሪም ያገር ባህል ልብሶች በማንኛውም ጊዜ ሊለበሱ የሚችሉ በመሆናቸው ጠቀሜታም፣ ተመራጭነትም አላቸው። በእነዚህ ተመራጭነት ባላቸው ልብሶች ሁላችንም ልንኮራ ይገባል።

ዋናው ነገር የእኛ የሆነውን ለእኛው ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ ነው። የባህል ልብሶቻችንን ባዘቦትም ሆነ በበአላት የምንለብሳቸው ከሆነ ሌላው ሀገርና ሌላው ሕዝብም እኛ የምንሰጠውን ክብር ያህል ለባህል ልብሶቻችን መስጠቱ አይቀርም። ይህ ደግሞ በባህል ልብሶቻችን ራሳችንን ከማስዋብ ባለፈ ሀገራችንን በገቢ ማሳደግ ያስችለናል።

[ምንጭ:- አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ፣ የተማሪ መጽሐፍ፣ 6ኛ ክፍል። (2007)። ገጽ 17፤ ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “የባህል ልብሶቻችን የማንነት መገለጫዎቻችን ናቸው።” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. የባህል ልብሶቻችን በራስ መተማመናችንን ከፍ የሚያደርጉት እንዴት ነው?

ሐ. የባህል ልብሶቻችንን ቱሪስቶች የሚመርጧቸው በምን ምክንያት ነው?

መ. የባህል ልብሶቻችንን በመልበስ ሀገራችንን እንዴት መደገፍ እንችላለን?

ሠ. የሀገር ባህል ልብሶችን መልበስ ትወዳላችሁ? ለምን?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፦ ባህላዊ ልብሶቻችን የራሳችን <u>የእደጥበብ</u> ውጤቶች ናቸው።

ጥበበኛ	ህብር	የእደጥበብ	ቱሪስቶችም	ቀልብ	የሚስብ	ጥሬዕቃ

ሀ. ባህላዊ ልብሶቻችን የራሳችን _____ ውጤቶች ናቸው።

ለ. የባህል ልብሶቻችን የሚሠሩበት _____ ከሀገር ውስጥ የሚገኝ ነው።

ሐ. በልብሶቹ ላይ የሚታዩ ጥልፎች፣ ጌጣጌጦችና ጥበቦች _____ ፈጥረው ዓይንን ይስባሉ።

መ. ጌጤ በእውቅ የባህል አልባሳት _____ የተሠራ ቀሚስ በመልበሷ ሁለመናዋ _____ ሆኗል።

ሠ. የኢትዮጵያን ባህላዊ ልብሶች አገሬው ብቻ ሳይሆን _____ ወደውታል።

መጻፍ

ሀ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።



ለ. ቢጋሩን በመጠቀም የሚከተለውን ጅምር አንቀጽ አስፋፍታችሁ ጻፉ።

ቀኑ የዘመን መለወጫ በዓል ዋዜማ ነው። በዚህም ምክንያት እናቴ ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ልትገዛ፣ ለእኔም ልብስና ጫማ ልትገዛልኝ ወደገበያ አብረን ሄድን። ወደገበያ ስሄድ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፤ በመሆኑም በገበያው ውስጥ የምመለከተው ነገር ሁሉ አዲስ ሆኖብኝ በትኩረት እመለከት ጀመር።

1.3.5 ክለሳ

መጻፍ

ባለፈው ክፍለጊዜ ያሟላችሁትን የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር በመጠቀም ጅምሩን አንቀጽ አስፋፍታችሁ ጻፉ።

ሰዋስው

1. የሚከተሉትን ቃላት በወልና በተፀውኦ ስም ምድብ ለይታችሁ ጻፉ።

ግመል	ወልድያ	ልብስ	ቤት	ላንጋኖ
አርሶአደር	ማሽላ	ሱዳን	ጊቤ	ፀሐይ

2. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የዋህ ኃላፊ ግሶቹን ለይታችሁ ጻፉ።

   ለምሣሌ፦ አርሶአደሩ ማሽላውን ቆረጠ።

   ሀ. መምህር የተማሪዎቹን ደብተር ያርማሉ።

   ለ. የኢትዮጵያ ሕዝብ አባይን ገደበ።

   ሐ. ዘርትሁን ከምንጩ ውኃ ትቀዳለች።

   መ. እነመኮንን ወደአዲስ አበባ ሄዱ።

   ሠ. ነጋዴው እህሉን ሰፈረ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ውበት” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

ምዕራፍ 2 ታዋቂ አትሌቶች

2.1.1 ማዳመጥ

ተከብሮ ያስከበረ

ቅድመማዳመጥ



በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ።

ሀ. ከርእሱና ከሥዕሉ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. ከስፖርታዊ የውድድር ዓይነቶች የትኛውን የበለጠ ትወዳላችሁ? ለምን?

ሐ. የምታውቋቸውን አትሌቶች ስም ተናገሩ። ከምታውቋቸው አትሌቶች ማንን የበለጠ ታደንቃላችሁ? ለምን?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. አበበ ቢቂላ የኦሎምፒክ ውድድርን ለመጀመሪያ ጊዜ ያሸነፈው የት ነበር?

ለ. ኢትዮጵያ ስሟ ከኦሎምፒክ ጋር እንዲጣመር ያደረገው ምን ነበር?

ሐ. አበበ ቢቂላ የጽናት ተምሳሌት ሆኖ የታየው በምን ምክንያት ነው?

መ. ኢትዮጵያ የአበበ ቢቂላን ውለታ የከፈለችው በምን መልኩ ነው?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተመሳሳይ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. አማተረ	ሀ. ተቆራኘ
2. ተምሣሌት	ለ. አሸናፊነት
3. የአጥቢያ ኮከብ	ሐ. ተንዙ
4. ተጣመረ	መ. ፈርቀዳጅ
5. ድል	ሠ. ምልክት
6. ተመሙ	ረ. ተመለከተ
	ሰ. ታሰረ
	ሸ. ሸንፈት

2.1.2 አንብቦ መረዳት

ካይላ ዊለር

ቅድመንባብ

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ፍቺ ጻፉ።

ሻምፒዮን	አካልጉዳተኛ	የይቻላል መንፈስ

ካይላ ዊለር



አካልጉዳተኝነታቸው ሳይበግራቸው ለስኬት የበቁ የሀገራችንና የውጭ ዜጎች በርካታ ናቸው። ከማኅበረሰቡ የሚደርስባቸውን ባህላዊና ማኅበራዊ ጫና ተቋቁመውና ያላቸውን አካል ጥበብ በታከለበት ሁኔታ ተጠቅመው ከሌሎች ሰዎች እኩል ማንኛውንም ተግባር መፈጸም እንደሚችሉ በተግባር አሳይተዋል። በማኅበራዊው፣ በኢኮኖሚያዊውና

በፖለቲካዊው እንቅስቃሴ ሁሉ ሙሉ አካል ካላቸው ወንድምና እህቶቻቸው ጋር እኩል በመሰለፍ አገራቸው የምትጠብቅባቸውን ኃላፊነት ሳያጓድሉ ፈጽመዋል። የሚሰጣቸውን ሥራ ትኩረት ሰጥተው፣ ጥራትና ብቃት ባለው ሁኔታ በጊዜው በማጠናቀቅ ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ ሊሆኑ እንደሚችሉ የብዙ አካል ጉዳተኞች ታሪክ ምስክር ነው። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶች ደግሞ አስገራሚ ተግባሮችን ሲፈጽሙ ማስተዋል የአደባባይ ሃቅ ነው። በሳይንስና ቴክኖሎጅ፣ በእለት ተእለት የኑሮ ተግባራት፣ በስፖርት ወዘተ አንቱ የተባሉ አካል ጉዳተኞች አሉ። ከእነዚህ መካከል አንዷ ካይላ ዊለር ናት።

ካይላ ዊለር በትምህርት ብቃቷና በዓለምአቀፍ የዋና ሻምፕዮንነቷ የሁሉንም ቀልብ የሳበች አካልጉዳተኛ ወጣት ናት። ኹለት እግርና አንድ እጅ የላትም። ወላጆቿ ልጃቸው በዚህ ዓይነት አካል ጉዳተኝነት ስትወለድ ፈጣሪያቸውን ከማማረርና ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ለልጃቸው ጥንካሬ አላበሷት። ማንኛውንም ነገር ከማድረግ የሚያግዳት ነገር እንደሌለ በማስገንዘብ በይቻላል መንፈስ አሳደጓት። በህጻንነት ዕድሜዋ እኩዮቿ የሚያደርጉትን በሙሉ እንድታደርግ ይገፋፏት ነበር። በዚህም እንደህጻናት ቦርቃና ተጫውታ አደገች። ወደትምህርትቤት ለመግባትም ያገዳት አንዳችም ነገር አልነበረም። የአካል ድጋፍ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን በመጠቀምና ከመምህሮቿ በምታገኘው እገዛ ትምህርቷን በስኬት ቀጠለች። ሃኪሟም በትምህርቷ እንድትጠነክርና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን እንድታደርግ ይመክሯት ነበር። በየጊዜው የጤንነቷን ሁኔታ እየተከታተሉ ማድረግ ስለሚገባት ጥንቃቄ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጧት ነበር።

ዊለርም በቤተሰቦቿና በሐኪሟ ያላሰለሰ እገዛ ጠንክራ በመሥራት በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት አስመዘገበች። በትምህርቷ ከምታሳያቸው ስኬቶች በተጨማሪ በሥነምግባሯና ለሰብዓዊነት ባላት ክብርም አንቱታን ያተረፈች ሆነች። ከትምህርቷ ውጪ ያለውን ጊዜዋን የምታሳልፈው በሃኪሟ ምክር እየታገዘች የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ነው። ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች መካከል አብልጣ የምትወደውና አዘውትራ የምታከናውነው ደግሞ የዉኃ ዋናን ነው። የተለያዩ ርቀቶችን የሚሸፍኑ የዋና ልምምዶችን ታደርጋለች። ራሷን ለማዘናናት የጀመረችውን የዉኃ ዋና ልምምድ አጠናክራ በመቀጠሏ ችሎታዋ ከፍተኛ እየሆነ መጥቶ በአገሯ የአካል ጉዳተኞች ውድድር ላይ ለመሳተፍ በቃች። ቀስበቀስም ታዋቂነትን እያገኘች መጣች። በዚህም ዊለር በ16 ዓመቷ የ50 ሜትር የአካል ጉዳተኞች የዉኃ ዋና ውድድርን ክብረወሰን በማሻሻል ሻምፕዮን ለመሆን በቃች።

ዊለር ለሌሎች አካል ጉዳተኞች አርኣያ መሆን ራዕይዋ ነው። ይህንን ራዕይዋን ለማሳካትም ሌትም ቀንም ያለመሰልቸት ልምምዷን ትሰራለች። በተለያዩ ርቀቶች በተለያዩ የአውሮፓና የላቲን አሜሪካ አገሮች እየተዘዋወረች ውድድሮችን በማድረግ ህልሟን በተግባር የፈፀመች ጀግና ለመባል በቅታለች።

[ምንጭ:- ዘሃበሻ ስፖርት። (2018)። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።]

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ካይላ ዊለር በተለይ የምትታወቅበት የስፖርት ዘርፍ ምንድን ነው?

ለ. ካይላ ዊለርን የአካል ጉዳተኝነቷ ሳያግዳት በትምህርቷና በስፖርት ስኬታማ እንድትሆን የረዳት ምንድን ነው?

ሐ. ከምንባቡ ያስደነቃችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን?

መ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ? እንዴት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ፍቺ ጻፉ።

ብቃት	ራዕይ	ዓለምአቀፍ	አርኣያ	ያላሰለሰ	ክብረወሰን

መጻፍ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ጻፉ።

ሀ. አካልጉዳተኛነት አንድ ሰው ያሰበውን ከማድረግ የሚያግደው ይመስላችኋል?

ለ. አንድ ሰው ካሰበበት ለመድረስ ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ? ለምን?

2.1.3 ማዳመጥ — ተከብሮ ያስከበረ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ተከብሮ ያስከበረ” በሚል ርዕስ የተነበበላችሁን ምንባብ አስታውሳችሁ ዋናውን ሐሳብ ተናገሩ።

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. “የዓለም ዐይኖች ከሮም ወደኢትዮጵያ ዞሩ” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ኢትዮጵያ ከአበበ ቢቂላ ድል ያገኘችው ጥቅም ምንድን ነው?

ሐ. ከታሪኩ ውስጥ በጣም ያስደነቃችሁ ምንድን ነው?

መ. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ? ይህን መማራችሁ ምን ሊጠቅማችሁ ይችላል?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ከፍ አደረገው	ማዕረግ	መስዋእትነት
የዓለም ዐይኖች	ውለታ	ጽናት

ሀ. ሻለቃ መኳንንት በጦር ግንባር በፈፀመው ጀብዱ የኮሎኔልነት _____ አገኘ።

ለ. በአትሌቲክስ ስኬታማ ለመሆን _____ ያስፈልጋል።

ሐ. በአፍሪካ ትልቁን የህዳሴ ግድብ ለመገንባት ስንነሳ _____ በኢትዮጵያ ላይ አነጣጠሩ።

መ. ኢትዮጵያ አንድነቷ ተጠብቆ የኖረው አባቶቻችን በከፈሉት _____ ነው።

ሠ. አበበ ቢቂላ በኦሎምፒክ መድረክ በፈፀመው ጀብዱ የኢትዮጵያን ስም በአለም ደረጃ _____።

ረ. ኢትዮጵያ ተከብሮ ባስከበረን ልጇ መስዋዕትነት ከራሷ አልፋ ለሌሎችም _____ ዋለች።

አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት “ካይላ ዊለር” የሚለውን ምንባብ አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

2.1.4 አንብቦ መረዳት

የደስታ መግለጫ ደብዳቤ

ቅድመንባብ

የደስታ መግለጫ ደብዳቤ ምንድን ነው? በምን አጋጣሚ ይጻፋል?

የደስታ መግለጫ ደብዳቤ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈትቤት

ቁጥር ጠ80-አጠ88/07/03

ቀን 22 መስከረም 1993 ዓ.ም

ለኦሎምፒክ ኮሚቴና ለአትሌቶቻችን

ሲድኒ

ጉዳዩ፡- የተሰማንን ደስታ ስለመግለጽ፤

ከአበበ ቢቂላና ከማሞ ወልዴ አስደናቂ ድል በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲናፍቀው የቆየውን የማራቶን ድል እውን ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ ላደረጉና ድል ለተጎናፀፉት ጀግኖች አትሌቶቻችን ያለንን ከፍተኛ አድናቆትና ክብር ለመግለጽ እንወዳለን። በተለይ ደግሞ ከግል ክብር ይልቅ የሀገርን ክብር በማስቀደም ጀግኖች አትሌቶቻችን ያሳዩት መተጋገዝና መደጋገፍ በአትሌቶቻችን ይበልጥ እንድንኮራና እንድንተማመን አድርጎናል።

ከሠላምታ ጋር

ፊርማ

ሙሉጌታ ዓለምሰገድ

የጠቅላይ ሚኒስቴር ልዩ ጽሕፈትቤት ኃላፊ

ምንጭ፡- ኦሎምፒክና ኢትዮጵያ፤ 1993፣ ገጽ 81)

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደብዳቤው መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የደስታ መግለጫ ደብዳቤው የተጻፈው መቼ ነው?

ለ. የደስታ መግለጫውን የጻፈው ማን ነው? የጻፈውስ ለማን ነው?

ሐ. "የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲናፍቀው የቆየውን የማራቶን ድል" ከሚለው አገላለፅ ምን ተረዳችሁ?

መ. የደስታ መግለጫ ደብዳቤው ለምን ዓላማ የተጻፈ ይመስላችኋል?

ሠ. የደብዳቤው ኹለተኛ ዓረፍተነገር ከያዘው ሐሳብ ለሕይወታችሁ የሚጠቅም ምን ቁም ነገር አገኛችሁበት?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ በተሠመረባቸው ቃላት በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

አስገራሚ	መደጋገፍ	እንድንመካ	ሲመኘው	የተቀዳጀው

ምሳሌ፦ አትሌቶቻችን ላስገኙት <u>አስገራሚ</u> ድል ክብር ይገባቸዋል።

አትሌቶቻችን ላስገኙት <u>አስደናቂ</u> ድል ክብር ይገባቸዋል።

ሀ. መቶ አለቃ አጥናፉ <u>ሲናፍቀው</u> የኖረውን የማዕረግ እድገት በማግኘቱ ተደስቷል።

ለ. በደስታም ሆነ በሐዘን ጊዜ <u>መተጋገዝ</u> የኢትዮጵያውያን የቆየ ባህል ነው።

ሐ. በቅኝ ገዢዎች አለመገዛታችን በታሪካችን <u>እንድንኮራ</u> አድርጎናል።

መ. ብሔራዊ ቡድናችን በአፍሪካ ዋንጫ <u>የተጎናፀፈው</u> ድል አስደስቶናል።

መጻፍ

ራሳችሁን የትምህርትቤታችሁ ርዕሰመምህር እንደሆናችሁ አድርጋችሁ አስቡ። ያላችሁን ሥልጣን ተጠቅማችሁ የትምርትቤታችሁ የእግር ኳስ ቡድን በትምህርትቤቶች ውድድር አሸናፊ መሆኑን ምክንያት በማድረግ የደስታ መግለጫ ደብዳቤ ለቡድኑ ጻፉ።

2.1.5 ክለሳ

ቃላት

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚሉና ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡- አዲሱ <u>ሕገመንግሥት</u> በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ፀደቀ።



ሕገመንግሥት

አቀላጥፎ ማንበብ

“የደስታ መግለጫ ደብዳቤ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

2.2.1 መጻፍ

1. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማብራሪያና ማስታወሻ መሠረት የሚከተሉትን ስሞች በአጎጽሮተቃል አሳጥራችሁ ጻፉ።

   ለምሣሌ፡- የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን = እ.ማ.ማ.ኮ

   ሀ. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት

   ለ. የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር

   ሐ. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

   መ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

2. በፊደል የተጻፉትን ብርና ሣንቲሞች በአሃዝ ጻፉ።

ምሣሌ፡- ዐምስት ብር ከአሥራዐምስት ሣንቲም = ብር 5.15

ሀ. ሀያ ሰባት ብር ከሰላሣ ዐምስት ሣንቲም

ለ. አንድ መቶ ስድስት ብር ከአርባ ዐምስት ሣንቲም

ሐ. ዘጠና ስምንት ብር ከሰማንያ ሣንቲም

መ. አንድ ብር ከኃምሣ ሣንቲም

ሠ. ሦስት መቶ አሥራዐምስት ብር ከሃያ ሳንቲም

2.2.2 አንብቦ መረዳት

ህልም ሲፈታ

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ።

ሀ. በሥዕሉ የምታዩዋቸውን ነገሮች ግለፁ?

ለ. ርዕሱን ከሥዕሉ ጋር ስታስተውሉ ታሪኩ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ህልም ሲፈታ



አንዳርጌ፣ አሰፋና፣ ትርንጎ በእስቴ ወረዳ የጅባሥራ አዳጊ ከተማ ነዋሪና ተማሪዎች ናቸው። በሚኖሩበት ከተማ የ2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት ባለመኖሩ ከ8ኛ ክፍል በላይ ያለውን ትምህርታቸውን የተማሩት በግምት 12 ኪ.ሜ ከሚርቀው እስቴ መካነየሱስ ትምህርትቤት በእግር በመመላለስ ነበር። ለሳምንት ያህል ከቤተሰብ ርቆ በስንቅ መማር በብዙ የገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች ሕይወት ነው። በዚህ መንገድ ተምረው ለስኬት የበቁ ኢትዮጵያውያን እልፍ ናቸው። ምስጢሩ ዓላማን ለማሳካት ችግርን በጽናት መቋቋም ነው። አንዳርጌ፣ አሰፋና ትርንጎም ይህንኑ ነገር በደንብ ከተረዱት ውለው አድረዋል።

የበለሰና ያልበሰለ ስንቅ ተሸክመው ሰኞ ጧት ወደእስቴ ከተማ ይሄዳሉ። አርብ ከሰዓት በኋላ ወደቤተሰቦቻቸው ይመለሳሉ። የ12 ኪ.ሜ የእግር ጉዞ ሁልጊዜም በየሳምንቱ የማይቀር ግዴታቸው ነበር። ይህ የማይቀር ግዴታ ግን ጽናትን አላበሳቸው እንጂ

ሌላ የፈጠረባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ የለም። ምክንያቱም የትምህርታቸው አንድ አካል አድርገው ወስደውታልና።

እየቆዩ አንድ ሐሳብ በአእምሯቸው ተጠነሰሰ። ጉዞው ያላበሣቸው የአካል ጥንካሬና ችሎታ አትሌት የመሆን ዝንባሌ አሳደረባቸው። ይህንን ህልማቸውን ለማሣካትም የ12 ኪ.ሜ ጉዟቸውን ባብዛኛው በሩጫ ይጨርሱት ነበር። “አንድ ቀንማ” ትላለች ትርንጎ “አንድቀንማ ይህ ህልሜ እውን መሆኑ አይቀርም፤ ስሜ በድፍን ጅባሥራና በእስቱ ወረዳ መጠራቱ አይቀርም፤ እናቴ ትሙት!” ትላለች። አንዳርጌና አሰፋም “እኛም ህልማችን ይኸው ነው፤ ህልማችንን ለማሣካት ሁልጊዜም እንሮጣለን፤ አትሌት ባንሆን እንኳ ጤናችን የተጠበቀ ይሆናል” በማለት ይደግፏታል። በዚህ ምክንያት ከትምህርታቸው ጎንለጎን ሁልጊዜም ስለአትሌቲክስ ይወያያሉ፤ የጤናና የሰውነት ማጎልመሻ መምህራቸውን ይጠይቃሉ፤ በትምህርት ቤቱ ቤተመጻሕፍት የሚገኙ መጻሕፍትንም ያነባሉ።

ከመምህራቸውና ከመጻሕፍት መረጃዎችን ለማግኘት ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ የአትሌቲክስ ተግባራዊ ክህሎታቸውን ለማደበር እንዲረዳቸው ከትምህርት ሰዓት ውጪ ልምምዶችን ያደርጋሉ። በሳምንት ኹለት ቀን ጠዋት ጠዋት ይሮጣሉ፤ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ። ይህ ሁሉ ጥረታቸው በአካልና በአእምሮ እንዲጎለብቱ ዕድል ፈጠረላቸው።

ዛሬ አሰፋና ትርንጎ ኢትዮጵያን በልዩ ልዩ ዓለማቀፋዊ የውድድር መድረኮች የሚወክሉ አትሌቶች ሆነዋል። አንዳርጌ ደግሞ በትምህርቱ ገፍቶ በደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህር ሆኗል። እነዚህ የልብ ጓደኞሞች አሁንም አልፎ አልፎ ይገናኛሉ። ያለፈውን እያስታወሱ ይጨዋወታሉ። በጽናታቸው ህልማቸው መፈታቱን ሲያስቡት ልባቸው በሃሴት ይሞላል።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አንዳርጌ፣ አሰፋና ትርንጎ በእግራቸው እየተመላለሱ የተማሩት ለምንድን ነው?

ለ. የባለታሪኮቹ አትሌት የመሆን ዝንባሌ መነሻው ምን ነበር?

ሐ. የባለታሪኮቹ ህልም የተሳካ ይመስላችኋል? እንዴት?

መ. ከታሪኩ ምን ተማራችሁ? እንዴት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በታሪኩ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ስንቅ	ዝንባሌ	አሳደረባቸው	ያላበሳቸው	በድፍን	ገፍቶ

መጻፍ

የራሳችሁን ወይም የሌላን ሰው ተመሳሳይ ገጠመኝ በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

2.2.3 ሰዋስው

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

እውን	ህልም	ገፋ	መድረኮች	የማይቀር	ደገፈ

ለ. ከሚከተሉት ቃላት ጥቅል ስም የሆኑትን ብቻ ለይታችሁ ጻፉ።

ምሣሌ፡- መንጋ

መንጋ	ውሻ	ብርቱካን	ግመል	አራዊት	እህል
ላም	ዋንዛ	ጥሬ	እንጨት	ንስር	እንስሳ
ጠበቃ	ሰራዊት	ወንዝ	ወፍ		

አቀላጥፎ ማንበብ

“ህልም ሲፈታ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

2.2.4 አንብቦ መረዳት

አጋጣሚ ወይስ . . .?

ቅድመንባብ

በምስሉ ላይ ስለምታዩዋቸው ሰዎች የምታውቁትን ተናገሩ።

አጋጣሚ ወይስ . . .?





በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች የሚለያዩባቸው ጉዳዮች በርካታ የመሆናቸውን ያህል የሚያመሳስሏቸው ነገሮችም አያሌ ናቸው። ሰዎች በመልክ፣ አንድን ነገር በመፈለግ፣ በመውደድ፣ በመጥላት ወዘተ ሊመሳሰሉ ይችላሉ። በእነዚህ ነገሮች መመሳሰላቸው ግን አንድ ዓይነት ናቸው የሚያስብል እንዳልሆነ መረዳት ይገባል። ለዚህ ምሳሌ እንዲሆነን በሀገራችን ብርቅዬ ስለሆኑ ኹለት አትሌቶች አስገራሚ መመሳሰል እንመልከት።

ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴና የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት የኦሎምፒክ ሜዳሊያ ተሸላሚ፣ አትሌት ደራርቱ ቱሉ፣ የተወለዱት በ1966 ዓ.ም ነው። የትውልድ ቦታቸውም አርሲ ዞን ውስጥ ነው። ኹለቱ አትሌቶች በኦሎምፒክ መድረክና በተለያዩ ዓለማቀፋዊ ውድድሮች ሜዳሊያ ተሸላሚ ናቸው። ኃይሌም ሆነ ደራርቱ የኢትዮጵያ አትሌትክስ ፌዴሬሽንን መርተዋል። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ኹለቱም የአትሌቲክስ ፈርጦች ከፍተኛ መዋዕለንዋይ በማፍሰስ በልማት ተሠማርተው አገራቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ።

በዚህ ሁኔታ መመሳሰላቸው የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ወይስ ሌላ ምን ምክንያት ሊኖረው ይችላል? እያንዳንዳችን የየራሳችን ምክንያት ልንሰጥ እንችላለን።

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴንና አትሌት ደራርቱ ቱሉን የሚያመሳስሏቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ለ. በኹለቱ አትሌቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. ከምንባቡ ያስደነቃችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን? አድናቆታችሁን እንዴት ትገልጻላችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

መዋዕለንዋይ	ተሠማርተው	ፈርጦች
ሜዳሊያ	መርተዋል	በማፍሰስ

መጻፍ

የሠንጠረዡን ሐሳቦች በመጠቀም በማወዳደርና በማነጻጸር አንቀጽ ጻፉ።

አትሌት አበበ ቢቂላ	አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ
▪ ሰሜን ሸዋ ተወለደ ▪ በኦሎምፒክ ሜዳሊያ ተሸለመ ▪ የሪከርድ ባለቤት ▪ የኢትዮጵያን ስንደቅ በዓለም አደባባይ ከፍ ያደረገ ▪ በማራቶን ሩጫ ታዋቂ ▪ በሕይወት የሌለ	▪ አርሲ ዞን ተወለደች ▪ በኦሎምፒክ ሜዳሊያ ተሸለመች ▪ የሪከርድ ባለቤት ▪ የኢትዮጵያን ስንደቅ በዓለም አደባባይ ከፍ ያደረገች ▪ በመም ሩጫ ታዋቂ ▪ በሕይወት ያለች

2.2.5 ክለሳ

መጻፍ

ባለፈው ክፍለጊዜ ስለሸለቱ አትሌቶች የጻፋችሁትን አንቀጽ እንደገና አንብቡት። የሥርዓተነጥብ ወይም የፊደል ስህተት መኖር አለመኖሩን፣ ዓረፍተነገሮቹ በተገቢ የቃላት ቅደምተከተል መዋቀራቸውንና የሐሳብ ፍሰቱን ገምግሙ፤ በመቀጠል ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ቃላት

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉና ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፦ የኢትዮጵያ <u>አየርመንገድ</u> በዓለም ግንባርቀደም ከሆኑ አየርመንገዶች አንዱ ነው።

አየር	+	አደር	=	አየርመንገድ
ብረት	+	አጥ	=	
እንጀራ	+	ሰራሽ	=	
ወዝ	+	መንገድ	=	
ሥራ	+	ምጣድ	=	
ሰው	+	እናት	=	

አቀላጥፎ ማንበብ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት “አጋጣሚ ወይስ...?” የሚለውን ምንባብ አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

2.3.1 ማዳመጥ

ጤናማ አመጋገብ

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ርዕሱን በማስተዋል የምታዳምጡት ጽሑፍ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. ጤናማ አመጋገብ የሚባለው እንዴት ያለ ነው?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በወጉ የታቀደ አመጋገብ የሚባለው እንዴት ያለ ነው?

ለ. አትሌቲክስና አመጋገብ እንዴት የሚዛመዱ ይመስላችኋል?

ሐ. በየቀኑ መካከለኛ (የ30 ደቂቃ) እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አትሌቶች በመቶኛ ምን ያህል ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግብ መመገብ አለባቸው?

መ. ጤናማ አመጋገብ የማይመገብ ሰው ስኬታማ ስፖርተኛ መሆን የሚችል ይመስላችኋል? ለምን?

ሠ. አትሌት ለመሆን ብትፈልጉ ምን ዓይነት ምግቦችን የምታዘወትሩ ይመስላችኋል? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

አፈፃፀም	በወጉ	እንዲጠገን	ወሳኝ
ያሻሽላል	የተመጣጠነ	የእንስሳት ተዋጽኦ	

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. ሥዕሉን በማስተዋል ጽሑፉ ስለማን እንደተጻፈ ገምቱ።

ለ. በምስሉ ላይ ስለምትመለከቷት አትሌት የምታውቁትን ተናገሩ።

ስኬት



ጥሩነሽ ዲባባ፤ መስከረም 21 ቀን 1978 ዓ.ም ከአባቷ ከአቶ ዲባባ ቀነኒና ከእናቷ ከወይዘሮ ጉቱ ቶላ በአርሲ ቼፋ ወረዳ ተወለደች። ምንም እንኳ አክስቶቿ ደራርቱ ቱሉና በቀሉ ዲባባ፣ እንዲሁም ታላቅ እህቷ እጅጋየሁ ዲባባ ቀድመው ሩጫ ጀምረው ታላቅ ስም ያተረፉ ቢሆንም እሷ ግን የመሮጥ ፍላጎት አልነበራትም። ወደአክስቶቿ አዲስ አበባ ስትመጣም ዓላማዋ መማር እንጅ መሮጥ አልነበረም። ወደአዲስ አበባ በመጣችበት ጊዜ የትምህርት ምዝገባ ጊዜ አልፎ ስለነበር ወደ አርሲ ከመመለስ ይልቅ አክስቷ በቀሉ አባል በነበረችበት የማረሚያ ፖሊስ ስፖርት ክለብ በመመዝገብ የሩጫ ህይወቷን "ሀ" ብላ ጀመረች። እንዲህ ባጋጣሚ የተጀመረው የሩጫ ህይወቷ ለድርብርብ ድልና ዓለምአቀፍ ዝና ያበቃታል ብሎ የገመተ ሰው አልነበረም።

ጥሩነሽ ዲባባ የመጀመሪያ ዓለምአቀፍ ውድድሯን ያደረገችው በ2001 በዓለምአቀፍ አትሌቶች ውድድር ላይ ነው። ውድድሩን ስታካሂድ የ15 አመት ልጅ ነበረች። በዚህ ውድድር ዐምስተኛ በመሆን ጨርሳለች። በ2003 በተደረገው የአፍሮ ኤሽያ ውድድር ላይ በ 5ሺ ሜትር የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆናለች።

ጥሩነሽ ዲባባ በዓለምአቀፍ ውድድሮች ላይ አስደናቂ ውጤት ማምጣት የጀመረችው በ2003 ላይ ነው። በዚህ ዓመት በ 5ሺ ሜትር በተደረገ ውድድር ተስፈንጥራ በመውጣት ስፔናዊቷን ማርታ ዶሚኒጌዝንና ኬንያዊቷን ኤዲት ማሳይን ቀድማ በመግባት አሸነፈች። በወቅቱ ታዋቂ አትሌት ባለመሆኗ ውድድሩን ያስተላልፉ የነበሩ ጋዜጠኞች ውድድሩ ሊጠናቀቅ 100 ሜትር እስኪቀረው ድረስ አንድም ጊዜ ስሟን አልጠሩም ነበር። በ2008 የቤጂንግ ኦሎምፒክ ውድድር በ5 እና 10 ሺ የወርቅ ሜዳሊያ በማግኘት በዓለም የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት በመሆን ስሟን በታሪክ መዝገብ አስፍራለች። በዚህ ወቅትም የዓመቱን ዓለምአቀፍ የታላቅ

አትሌት ሽልማት አግኝታለች። ከላይ የቀረቡት ስኬቶቿ ዋናዋናዎቹ እንጂ ሌሎች በርካታ ድሎችን ያስመዘገበች ድንቅ አትሌት ናት።

አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ለማረሚያ ፖሊስ ስፖርት ክለብና ለሃገሯ ባደረገችው አስተዋጽኦ የሌተናል ኮሎኔልነት ማእረግ ተሰጥቷታል። አዲስ አበባ ውስጥም በስሟ ሆስፒታል ተሰይሞላታል። በግል ሕይወቷም የተሳካላት ይህች አትሌት፣ ከአትሌት ስለሺ ስህን ጋር ትዳር መስርታ ዐይኗን በዐይኗ ለማየት በቅታለች።

[ምንጭ:- ድሬ ቲዩብ ድረገጽ። (የካቲት 4/2014)]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በቅድመንባብ የሰጣችሁት ግምት ትክክል ሆኖ አገኛችሁት? እንዴት አረጋገጣችሁ?

ለ. ጸሐፊው ስለአትሌቷ ምን ዓይነት ስሜት አለው? እንዴት አወቃችሁ?

ሐ. “ጥሩነሽ ዲባባ ዝነኛ አትሌት መሆን የልጅነት ምኞቷ ነበር።” ባነበባችሁት መሠረት ይህ ሐሳብ ትክክል ይመስላችኋል? ለምን?

መ. ጽሑፉ ምን ስሜት ፈጠረባችሁ? ለምን?

ሠ. ስለአትሌቷ የምታውቋቸውን ሌሎች ድሎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ቃላት

በ”ሀ” ክፍል ላሉት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ከ”ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ታላቅ ስም	ሀ. ምንምጊዜ
2. አንድም ጊዜ	ለ. አፈትልካ
3. ተስፈንጥራ	ሐ. የክብር መጠሪያ
4. ድርብርብ	መ. ብዙ
5. ማዕረግ	ሠ. ዝና
	ረ. ታዋቂ
	ሰ. ነጠላ

መጻፍ

የሚከተሉትን ጅምር ዓረፍተነገሮች አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. _____ ለጤንነት ጠቃሚ ነው።

ለ. ፈተና ስለደረሰ _____።

ሐ. በትምህርትቤታችን በተደረገው የሩጫ ውድድር _____።

መ. እኔና ጓደኞቼ _____።

ሠ. ነገ ረፍት ስለሆነ _____።

2.3.3 ማዳመጥ

ጤናማ አመጋገብ

ቅድመማዳመጥ

“ጤናማ አመጋገብ” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።
   ሀ. በየቀኑ ከ60 ደቂቃ እስከ90 ደቂቃ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አትሌቶች በመቶኛ ምን ያህል ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግብ መመገብ አለባቸው?
   ለ. ለአንድ አትሌት ወሳኝ የሆኑ ምግቦች ምን ምን ናቸው?
   ሐ. ጥሩ አመጋገብ የሚያስፈልገው ለአትሌቶች ብቻ ነው? ለምን?
2. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟሉና በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ።



ቃላት

በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት አዲስ ቃል መሥርቱ።

ምሣሌ፡- ሸቀጥ → ሸቀጣሸቀጥ

ሀ. ቅመም

ለ. ትል

ሐ. ጥቅም

መ. ቅርጽ

ሠ. ቁስ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ስኬት” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

2.3.4 አንብቦ መረዳት

ክብር ለሚገባው ክብር እንስጥ

ቅድመንባብ

ስለዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ ታውቃላችሁ? በምን ይታወቃሉ?

ክብር ለሚገባው ክብር እንስጥ

ክብር ለሚገባው ክብር መስጠትን ባህል ልናደርግ ይገባል። በተለያዩ የሙያ መስኮች ለአገራቸው መስዋእትነት የከፈሉ እንቁ ዜጎችን ታሪክ ከትቦ ለቀሪው ትውልድ ማስቀመጥም አንዱ ክብር የመስጠት ተግባር ነው። ከዚህ ታሪክ ወጣቶች ብዙ ቁም ነገሮችን፣ ጽናትን፣ ለወገን ራስን መስዋእት ማድረግን ወዘተ ይማራሉ፤ እነሱም ለላቀ አስተዋጽኦ ይነሳሳሉ። የትውልድ ቅብብሎሽ የሚኖረውና የተሻለ እድገት የሚመዘገበው ይህ ሲሆን ነው። ታሪካቸው ሊመዘገብ፣ ሊታወቅና ልንማርበት ከሚገባቸው እውቅ ኢትዮጵያውያን መካከል የአትሌቲክስ አርበኛ የሆኑት ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ አንዱ ናቸው።

ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ ጥር 21 ቀን 1939 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ፣ ተጉለትና ቡልጋ ልዩ ስሙ ወመንፈስ በተባለ ቀበሌ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቤተክህነት ተማሪ ቤት ገቡ። ከዚያም ወደአዲስ አበባ በመሄድ በአስፋወሰንና ደጃች ወንድይራድ ትምህርትቤቶች ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። በእነዚህ

ትምህርትቤቶች ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት የተለያዩ ርቀቶች ባሏቸው የሩጫ ውድድሮች ላይ ይካፈሉ ነበር።

የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የአንድ ዓመት የመምህርነት ስልጠና ወስደው በጤናና ሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት መምህርነት አገልግለዋል። በ1956 ዓ.ም በሃንጋሪ የውጭ ትምህርት ተከታትለዋል። በዚህ ጊዜም በሩጫ ውድድሮች ተሳትፏቸው የላቀ ነበር። ከውጭ ሀገር ተመልሰውም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አስተምረዋል።

በ1966 ዓ.ም ዳግም ወደሀንጋሪ በመመለስ ቀጣይ ትምህርታቸውን ተከታትለው የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ወደአገራቸው ተመልሰውም በስፖርት ኮሚሽን ውስጥ ሰርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ርቀት ሩጫዎች በአሰልጣኝነት በመሳተፍ ዓለምአቀፍ አትሌቶችን አፍርተዋል። ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን በአትላንታና በባርሴሎና ኦሎምፒኮች ባስመዘገቡት ድል ውጤታማ አሰልጣኝነታቸውን አስመስክረዋል።

እኒህ ታላቅ ሰው በሚያዝያ 2008 ዓ.ም ከዚህ ዓለም የተለዩ ቢሆንም ያሳረፉት አሻራ ዛሬም ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ እንድትጠራ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን መረዳት አያዳግትም። “ጥሩ ስም ከመቃብር በላይ ነው“ የሚባለውም ለዚህ ነው።

[ምንጭ:- ኦሎምፒክና ኢትዮጵያ። (1993)። ገጽ 27-28፤ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ የተወለዱበት ቦታ ልዩ ስሙ ማን ይባላል?

ለ. የአትሌቲክስ ተሳትፏቸውን የጀመሩት መቼ ነበር?

ሐ. ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ ውጤታማ አሠልጣኝነታቸውን ያስመሰከሩበት አጋጣሚ ምንድን ነው?

መ. ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬን ወደአትሌቲክስ አሠልጣኝነት የገፋቸው ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

ሠ. በተለያዩ የሙያ መስኮች ለሀገራቸው መስዋዕትነት የከፈሉ ዜጎችን ታሪክ መዝግቦ ለትውልድ ማስተላለፉ ምን ጠቀሜታ አለው?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተመሳሳይ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱና በትክክለኛው ቃል ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

"ሀ"	"ለ"
1. ተከታትለዋል	ሀ. ይሳተፍ
2. የላቀ	ለ. ተምረዋል
3. ይካፈል	ሐ. የጨረሱበት
4. አፍርቷል	መ. ከፍተኛ
5. ያጠናቀቁበት	ሠ. አስገኝቷል

ሀ. አንዷለም በልጅነቱ በትምህርትቤቶች የሩጫ ውድድር _____ ነበር።

ለ. የኢትዮጵያ አትሌቶች ከአንደኛ እስከሦስተኛ ደረጃ ይዘው _____ የማራቶን ውደድር የሚረሳ አይደለም።

ሐ. የኢትዮጵያ የፖሊስ አትሌቲክስ ቡድን ለሀገራችን በርካታ ስኬታማ አትሌቶችን _____።

መ. ወርቂቱ በትምህርቷ ላስመዘገበችው _____ ውጤት ተሸለመች።

መጻፍ

የሚከተለውን መረጃ በመጠቀም ስለአትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ አጭር አንቀጽ ጻፉ።

ይቻላል!

የአትሌት ስም፡- ሻለቃ ኃይሌ ገብረሥላሴ

የአባት ስም፡- አቶ ገብረሥላሴ በቀለ

የእናት ስም፡- ወይዘሮ አየለች ገብሩ

የትውልድ ዘመን፡- 1966 ዓ.ም

የትውልድ ቦታ፡- አርሲ ዞን፣ ጭላሎ፣ ጥዬ ወረዳ

አብይ የሕይወት መርህ፡- ይቻላል!

ድሎች፡- በ2ሺ፣ 5ሺ እና 10ሺ ሜትር ውድድሮች የሪከርዶች ባለቤትና ሜዳሊያ ተሸላሚ

በአሁኑ ጊዜ ያላቸው ተግባር፡- ከፍተኛ መዋዕለንዋይ በማፍሰስ በልማት የተሠማሩ

[ምንጭ፡- ኦሎምፒክና ኢትዮጵያ። (1993)]

2.3.5 ክለሳ

መጻፍ

1. ባለፈው ክፍለጊዜ ስለአትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ የጻፋችሁትን አንቀጽ እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ።
2. የሚከተሉትን ሐረጎች በአጎጽሮተቃል ጻፉ።

   ምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ = ኢ.ሕ.ፌ.ዴ.ሪ

   ሀ. የአማራ ልማት ማኅበር

   ለ. የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት

ሐ. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን

መ. የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም

ሠ. የአማራ ብዙኀን መገናኛ ድርጅት

3. በፊደል የተጻፉትን ብርና ሳንቲምች በአሀዝ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሰባ ኹለት ብር ከአሥራ ዐምስት ሳንቲም = ብር 72.15

ሀ. አሥራ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም

ለ. ስድሳ አንድ ብር ከሰማንያ ሳንቲም

ሐ. ዘጠኝ መቶ ሦስት ብር ከዐምስት ሳንቲም

መ. አንድ መቶ አራት ብር ከአንድ ሳንቲም

ሰዋስው

ከሚከተሉት ቃላት የጥቅል ስም የሆኑትን መርጣችሁ ጻፉ።

ዶሮ	ሕዝብ	በቅሎ	ከተማ
እጽዋት	ወይራ	አዝመራ	ደን

አቀላጥፎ ማንበብ

“ክብር ለሚገባው ክብር እንስጥ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 3 ቃላዊ ግጥሞች

3.1.1 ማዳመጥ — ቃላዊ ግጥሞች

ቅድመማዳመጥ

ሀ. በሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ፍቺ ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

ቃላዊ ግጥም	ምጣኔ	ጣውንት
ሙሾ	ሞት	ቅርስ

ለ. የበዓል ወይም የሠርግ ወይም የእርሻ ወይም የውቂያ ጊዜ ቃላዊ ግጥም ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. የሰው ልጅ ቃላዊ ግጥሞችን መጠቀም የጀመረው መቼ ነው?

ለ. የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ቃላዊ ግጥሞች ቃላዊ የሚባሉት ለምንድን ነው?

መ. ቃላዊ ግጥሞች ለታሪክ ጥናት የመረጃ ምንጭ የሚሆኑት እንዴት ነው?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተቃራኒ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ቁምነገር	ሀ. አሞገሰ
2. በጎ	ለ. ጽሑፋዊ
3. ገሰፀ	ሐ. መልካም
4. ቃላዊ	መ. ቀልድ
5. ሙሾ	ሠ. መጥፎ
	ረ. ለመነ
	ሰ. ዘፈን

3.1.2 አንብቦ መረዳት

ደመላሽ

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ።

ሀ. ርዕሱንና ሥዕሉን በማስተዋል ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. ደመላሽ፤ የሚለው ቃል ፍቺ ምን ይመስላችኋል?

ደመላሽ



ጠላት የሀገራችንን ድንበር ጥሶ በመግባት ወገኖቻችንን መጨፍጨፍ በጀመረበት አንድ ወቅት በአንድ ጠጅ ቤት ውስጥ የተሰበሰቡ ሰዎች ይህንን የጠላት ግፍ በተመለከተ ግጥሞችን ለአዝማሪ እያቀበሉ ብሶታቸውን ይተነፍሳሉ። ከመካከላቸው አንዱ እንዲህ የሚል ግጥም ለአዝማሪው አቀበለ፦

ያስጨንቅ የለም ወይ ከሁሉ ከሁሉ፤

ስምስ አይከብድም ወይ ደመላሽ መባሉ።

አዝማሪው ከማሲንቆው አዋህዶ ይህንን ግጥም እየደጋገመ በዜማ ሲያንቆረቁረው ጠጪዎቹ ወደአቶ ደመላሽ በትዝብት ዓይን እየተመለከቱ “ትክክል ነው” በሚል ስሜት አንገታቸውን ነቀነቁ። በዚህ ጊዜ አቶ ደመላሽ ደምሥራቸው ተገታተረ። ላባቸው ቁ...ር...ር እያለ በግንባራቸው ወረደ። የያዙትን ጠጅ የሞላ ብርሌ ቁጭ አድርገው ጠጪዎቹን ገላምጠው በፍጥነት ወጡ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አዝማሪው፣

“ያስጨንቅ የለም ወይ ከሁሉ ከሁሉ፣

ስምስ አይከብድም ወይ ደመላሽ መባሉ።” ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. አዝማሪው ግጥሙን እየደጋገመ ሲያዜም የአቶ ደመላሽ ስሜት ምን ይመስል ነበር? እንዴት አወቃችሁ?

ሐ. የአቶ ደመላሽ ስሜት የተለዋወጠው ለምን ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

መ. አቶ ደመላሽ ከጠጅቤቱ ከወጡ በኋላ ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ማሲንቆ	ገላምጠው	ተገታተረ
ሲያንቆረቁረው	አዋህዶ	

መጻፍ

ግጥሞቹን አስተካክላችሁ እንደገና ጻፏቸው።

ሀ. ዲቡን አፍርሶ መዝራት ነው እንጂ፣

መስረቅ ምንድን ነው ጨለማ ለብሶ።

ለ. ያልተቆላ ሱፍ ጥርስሽ የሚመስለው፣

የሚያንሰፈስፍ ሰጠሽኝ በሽታ።

ሐ. እናቱ ብር ሆና እኔ ልበደራት፣

ዘላለም ላኑራት አራጣ እየከፈልኩ።

መ. ማር ቅቤ ወተት የሚበላው ጮማ፣

አገሬ ኢትዮጵያ ምድራዊ ገነት።

ሠ. የወደዱት ባይሞት ያመኑት ባይከዳ፣

ይሆን ነበር ሜዳ የዓባይ ቁልቁለቱ።

3.1.3 ማዳመጥ

ቃላዊ ግጥሞች

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ቃላዊ ግጥሞች” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ቃላዊ ግጥሞች ምን ምን ጠቀሜታዎች አሏቸው?

ለ. ቃላዊ ግጥሞች በጎውን የሚያበረታቱትና አጥፊውን የሚገስፁት እንዴት ነው?

ሐ. “ቃላዊ ግጥሞች ሊጠበቁ የሚገባቸው ቅርሶች ናቸው።” የተባለው በምን ምክንያት ነው?

መ. የምታውቋቸውን የአውደዓመት፣ የሥራ ወይም የፍቅር ግጥሞች ተናገሩ።

ቃላት

1. በ“ሀ” ክፍል ላሉት ተመሳሳይ ከ”ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. በእንጉርጉሮ	ሀ. ባገኙት ወይም በሠሩት ነገር መደሰት
2. አጥፊዎች	ለ. ተጽዕኖ
3. እርካታ	ሐ. መገኛ
4. ምንጭ	መ. ግጥሞችን በዜማ ማለት
5. አሻራ	ሠ. መጥፎ ነገር የሚፈፅሙ
	ረ. ቡረቃ

2. ከላይ በ“ሀ” ክፍል ካሉት ቃላት/ሐረግ መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. ተስፋዬ በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈፀመው የበጎ አድራጎት ተግባር _____ ተሰማው።

ለ. በዓሉ ግርማ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ላይ ጉልህ _____ ያሳረፈ ታላቅ ደራሲ ነው።

ሐ. ዉኃ ከመጠጥ ባለፈ የኃይል _____ በመሆን ያገለግላል።

መ. ትሁኔ ሲከፋት ብሶቷን _____ መግለጽ ይቀናታል።

ሠ. _____ በጊዜ ካልታረሙ ለማኅበረሰቡም ሆነ ለሀገር ሸክም ይሆናሉ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ደመላሽ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ዘር

ቅድመንባብ

ርዕሱንና ሥዕሉን በማስተዋል ግጥሙ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ዘር



ዝናቡ መጣ እም እም እያለ፣
ቆላ ደጋውን በለው እያለ፣
ይደሰት ጀመር ዘርቶ የዋለ።
አማረ ሰኔ አማረ ግንቦት፣
ያለው ሲዘራ የሌለው ሲሞት።
ጠንክሬ ሠርቼ እዘራለሁ ገብስ፣
ለምጃለሁና በሰፊው መጉረስ።
መዝራት ነው እንጂ ከጎታ ዝቆ፣
ምንድን ነው ብድር ኬሻ ወሽቆ።

[ምንጭ:- ሞላ ደመቀ። (2005)። *የግብርና ግጥማዊ ሥነቃል*፣ ገጽ 85፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።
   ሀ. አርሶአደር የሚደሰተው ምን ሲሆን ነው?
   ለ. “ያለው ሲዘራ የሌለው ሲሞት”፤ ማለት ምን ማለት ነው?
   ሐ. ከግጥሙ ውስጥ ሰነፍ አርሶአደርን የሚነቅፉ ስንኞችን ለይታችሁ ጻፉ።
   መ. የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?
2. የተሰመረባቸውን ሐረጋት በተመሳሳይ ሐረግ በመተካት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።
   ሀ. ዝናቡ መጣ <u>እም እም እያለ</u>፣
   ለ. ያለው ሲዘራ <u>የሌለው ሲሞት</u>፣
   ሐ. ለምጃለሁና <u>በሰፊው መጉረስ</u>፣
   መ. መዝራት ነው እንጂ <u>ከጎታ ዝቆ</u>፣

ቃላት

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።

	አውዳዊ ፍቺ	ተቃራኒ
ሀ. ዝቆ		
ለ. ወሸቆ		
ሐ. ቆላ		
መ. አማረ		
ሠ. በሰፊው		

መጻፍ

የሚከተሉትን ጅምር ግጥሞች አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. አፈር ምሼ ምሼ አወጣሁ መግላሊት

_____።

ለ. የቦርከና ዉኃ የተንጋለልከው፣

_____።

ሐ. እምዬ አትቅደሚ ልቅደምልሽ እኔ፣

_____።

መ. ከሀገር ሆድ ይሰፋል ላስቻለው ሰውማ፣

_____።

ሠ. ከደጅ ሲያባርረኝ ዘመዴ ወዳጄ፣

_____።

ረ. አንቺና እኔ ሆነን ያረምነው አረም፣

_____።

ሰ. እንግዲህ ነዶኛል ተው አትናገሩኝ፣

_____።

3.1.5 ክለሳ

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ተስማሚ የሆኑት ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

ሀ	ለ
የቃላዊ ግጥሙ ዓይነት	ቃላዊ ግጥም
1. የሠርግ	ሀ. በእርፍ ቢወቁ በሽመል ቢወቁ፣ በርዬ ካልገባ አይሰበር ምርቁ።
2. የእርሻ	ለ. በሣር በቅጠሉ ተጽፏል ስምህ፣ ልቤ ደነገጠ አንተን ሲጠሩህ።
3. የሙሾ	ሐ. አልቤኑን አጉርሰው እስከላንቃው ድረስ፣ ቁጭ ብሎ አይገኝም አፍን ከፍቶ መጉረስ።
4. የውቂያ	መ. ኧረ ሚዜው ሚዜው አሁን አምሮብሀል፣ ነፋስ ያዋከበው ባህርዛፍ መስለሃል።
5. የፍቅር	ሠ. በሰኔ በግንቦት እርፍ የነቀነቀ፣ ወፍጮው እንዳንራ መስከረም ዘለቀ።
6. የአጨዳ	ረ. ከመንገዱ አጠገብ ሰፊ አዳራሽ ሰርቶ፣ ጣል አድርጎት ሄደ እንግዳውን ፈርቶ።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡- አዋሃዱ → ለዩ

አርሶአደሮቹ ገለባውን ከምርቱ በማራገቢያ ለዩ።

ደጋ	ቁምነገር	በጎ	አዋሃዱ
ሰፊ	ገሰፀ	ነቀነቀ	

አቀላጥፎ ማንበብ

“ዘር” በሚለው ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

3.2.1 መጻፍ

ሀ. በምሳሌው መሠረት ጻፉ።

ምሣሌ፡- ፍርድ ቤት → ፍ/ቤት

ሀ. ፍርድ ቤት　　መ. ማተሚያ ቤት

ለ. ትምህርት ሚኒስቴር　　ሠ. ጠቅላይ አቃቤ ሕግ

ሐ. ጠቅላይ ሚኒስቴር

ለ በሚከተለው ጽሑፍ የተሰመረባቸውን እዝባር በመጠቀም በአጎጽሮተቃል ጻፉ።

ሆጤ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት　　ቁጥር ሆ/አ/2ኛ/ደ/ት/ቤት/305/2095/13

ደሴ　　ቀን 15/11/13 ዓ.ም

ጉዳዩ፡- በሳይንስ ትምህርትና ፈጠራ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ስለመመልመል

ለመምህር ጥበቡ አጎናፍር፣ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በቀረበለት ጥያቄ መሠረት በሳይንስ ትምህርትና ፈጠራ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተማሪዎችን መልምለን እንድንልክ አሳውቋል። በመሆኑም ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመጡትን ኢንጅነር ታደለ ወርቅነህን ከፈጠራና ሳይንስ ትምህርት ክበብ አባላት ጋር እንዲያገናኟቸው ስል አሳስባለሁ።

ከሰላምታ ጋር!

ፊርማ

አቶ ሰለሞን ደመላሽ

ርዕሰ መምህር

3.2.2 አንብቦ መረዳት

ከአፍ የወጣ አፋፍ

ቅድመንባብ

ሀ. ርዕሱን በማንበብ ታሪኩ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. ለሚከተለው ሐረግ/ቃል ፍቺ ስጡ።

- ከአፍ የወጣ አፋፍ
- ጣውንት

ከአፍ የወጣ አፋፍ

“የሐምሌ ዳመና እያጉረመረመ፣

ከምወደው ጓደ ለይቶኝ ከረመ ይላል ያገሬ ሰው” አሉ ወይዘሮ አንችናሉ።

“አሄሄ!... አሄ!”... በረጅሙ ተነፈሱ። ከአፍ የወጣ አፋፍ ሆኖባቸው እንጂ ያደረጉት ነገር ሳይቆጫቸው አልቀረም። ለባለቤታቸው ያላቸው ንቀት ለከት ያጣ ነው። አይናቸውን ሞልተው አያይዋቸውም፤ ይገላምጧቸዋል። በዚህ ምክንያት በነጋ በጠባ ጭቅጭቅ ነው። ባለቤታቸው ውለው ሲመጡ ከምግብ በፊት የሚያቀርቡላቸው ነገር ነው። በርግጥ ባለቤታቸው ያልተገባ ሥራ በመሥራት ጥፋት አጥፍተዋል። ነገርግን በድርጊታቸው ተጸጽተው “ይቅርታ አድርጊልኝ” ብለው እግራቸው ሥር ተደፍተው ለምነዋቸው ነበር። ይህንን ወዳጅ ዘመድ ያውቃል፤ ሽማግሌም ታዝቧል።

ወይዘሮ አንችናሉ በዘመድ አዝማድና በሽማግሌ ቢለመኑ ይቅርታ ማድረግ መሸነፍ መሰላቸው። ግትርነታቸውና ነገራቸው እየባሰ ሄደ። ይህንን መቋቋም ያቃታቸው ባለቤታቸው ከቤት ወጥተው ኮበለሉ። ላዩ ዉኃ፣ ታቹ ዉኃ በሆነበት የሃምሌ ምድር ባለቤታቸው ከቤት ወጥተው ጣውንታቸው ቤት ገቡ። ከዚያ በኋላ ወይዘሮ አንችናሉን ቅናት ያንገበግባቸው ጀመር። ጣውንታቸውን በጥርሳቸው ቢነክሷቸው ይወዱ ነበር። ከጣውንታቸው ጋር መንገድ ላይ ሲገናኙ ሁልጊዜም በነገር ይጎነታተላሉ። ጣውንቷም የዋዛ አይደለችም መልሳ ታቀምሳቸዋለች። እንዲህ እየተባባሉ፡-

ጣውንት፤ ፊቷን አትታጠብ መስታወት አታይ፣
ያላትን ቢቀሟት ኃጢኣት አለው ወይ?

ወይዘሮ አንቺናሉ፤ ፊቴን ባልታጠብ መስታወት ባላይ፣
የኔ የሆነውን ልትቀሚኝ ነው ወይ።

ጣውንት፤ አፍንጫሽ ቢገተር እንደመግላሊት፣
በደም እንበልጣለን እነጎራዲት።

ወይዘሮ አንቺናሉ፤ መቼም ማከፋፋት ስም ማጥፋት ሥራሽ ነው፣
ያንችማ ሴትነት ማማት ማጥላላት ነው።

ሁልጊዜም ሲገናኙ የሚያደርጉትን አላስፈላጊ መበሻሸቅ የተመለከተው የአካባቢው ነዋሪም ነገሩን በዝምታ አላላፈውም። ይህንን ጥሩ መልእክት የማያስተላልፍ፣ አስተማሪ ያልሆነና ጥቅምአልባ መዘላለፍ እንዲያቆሙና ያለባቸውን ችግር በቆየው ባህላዊ ሥርዓት መፍታት እንዳለባቸው እያሳሰባቸው ነው። ለዚህም ይመስላል ወይዘሮ አንቺናሉ ሰሞኑን ልመናቸውን ወደገፉትና ምክራችሁን አልቀበልም ወዳሏቸው ሽማግሌዎች ቤት እግር አብዝተዋል።

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ወይዘሮ አንቺናሉን ያስቆጫቸው ነገር ምን ነበር?

ለ. "አፍንጫሽ ቢገተር እንደመግላሊት፣
በደም እንበልጣለን እነጎራዲት።" ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. የወይዘሮ አንቺናሉ ጣውንት፤
"ፊቷን አትታጠብ መስታወት አታይ፣
ያላትን ቢቀሟት ኃጢኣት አለው ወይ?" ባሉት ሐሳብ (አባባል) ትስማማላችሁ? ለምን?

መ. ወይዘሮ አንቺናሉ ወደሽማግሌዎቹ ቤት እግር ያበዙት ለምን ይመስላችኋል?

ቃላት

የተሰመረባቸውን ቃላት/ሐረጋት በሌሎች በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. ብሩክ የዓመት ረፍት ስለተሰጠው ከናፈቁት ቤተሰቦቹ *ጋር* <u>ከረመ</u>።

ለ. ይልማ ባልረባ ምክንያት ከሚስቱ *ጋር* መለያየቱ <u>ቆጭቶታል</u>።

ሐ. ሰማዩ ደመና ቋጥሮ <u>ሲያጉረመርም</u> ፍጥረታት ሁሉ ወደጎጇቸው ለመከተት ተሯሯጡ።

መ. “አይ ፈጣሪ! ምን ኃጢአት ብሠራ ነው እንዲህ መከራዬን ያበዛኸው?” በማለት አማረረች - ጀሚላ።

ሠ. የበላይነሽ ሠርግ ላይ ከተጣሉ ወዲህ ዘርትሁን አረጋሽን በበሯ ባለፈች ባገደመች ቁጥር በነገር ትጎነትላት ይላለች።

ረ. ሰሞኑን ልትጠይቃቸው የመጣችው ዘመዳቸው ላይ ቀልቡ ስላረፈ ባንታለም ከነእርቅይሁን ቤት እግር አብዝቷል።

1. በፊደል የተገለጹትን ቀናት፣ ወራትና ዓመተምህረቶች እዝባርን በመጠቀም በአሀዝ ጻፉ።

   ምሣሌ፡- ሐምሌ አስር፣ ኹለት ሺህ አሥራ ሦስት ዓመተምህረት

   → 10/11/2013 ዓ.ም

   ሀ. መስከረም ኹለት፣ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ዓመተምህረት

   ለ. ታህሣስ አሥራ ስድስት፣ ኹለት ሺህ አስር ዓመተምህረት

   ሐ. ጥቅምት ሀያ ስምንት፣ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስድስት ዓመተምህረት

2. መረጃዎቹን በምሣሌው መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ።

   ምሣሌ፡- የመሥሪያቤቱ ስም = ደቡብ ወሎ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ

   = ደወዞባቱ

   የሚጻፈው ጉዳይ = ሪፖርቶች = 101

   የደብዳቤ መዝገብ ቁጥር = 3055

   ደብዳቤው የተጻፈበት እለት = ሐምሌ 01/2013 ዓ.ም

   ቁጥር ደወዞባቱ 101/3055/13

   ቀን 01/11/13 ዓ.ም

ሀ. የመስሪያቤቱ ስም፡- ምዕራብ ጎጃም ዞን ትምህርት መምሪያ = ምጎዞትመ

   የሚጻፈው ጉዳይ፡- ግብረመልስ = 102

   የደብዳቤ መዝገብ ቁጥር፡- 2032

   ደብዳቤው የተጻፈበት እለት፡- ጥር 25፣ 2010 ዓ.ም

   ቁጥር _____

   ቀን _____

ለ. የተቋሙ ስም፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ = አአዩ

የሚጻፈው ጉዳይ፡- ጥናቶች = 209

የደብዳቤ መዝገብ ቁጥር፡- 143

ደብዳቤው የተጻፈበት ዕለት፡- ሰኔ 15፣ 2011 ዓ.ም

ቁጥር _____

ቀን _____

ሐ. የመስሪያቤቱ ስም፡- ሰሜን ጎንደር ዞን ሴቶችና ሕፃናት = ሰጎሴህ

የሚጻፈው ጉዳይ፡- ደብዳቤዎች = 203

የደብዳቤ መዝገብ ቁጥር፡- 1073

ደብዳቤው የተጻፈበት እለት፡- የካቲት 20፣ 2012 ዓ.ም

ቁጥር _____

ቀን _____

3.2.3 ሰዋስው

1. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ተውሳከግሶችን ለይታችሁ ጻፉ።

ምሣሌ፡- ከበደ <u>ዘንድሮ</u> አገባ።

ሀ. አያቴ ስለሞተች እጅግ አዘንኩ።

ለ. ነጎድጓዱ ድንገት ሲያንባርቅ ክፉኛ ደነገጠ።

ሐ. ሳንካ ስለገጠመው ትዳሩ እያሰበ ብዙ ጠጣ።

መ. ፋጡማ ቶሎ መጣች።

ሠ. ተመስገን ከአሜሪካ ትናንት መጣ።

2. በ“ሀ” ክፍል ላሉት ተስማሚ የሆኑትን ከ”ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ። (ከአንድ ጊዜ በላይ ማዛመድ ይቻላል።)

“ሀ”	“ለ”
1. ቅድም	ሀ. የመጠን
2. በጣም	ለ. የጊዜ
3. ክፉኛ	ሐ. የቦታ
4. ጥቂት	መ. የሁኔታ
5. ጧት	
6. እዚህ	
7. ምንኛ	

አቀላጥፎ ማንበብ

“ከአፍ የወጣ አፋፍ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

3.2.4 አንብቦ መረዳት

አካባቢያችን

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. የቃላዊ ግጥም ዓይነቶችን ተናገሩ።

ለ. በአካባቢያችሁ ከሚነገሩ ቃላዊ ግጥሞች የምታውቋቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

አካባቢያችን

ኢትዮጵያ የበርካታ ቃላዊ ግጥሞች ባለቤት ናት። የአማራ ሕዝብም እንደሌላው የሀገሪቱ ማኅበረሰብ ስሜቱንና ሐሣቡን የሚገልጽባቸው ልዩ ልዩ በቃል የሚቀርቡ ግጥሞች አሉት። በየአካባቢያችንም እንዲሁ በተለያዩ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና

ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ጎብረተሰቡ ሐሳቡን የሚገልጽባቸው የሚከተሉትን የመሰሉ የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞች አሉ።

የወፍጮ ቃላዊ ግጥሞች

ወፍጮው ውረድ ውረድ ቋቱን ሙላ ሙላ፣
እንዲሁ አይገኝም የሰው ቤት እንጀራ።
ስጋግር አዝዬ ስፈጭም አዝዬ፣
አንቀልባው ተፈታ ና ውረድ ማሙየ።

የሀገር ፍቅር ቃላዊ ግጥሞች

ሀገሬን ሀገሬን አይልም ወይ ሰው፣
ክፉ ሲናገሩት ሆድ እየባሰው።
አንተ የሀገሬ ዉኃ አረንጓዴ አትልበስ፣
እጠጣህ ይሆናል ካገሬ ስመለስ።
ከሀገሩ የወጣ ሀገሩ እስኪመለስ፣
ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ።

የክብት እገዳ (ጥበቃ) ቃላዊ ግጥሞች

ነይ ዙሪ መግላሊት ተመለሽ አለላ፣
ቆላ መውረዴ ነው በሮቹን ላበላ።
ዝናብ እንዳይመታኝ ገሳ ለብሻለሁ፣
ፀሐይ እንዳይመታኝ ጥላ ዘርግቻለሁ፣
ባገልግል ቋጥሬ ምሳዬን ይዣለሁ፣
በጡሊዬ ደግሞ ዉኃ ቀድቻለሁ፣
ሥራዬን በጊዜ አጠቃልያለሁ።

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከሀገር ፍቅር ቃላዊ ግጥሞች መካከል የመጀመሪያዎቹ ኹለት መስመሮች መልዕክት ምንድን ነው?

ለ. "ወፍጮው ውረድ ውረድ ቋቱን ሙላ ሙላ፣

እንዲሁ አይገኝም የሰው ቤት እንጀራ።" ሲባል ምን ማለት ነው?

ይህን ቃላዊ ግጥም የተናገረችው ምን ዓይነት ሴት ትመስላችኋለች? እንዴት አወቃችሁ?

ሐ. "ሀገሬን ሀገሬን አይልም ወይ ሰው፣

ክፉ ሲናገሩት ሆድ እየባሰው።" በሚል የገጠመው ሰው በምን ዓይነት ስሜት ውስጥ ያለ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

መ. የምታውቁትን የሀገር ፍቅር ቃላዊ ግጥም ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ቃላት

መምህራችሁ ሰሌዳ ላይ ቃላት ይጽፉላችኋል። ቡድናችሁን ወክለው ፊት ለፊት ለሚቀመጡት የቡድን ጓደኞቻችሁ የቃላቱን ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ በመናገር፣ በወረቀት ላይ በመሳል ወይም በድርጊት በማሳየት ቃሉን እንዲገምቱ አድርጉ።

መጻፍ

1. የሚከተሉትን ቃላዊ ግጥሞች መልዕክት በአጭሩ ጻፉ።

   ሀ. እርሻ ያላረሰ እርፍ ያልነቀነቀ፣

   የሐምሌ መባቻ ተጣጥፎ ወደቀ።

   ለ. መከራ ሲመጣ አይነግርም አዋጅ፣

   ሲገሰግስ አድሮ ቀን ይጥላል እንጅ።

   ሐ. የዓባይ ጥቁር እንጨት ባሕር ያጠለቀው፣

   መች እተዋወቅ ነበር መለየቴን ባውቀው።

2. ከሚከተሉት በአንዱ ቃላዊ ግጥሞች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሀ. የሠርግ ቃላዊ ግጥም

ለ. የአውደዓመት ቃላዊ ግጥም

ሐ. የእርሻ ቃላዊ ግጥም

3.2.5 ክለሳ

መጻፍ

የትምህርትቤታችሁ የሚኒሚዲያ አስተባባሪ እንደሆናችሁ አስቡና መነሻ ሀሳቡን በመጠቀም ለትምህርትቤታችሁ ርዕሰመምህር አስፈላጊ ቁሳቁሶች እንዲገዙ የሚጠይቅ ደብዳቤ ጻፉ።

በደብዳቤው ራስጌ በስተግራ በኩል የሚጻፉ፡-

- የትምህርትቤቱ ስም
- የሚኒሚዲያ ክበቡ ስም
- የከተማው ስም

በደብዳቤው ራስጌ በስተቀኝ በኩል የሚጻፉ፡-

- የመስሪያቤቱ ስም፡- የ_____1ኛ ደረጃ ትምህርትቤት ሚኒሚዲያ ክበብ (በእዝባር አሳጥሮ መጻፍ)
- የሚጻፈው ጉዳይ፡- ደብዳቤዎች = 112
- የደብዳቤ መዝገብ ቁጥር፡- 315
- ደብዳቤው የተጻፈበት ቀን፡- _____

ጉዳዩ፡- <u>ለሚኒሚዲያ ክበብ ቁሳቁሶች እንዲገዙ ስለመጠየቅ</u>

ሰዋስው

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

እንዴት	ትንሽ	ዘወትር	ዛሬ
እዚህ	ክፉኛ	ውስጥ	ብዙ

ሀ. ከመሰላሉ ላይ የወደቀው አናፂ _____ ተጎድቷል።

ለ. ከዚያ አስከፊ አደጋ _____ ተረፈ?

ሐ. ፀሐይ ሲመታኝ ስለዋለ ራሴን _____ አሞኛል።

መ. ከሱ እርቃ ስለምትኖረው ልጁ _____ ይጨነቃል።

ሠ. አባቴ መጽሐፍ እያነበበ ከቤት _____ ተቀምጧል።

ረ. አቤል የሒሳብ ትምህርት ውጤቱን ለማሻሻል _____ ደከመ።

ሰ. ከረጅም ጊዜ መለያየት በኋላ ጓደኛዬ ገብሬን _____ አገኘሁት።

3.3.1 ማዳመጥ

ሀገር መውደድ

ቅድመማዳመጥ

ሀ. ሥዕሉን በማስተዋል የምታዳምጡት ታሪክ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።



አብዮት	ጠቅላይ ጦር ሠፈር	ጦር ግንባር	ዘመቻ

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ታሪኩ የተከናወነው መቼ ነው?

ለ. ሶማሊያ ኢትዮጵያን እንድትወር መልካም አጋጣሚ የፈጠረላት ምንድን ነበር?

ሐ. "ጥይት ግንባሩን እንጂ ከቶውንም ጀርባውን እንደማይመታው" ማለት ምን ማለት ነው?

መ. "ተው በሉት ያንን ሰው ምንድን ነው ዘንድሮ

እሳት ሊበላው ነው በገዛ እጁ ጭሮ።" የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

ሠ. በርዕሱና ባዳመጣችሁት ታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት አብራሩ።

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ተመሳሳይ ፍቺ ጻፉ።

አዝልቃ	ድንበር	አስተጋባ
ተጥለቀለቀ	ጎህ ሲቀድ	ያልተደራጀ

3.3.2 አንብቦ መረዳት

የቺምቺም ጨዋታ

ቅድመንባብ

ስለምታውቋቸው የባህላዊ ጨዋታዎች ግጥሞች አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ምሳሌ፤

- ሆያ ሆዬ
- አሲና ገናዬ
- ሚሻሚሾ

የቺምቺም ጨዋታ

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዝግጅቶች ላይ ጭፈራዎችን መመልከትና በዜማ የሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞችን ማዳመጥ የተለመደ ነው። የአዲስ ዓመትና የተለያዩ በዓላት ማድመቂያዎችም እነዚሁ ጭፈራዎችና በዜማ የሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ድርቅ ሲሆን፣ ለጦርነት ዘመቻ ሲደረግ፣ በጎበረተሰቡ ላይ በደል ሲደርስ ወዘተ ሐሳብን፣ ደስታንና ሐዘንን በእነዚሁ ባህላዊ መንገዶች መግለጽ ሕዝቡ እያዳበረው የመጣ እሴቱ ነው። ከእነዚህ በዜማና በጭፈራ ታጅበው ከሚቀርቡ ቃላዊ ግጥሞች መካከል የቺምቺም ጨዋታ አንዱ ነው።

የቺምቺም ጨዋታ በአዲስ ዓመት ዋዜማ የሚከወን የወግዲና አካባቢዋ ጎረምሶች ባህላዊ ጨዋታ ነው። ጭፈራው የሚከተሉትን ስንኞች በጋራ በማዜም ይጀመራል።

ያሆ! ያሆ! ያሆ! (2 ጊዜ)

እምቢአለ! እምቢአለ! (2 ጊዜ)

እያጋመረ! እያጋመረ! (2 ጊዜ)

ቀጥሎ አቀንቃኙ የሆታ ግጥሞችን ሲያወርድ፣ ተቀባዮች “እያጋመረ! እያጋመረ!” በማለት ይቀበሉታል።

አቀንቃኝ፤ አንድ አልፎ አንድ አልፎ ይበሳል ቀንበር፣

ተቀባይ፤ እያጋመረ! እያጋመረ!

አቀንቃኝ፤ የዱላው ለታ የት ሄደህ ነበር።

ተቀባይ፤ እያጋመረ! እያጋመረ!

አቀንቃኝ፤ አንተ እንዴት እንዴት ትናገራለህ፣

ተቀባይ፤ እያጋመረ! እያጋመረ!

አቀንቃኝ፤ ዙሪያው ገደል ነው መሸሻም የለህ።

ተቀባይ፤ እያጋመረ! እያጋመረ! (3 ጊዜ)

ቀጥሎም አቀንቃኙ ግጥሞችን ሲያወርድ፣ ተቀባዮች ለየት ባለ መልኩ “አበባ! መውዜር አበባ!” በማለት እየተቀበሉት ጨዋታው ይቀጥላል።

አቀንቃኝ፤ አበባ! መውዜር አበባ!

ተቀባይ፤ አበባ! መውዜር አበባ!

አቀንቃኝ፤ ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ዋሾ፣

ተቀባይ፤ አበባ! መውዜር አበባ!

አቀንቃኝ፤ ሲሸሽ አየነው ጌሾ ለጌሾ።

ተቀባይ፤ አበባ! መውዜር አበባ!

አቀንቃኝ፤ ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ላዛ፣

ተቀባይ፤ አበባ! መውዜር አበባ!

አቀንቃኝ፤ ሲሸሽ አየነው ታዛ ለታዛ።

ተቀባይ፤ አበባ! መውዜር አበባ! (3 ጊዜ)

በሦስተኛ ደረጃ "ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም " በማለት ይቀበሉታል።

አቀንቃኝ፤ ነይ ዞማ ዓለም፣ ነይ ዞማ ዓለም፣

ተቀባይ፤ ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም፣

አቀንቃኝ፤ ድግሳቸውን ወልምጠህ ወልምጠህ፣

ተቀባይ፤ ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም፣

አቀንቃኝ፤ ወዴት ትሸሻለህ ደረት ገልብጠህ።

ተቀባይ፤ ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም፣

ተቀባይ፤ ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም፣

አቀንቃኝ፤ ሲሸሽ ይውልና እንደቀንዳም በሬ፣

ተቀባይ፤ ህም! ህም! ነይ ዞማ ዓለም ዓለም፣

አቀንቃኝ፤ ማታ ቤት ሲገባ ያበጃጃል ወሬ።

ተቀባይ፤ ህም! ህም! ነይ ዞማ አለም ዓለም፣ (3 ጊዜ)

በማለት ሌሊቱን በሙሉ በየቤቱ አየገቡ ሲጨፍሩና ሽልማት ሲቀበሉ ያድራሉ።

[ምንጭ፤ አያሌው አራጌ። (2007) የቺምቺም ጨዋታ በወግዲ። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የቺምቺም ጨዋታ የሚከወነው የት አካባቢ ነው?

ለ. የቺምቺም ጨዋታ የሚከወነው መቼ ነው?

ሐ. “አንድ አልፎ አንድ አልፎ ይበሳል ቀንበር፣

የዱላው ለታ የት ሄደህ ነበር።” የተባለው ለምን ዓይነት ሰው ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

መ. በዚህ ባህላዊ ጨዋታ ውስጥ የሚባሉ ግጥሞችን በማስተዋል የአካባቢው ማኅበረሰብ ምን ዓይነት ባህርይ የሚያደንቅ ይመስላችኋል?

ሠ. ከምታውቋቸው ባህላዊ ጨዋታዎች አንዱን መርጣችሁ በክፍል ውስጥ ከውኑ።

ቃላት

የተሰመረባቸውን በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተኩ።

ሀ. ሲሸሽ አየነው <u>ታዛ ለታዛ</u>፣

ለ. ድግሳቸውን <u>ወልምጠህ ወልምጠህ</u>፣

ሐ. ይሄ ምን ይላል <u>ጎፈሬው ዋሸ</u>፣

መ. ዙሪያው ገደል ነው <u>መሸሻም</u> የለህ፣

ሠ. ማታ ቤት ሲገባ <u>ያበጃጃል</u> ወሬ፣

መጻፍ

ግጥሙን አንብባችሁ ዋናውን መልዕክት በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

ሕይወት ጥንድ እግር

ለረጅም ርቀት ጉዞ ላይ እንዳሉ፣

ሕይወት በባህርይዋ ጥንድ እግር ናት አሉ።

ከፊት የቀደመው አይመሳደቅም፣

ከኋላም የቀረው አይሸማቀቅም።

ያለበት ሁኔታ ይገለባበጣል፣

ኋላ የነበረው ወደፊት ይመጣል።

[ምንጭ፤ እንዳለ ወርቁ። (2012 ዓ.ም)። የኹለት የብር ኖቶች ወግ፤ ገጽ 85፤ ለወጥ ተደርጎ የተወሰደ።]

3.3.3 ማዳመጥ

ሀገር መውደድ

ቅድመማዳመጥ

“ሀገር መውደድ” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁ ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ጦርነቱን ያሸነፈው ማን ነበር? እንዴት አወቃችሁ?

ለ. ሀገር መውደድ ማለት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይገለፃል?

ሐ. ከምንባቡ ያስገረማችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን?

መ. የምታውቁትን የጀግንነት ግጥም በክፍሌ (በፉከራ) አሳዩ።

ቃላት

የተሰመረባቸውን ቃላት በተመሳሳይ ቃላት ተኩ።

ሀ. ያገሬ አርሶአደር ሞፈር መቁረጥ ያውቃል፣

ካልተለበለበ መቼ ይታረቃል።

ለ. እሳት ሊበላው ነው በገዛ እጁ ጭሮ፣

ሐ. ያሉት ጥቂት ወታደሮችም አብዮቱን በመጠበቅ ግዳጅ ላይ ናቸው።

መ. ፉከራው ቀለጠ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የቺምቺም ጨዋታ” በሚለው ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

3.3.4 አንብቦ መረዳት

ሐሳብን በግጥሞች

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ቃላዊ ግጥሞች በተመሣሣይ ቃላዊ ግጥሞች ተኩ።

ሀ. ያርሣል ያሣርሣል ያወጣል እዳሪ፣
ሚስቱን አይላትም በቅል ተበደሪ።

ለ. አባይ ጉደል ብለው አለኝ በትሳስ፣
የማን ሆድ ይችላል እስከዚያው ድረስ።

ሐሳብን በግጥሞች

ሀ	ለ
1. እጅም ሥራ ሥራ እግሬም ተራመድ፣ ራስን ካልቻሉ አይወድም ዘመድ። 2. ኧረ ሰው ኧረ ሰው፣ ሰው አስቸገረኝ፣ ብናገር አፈኛ ዝም ብልም ሞኝ። 3. ከሰው ቤት እንጀራ ከፍትፍት መረቁ፣ የእናት ቤት ይሻላል ዘንጋዳው ደረቁ። 4. ምነው በሰማሁሽ ያኔ ስትነግሪኝ፣ እንግዲህ ተውኩልሽ ይቅርታ አድርጊልኝ።	ሀ. እኔ ሰው አምናለሁ ሰው ግን ይከዳኛል፣ የሆዱን እያየ አምላክ ይረዳኛል። ለ. እናት ለምን ትሙት ትሂድ አጎንብሣ፣ የምታሣድግ ናት በችግር ተጠብሣ። ሐ. አንበሳ ተኝቶ ላም ተራመደችው፣ አውቆ ቢያሳልፋት ሞኝ አደረገችው። መ. ሁሉንም አየሁት በቀኝም በግራ፣ እንደሥራ የለም ሁሉን የሚያኮራ። ሠ. እንግዲህ አልወጣም እኔ ከሰው ፊት፣ አስተምረሽኛል ራስን መርዳት።

ድኅረንባብ

ሐሳብን በግጥሞች በሚል ርዕስ በቀረቡት ግጥሞች መሠረት በ"ሀ" ክፍል ላሉት ግጥሞች ተስማሚ የሆኑትን ከ"ለ" መርጣችሁ አዛምዱ።

ቃላት

ለተሰመረባቸው ሐረጋት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ራስን ካልቻሉ አይወድም ዘመድ፣

ለ. የሆዴን እያየ አምላክ ይረዳኛል፣

ሐ. የምታሣድግ ናት በችግር ተጠብሳ፣

መ. እናት ለምን ትሙት ትሂድ አሳንብሳ፣

መጻፍ

ከሚከተሉት ርዕሰጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ ግጥም ጻፉ።

ሀገር	እናት	ትምህርት	ጓደኛዬ	ትምህርትቤቱ

3.3.5 ክለሳ

ሰዋስው

በሚከተሉት ተውሳከግሶች የተሟሉ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

እዚያ	ትንሽ	ክፉኛ	ቶሎ	እዚህ	አምና

አቀላጥፎ ማንበብ

“ሐሳብን በግጥሞች” በሚለው ርዕስ የቀረቡትን ግጥሞች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 4 ዘመናዊ ግብርና

4.1.1 ማዳመጥ

ክፉ ቀን

ቅድመማዳመጥ

ክፉ ቀን ምንድን ነው? ስለክፉ ቀን የምታውቁትን ተናገሩ?



ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. “ጎድናቸው አንድ ኹለት ተብሎ የሚቆጠር” የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

ለ. “የሞት ፍርዱን የሚጠባበቅ እስረኛ ይመስላሉ”፤ የተባሉት እነማን ናቸው?

ሐ. ይህን ታሪክ የሚተርከው ማን ነው? እንዴት አወቃችሁ?

መ. በዕድሜ የገፉት አርሶአደሮች የመጨረሻ እጣ ፈንታቸው ምን ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

ሠ. ድርቅን መከላከል የሚቻል ይመስላችኋል? እንዴት?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ጭር

ለ. ነበልባል

ሐ. ማሚሸት

መ. እጣን

ሠ. ያሸልባሉ

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ርስበርስ ተወያዩ።

ሀ. ስለምርጥ ዘር ታውቃላችሁ? በምርጥ ዘርና በሌላው ዘር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ለ. ምርጥ ዘር ለምን ይጠቅማል?

ምርጥ ዘር

የሀገራችን የሕዝብ ቁጥር ከእለት እለት እየጨመረ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። አርሶአደሮቻችን ባላቸው የተቆራረጠ አነስተኛ የመሬት ይዞታና ባህላዊ የአመራረት ዘይቤ እያደገ የመጣውን ሕዝብ መመገብ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ነባራዊ ሁኔታው ማስረጃ ነው። መፍትሄው ዘመናዊ እርሻን መቅሰምና መተግበር ነው። ምርጥ ዘር ተጠቅሞ የምርታማነት እመርታን ማምጣት ደግሞ አንዱ የዘመናዊ እርሻ ጉዳይ ነው። በሀገራችን ከማዕዳችን በብዛት የማይጠፋውን የጤፍ ምርትን ለማሳደግም በምርምር ተቋማት የሚወጡ የጤፍ ምርጥ ዘሮች አሉ። የሚከተለው ሠንጠረዥ ይህንኑ መረጃ ያቀርባል።

በቂ ዝናብ ላላቸው አካባቢዎች

የምርጥ ዘሩ ዓይነት	ተስማሚ ከፍታ (ሜትር ከባህር ጠለል በላይ)	የዝናብ መጠን (በሚሊ ሜትር)	ለመድረስ የሚያስፈልጉ ቀናት(በምርምር መደብ)	የዘር ቀለም በአርሶአደር ማሳ	ምርታማነት (ኩንታል በሄክታር)	
ማኛ	1500-2400	200-700	80-113	በጣም ነጭ	18-22	14-16
ቁንጮ	1500-2500	300-700	80-113	በጣም ነጭ	24-28-	20-22
ዱከም	1400-2400	150-700	76-138	ነጭ	24-34	20-25
ኬና	1850-2400	1000-1200	110-134	በጣም ነጭ	17-27	13-23
እፁብ	1800-2600	1230	92-127	ነጭ	19-27	16-22
ዲማ	2000-2600	>600	105	ቀይ	24.6	16.8
ኮራ	1650-2400	500-800	110-117	በጣም ነጭ	25-28	20-22
ዳግም	1700-2500	700-1200	111-114	በጣም ነጭ	25-28	20-24
ንጉሥ	1700-2400	700-1200	105	በጣም ነጭ	አማካይ 28	22-26

[ምንጭ:- የኢፌዴሪ ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር። (2010 ዓ.ም)። "የሰብል አመራረት ፓኬጅ"] ዓ.ም)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሀገራችን ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መምጣት አሳሳቢ የሆነው በምን ምክንያት ነው?

ለ. የምርጥ ዘርና የምርታማነት ግንኙነት ምንድን ነው?

ሐ. "ኮራ" በሚል ስም የሚታወቀው የተሻሻለ የጤፍ ዝርያ የሚፈልገው የዝናብ መጠን ምን ያህል ነው?

መ. "ንጉሥ" የሚባለው የጤፍ ዘር ለመድረስ ስንት ቀናት ያስፈልጉታል?

ሠ. ከፍተኛ ምርት የሚያስገኘው የጤፍ ዓይነት የትኛው ነው? በምን ያህል ሄክታር ምን ያህል ኩንታል ምርት ያስገኛል?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተመሳሳይ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ዘይቤ	ሀ. ግልጽ
2. መቅሰም	ለ. ምግብ
3. እምርታ	ሐ. ተጨባጭ ሁኔታ
4. ማዕድ	መ. ባለቤትነት
5. የአደባባይ ምስጢር	ሠ. እድገት
6. ይዞታ	ረ. መማር
7. ነባራዊ ሁኔታ	ሰ. ዘዴ
	ሸ. ድብቅ

መጻፍ

የእርሻ መሬት ለማግኘት ሲባል ደንን መመንጠር ስለሚያስከትለው ጉዳት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

4.1.3 ማዳመጥ

ክፉ ቀን

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ክፉ ቀን” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ታሪክ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. “እንደወንዞች ደርቀው፣ እንደከብቶች ከስተው፣ በዝምታ የተፈጥሮን ልግስና ይጠባበቃሉ” የተባሉት እነማን ናቸው? እንዴት አወቃችሁ?

ለ. “ተፈጥሮ ፊቷን አዙራባቸዋለች” የተባሉት እነማን ናቸው?

ሐ. በታሪኩ የተገለጸው ችግር በምን ምክንያት የተፈጠረ ይመስላችኋል?

መ. ታሪኩ የተፈፀመው የትና መቼ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ጻፉ።

ወበቅ	ልግስና	ሕይወት	ገርጥቶ	ተነፍቶ	ከስተው

አቀላጥፎ ማንበብ

“ምርጥ ዘር” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

4.1.4 አንብቦ መረዳት

ተሸላሚው አርሶአደር

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

ሀ. አርሶአደሮችን መሸለም ለምን የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?

ለ. በአርሶአደሮች መካከል ልዩነት ያለ ይመስላችኋል? ለምን?

ተሸላሚው አርሶአደር

በደጀን ወረዳ የየትኖራ ቀበሌ ነዋሪውና የአረንጓዴ “ሪባን” ተሸላሚው አርሶአደር ገላነህ ታምራት ጤፍን በዘመናዊ መንገድ በማምረት ለአካባቢያቸው ማኅበረሰብ አርኣያ ናቸው። በዚህ የመኸር ወቅትም ካለፉት ዓመታት የላቀ ጥራትና መጠን ያለው ጤፍ ለማምረት የባለሙያ እገዛ እየተሰጣቸው ነው። ማወቅ የሚፈልጉትንና ለግብርና ሥራቸው የሚያግዛቸውን መረጃ ለማግኘት ሁልጊዜም የየትኖራ አካባቢ የሰብል ባለሙያዎችን እየጠየቁ ይረዳሉ። ዛሬም ከሰብል ባለሙያ ጋር በመገናኘት የጤፍ ምርትን ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ እየተወያዩ ነው፤

አርሶአደር ገላነህ፤ “ጤፍን በውጤታማነት ለማምረት ምን ዓይነት የማሳ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል?”

የሰብል ባለሙያ፤ “ማሳው በሚገባ የለሰለሰና የተስተካከለ መሆን አለበት። በአማካይ ከ3-5 ጊዜ ሊታረስ ይገባል።”

አርሶአደር ገላነህ፤ “በኮትቻ አፈር ጤፍ ማምረት ይቻላል?”

የሰብል ባለሙያ፤ “የዉኃ መጠን በሚበዛባቸው ‘ኮትቻማ’ መሬቶች ‘ቢቢኤም’ ተጠቅሞ መደብ በማዘጋጀትና ትርፍ የሆነውን ዉኃ በማጠንፈፍ በጥሩ ሁኔታ ጤፍ ማምረት ይቻላል።”

አርሶአደር ገላነህ፤ “አሲዳማነት ባላቸው መሬቶችስ?”

የሰብል ባለሙያ፤ “ጥሩ! የአሲዳማነት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች አፈሩን በኖራ በማከም ምርታማነትን መጨመር ይቻላል። ነገርግን ለጤፍ ሰብል ኖራ መጠቀምን በተመለከተ የተለየ የጥናት ውጤት ስለሌለ በሀገርአቀፍ ደረጃ ለሁሉም ሰብሎች በጥቅል በተቀመጠው ምክረሐሳብ መሠረት መጠቀም ያስፈልጋል።”

አርሶአደር ገላነህ፤ “ለዛሬ ያሉኝ ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው። ጠቃሚ ቁምነገር ጨብጫለሁ። አመሰግናለሁ።”

የሰብል ባለሙያ፤ “ያው እንደተለመደው ያገኙትን እውቀት ተጠቅመው የተሻለ የጤፍ ምርት እንደሚያገኙ እተማመናለሁ። እዚህ ድረስ መጥተው ለማወቅ ያደረጉትን ጥረት አደንቃለሁ። ለዚህም አመሰግንዎታለሁ።”

አርሶአደር ገላነህ ያገኙትን ምክረ ሐሳብ ለየትኖራ ቀበሌ አርሶአደሮች ለማካፈል ሁሉንም ጠቃሚ ነገር በማስታወሻቸው ላይ አስፍረዋል።

[ምንጭ፦ መነሻ ሐሳብ፤ የኢፌዴሪ ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር። (2010 ዓ.ም)። “የሰብል አመራረት ፓኬጅ]”

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምልልሳዊ ምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አርሶአደር ገላነህ ታምራት በተለይ ውጤታማ የሆኑበት የምርት ዓይነት ምንድን ነው?

ለ. አንድ የጤፍ የእርሻ መሬት የተሻለ ምርት እንዲሰጥ ምን ያህል ጊዜ መታረስ አለበት?

ሐ. በኮትቻ አፈር ጤፍ ማምረት የሚቻለው እንዴት ነው?

መ. አርሶአደር ገላነህ ውጤታማ የሆኑት ለምን ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

ሠ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሰብል	መኸር	ማከም	ምርታማነት	ማጠንፈፍ	ኮትቻ	ኖራ	አርኣያ

መጻፍ

ጅምር ዓረፍተነገሮቹን ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. _____ የጓሮ አትክልቱን ኮተኮተ

ለ. ችግኝ መትከል _____

ሐ. በጧት ተነስቼ _____

መ. የትምህርትቤታችን ግቢ _____

ሠ. መንገድ ስናቋርጥ _____

4.1.5 ክለሳ

ቃላት

1. ለተሰመረባቸው ቃላት ከአውዳዊ ፍቻቸው ውጪ በሚኖራቸው ትርጉም ዓረፍተነገር መሥርቱ።

   ሀ. እንደእሳት ላንቃ …

   ለ. አዝማሪዎች ማሲንቆዎቻቸውን በባህር እጣን ማሟሸትና መቃኘት ትተዋል።

   ሐ. በመቃጠል ላይ ካለው ቤት እንደእሳተገሞራ የሚቆረጠው ነበልባል በሩቁ ይጋረፋል።

   መ. በዕድሜ የገፉ አርሶአደሮች …

2. በሚከተሉት ቃላት/ሐረግ የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

መቅሰም	ገርጥቶ	ማዕድ	የአደባባይ ምስጢር	ማጠንፈፍ	ወበቅ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ተሸላሚው አርሶአደር” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

4.2.1 መጻፍ

1. የቅንፍ ሥርዓተነጥብን በአግባቡ በመጠቀም ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

   ምሳሌ፦ ወደቤት እንደገባን እንደተከበረ እንግዳ ስለታየን ወቃሊሞ (በአርጎባ አካባቢ ከሥጋና ከቅመማቅመም የሚሠራ ምግብ) ቀረበልን።

   ሀ. በአካባቢው በባህላዊ መልኩ ከጥጥ ከሚሠሩ ባህላዊ አልባሳት መካከል ወንዶች ከወገብ በታች የሚለብሱት መስነፍ ሸርጥ አንዱ ነው።

   ለ. በተለየ አጥር የተከለለው የእንስሳት ተራ በበሬ፣ በላም፣ በበግ፣ በፍየልና በጋማ ከብቶች አህያ፣ በቅሎ፣ ፈረስ ተጠቅጥቋል።

   ሐ. እንደዚህ ዓይነቱ የጤና እክል ችግር ያለበት ሰው ወደባህል ሀኪሞች ዘንድ ሄዶ መድኃኒት ይሰጡት ዘንድ በምስጢር ይጠይቃል።

መ. በዚህ ጊዜ የሚዘሩ የአዝርዕት ወይም የሰብል ዓይነቶች የአበባ፣ የብርዕ የስንዴ፣ የገብስ እና የጤፍ ሰብሎች ናቸው።

2. ከመምህራችሁ ጋር በጋራ በመሆን የሚከተለውን መንደርደሪያ ዓረፍተነገር በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ።

ልጆችንና ችግኞችን ብዙ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች አሉ። . . .

4.2.2 አንብቦ መረዳት

ምርቃንና ርግማን

ቅድመንባብ

ሀ. ርዕሱንና ሥዕሉን ስታስተውሉ ምንባቡ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. በሚከተሉት ቃላት ፍቺ ላይ ርስበርስ ተወያዩ።

- ምርቃን
- ርግማን

ምርቃንና ርግማን





በድሮው ጊዜ ዝንቦች እንደንቦች ሁሉ መሪ ነበራቸው፤ ኑሯቸውም በትብብር ላይ የተመሰረተ ነበር። ከቦታ ቦታ በመብረር ልዩ ልዩ የሆነ የማር ዓይነት ይሠሩም ነበር። ከንቦች ጋር በመልካም ጉርብትና ተከባብረው የመኖር እሴት ከማዳበራቸው የተነሳ የታታሪነትና የትጋት ክብረበአላቸውን ከንቦች ጋር አንድ ላይ ሆነው ያከብሩ ነበር። ኑሯቸውን ለማሻሻልም በየጊዜው በመገናኘት በጋራ ይመክራሉ።

ከእለታት አንድ ቀን ንብና ዝንብ በአንድ ጉዳይ ላይ ለመምከር ቀጠሮ ያዙ፤ ቀጠሯቸውን አክብረው በተወሰነው ቦታ በሰዓቱ ተገኙ። የዝንብ ንጉሥና የንብ ንግሥት ስብሰባውን መምራት ጀመሩ። የዝንብ ንጉሥ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ "የተከበርከው የዝንብና የንብ ሰራዊት ሆይ፣ ሕይወታችን የበለጠ የሰመረ እንዲሆን ከሰዎች ጋር መተባበር ይኖርብናል፤ ይህንን ትብብር ለመጀመር የሚያስችለንን ጥበብ ለመቅሰምም ከሰዎች ዘንድ የላቀ ጥበብ ወዳለው ንጉሥ ሰለሞን ዘንድ በመሄድ ምክር መቀበል ስለሚኖርብን ከዝንብና ከንብ ሰራዊት አንዳንድ ተወካይ

መርጠን ወደንጉሡ ቤተመንግሥት መላክ ይኖርብናል።" ብሎ ንግግሩን ሲጨርስ የንብ ንግሥትን ጨምሮ ሁሉም በጭብጨባ ደገፉት።

ወዲያው ከኹለቱ ወገኖች አንዳንድ ተወካዮች ተመረጡ። ተወካዮችም ካመረቱት ማር ምርጡን በገፀበረከትነት በመያዝ ምክር ፍለጋ ወደንጉሥ ሰለሞን ዘንድ ሄዱ። እንደደረሱም ከወገባቸው ጎንበስ በማለት "ንጉሥ ሆይ ሺ ዓመት ንገሥ! ጥበብህ የላቀና የረቀቀ፣ የኛን ቋንቋም የምትችል መሆኑን ሰምተን ከሰው ጋር እንዴት መኖር እንዳለብን ምክርህን ፈልገን መጣን" አሉ። ንጉሡም በደስታ ተቀብሎ ምግብና መጠጥ እንዲቀርብላቸው አደረገ።

ምክሩን ከመስጠቱ በፊት ግን ንብ ንግሥቷን፣ ዝንብ ደግሞ ንጉሣቸውን እንዲገድሉ አዘዛቸው። ዝንብ በፍጥነት ሄዶ የዝንቦችን ንጉሥ በመግደል በኩራት "ንጉሥ ሆይ! ያዘዝከኝን ፈጽሜያለሁ!"፤ አለ። ንጉሥ ሰሎሞንም ፊቱን አጥቁሮ "እንዴት መሪህንና ሰብሳቢህን ትገድላለህ?! ያዘዝኩህ የአስተሳሰብ ብስለትክን ለመለካት ነበር። አዝናለሁ! ከእንግዲህ ዝንቦች ሁሉ መልካም ከሆነ ነገር ርቃችሁ፣ ውሎ አዳራችሁ ያለመሪና ያለሰብሳቢ በቆሻሻ ቦታ ይሁን" ብሎ ረገማቸው።

ወዲያውም ንብ ስትከንፍ ከተፍ አለች። "ትእዛዜን ፈፀምሽ?" አላት ንጉሡ። "ንጉሥ ሆይ እንዳስረዳ ይፈቀድልኝ፤ መሪዬን መግደል ህሊናዬ አልፈቀደም። ንግሥታችንን ብገድላት የንብ ሰራዊት ያለሰብሳቢ ስለሚቀር ማር የመሥራት ጥበብ ይጠፋል፤ ስለዚህ በንግሥቲቱ ፈንታ እኔ ለመሞት ፈቃደኛ ነኝ።" አለች። ጠቢቡ ሰለሞንም ፈገግ አለና "አይዞሽ! አንቺም ንግሥትሽም አትሞቱም። ከዛሬ ጀምሮ የንብ ዘር የተባረከ ይሆናል። ማራችሁ መድኃኒት ይሆናል። ሰውም ቢሆን ለማራችሁ ሲል ሲንከባከባችሁ ይኖራል"፤ በማለት መረቃት።

[ምንጭ:- አብክመ ቱሪዝም ቢሮ። (2001 ዓ.ም.)። የአማራ ክልል ተረታተረት ስብስብ። የተወሰነ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "ከወገባቸው ጎንበስ በማለት"፤ የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

ለ. ዝንብ የተረገመው በምን ምክንያት ነው?

ሐ. ዝንብ ንጉሡን ለመግደል የጨከነው ለምን ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

መ. የማንን ድርጊት ትደግፋላችሁ? የዝንብን ወይስ የንብን? ለምን?

ሠ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተስማሚውን መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ገፀበረከት	ፊቱን አጥቁሮ	ፈንታ	ምርጡን	ያለሰብሳቢ	ከተፍ አለች

ሀ. ወደቤቱ በጧት የሄድኩት ብድር ልጠይቀው እንደሆነ ስለገባው _____ ተቀበለኝ።

ለ. የጓደኛዬ ልደት ነገ ስለሆነ የልደት _____ ልገዛ ከእናቴ ጋር ወደሱቅ ሄድኩ።

ሐ. እናት ምንጊዜም ምርጥ _____ ለልጇ መስጠት ትወዳለች።

መ. ባህር ዳር የምትኖረው ታላቅ እህቴ ድንገት _____።

ሠ. አባታችን በመኪና አደጋ ከሞተ ወዲህ ቤተሰባችን _____ ቀረ።

ረ. ሰሚራ ታማ ስለቀረች በሷ _____ ብሩክ ክፍላችንን ወክሎ ተወዳደረ።

መጻፍ

ሀ. የሚከተለውን የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር በደብተራችሁ አዘጋጁና ስለንብና ስለዝንብ ተመሳስሎና ልዩነት መረጃዎችን አሟልታችሁ ጻፉ።



ለ. ያዘጋጃችሁትን ቢጋር በመጠቀም ስለንብና ዝንብ ተመሳሳይነትና ልዩነት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

4.2.3 ሰዋስው

ከሚከተሉት ቃላት የጊዜ ተውሳከግስ በሆኑት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡- የትርሲት ልደት ዛሬ ተከበረ።

እንዴት	ጥቂት	ለምን	አያሌ	ቅድም	ትንሽ	ማታ	እዚህ
ዛሬ	አምና	ዘወትር	አሁን	ወዲህ	ወዲያው	ድሮ	ክፉኛ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ምርቃትና ርግማን” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

4.2.4 አንብቦ መረዳት

ስንፍናን ርገሙት

ቅድመንባብ

ርዕሱን በማስተዋል ግጥሙ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ስንፍናን ርገሙት

“የተማረ ሆኖ እውነቱን የማይገልጽ፣
ባለፀጋ ሆኖ ከገንዘቡ ማይሰጥ፣
ደሃ ሆኖ መሥራት የማይሻ ልቡ፣
ሦስቱም ፍሬ ቢሶች ለምንም አይረቡ።”

እንዳለ ገጣሚው በተባ ብዕሩ፣
ያገሬ ወጣቶች ጠንክራችሁ ሥሩ።
ሀገር የምትለማው በሥራ ነውና፣
ትጋትን ሃብት አርጉ ይቅርና ስንፍና።
ገጣሚው ሲቀጥል ወጣቱን ሲመክር፣
ስንፍናን ሲኮንን እንዲጠፋ ካገር፣
በጠለቀ ቋንቋ እንዲህ ብሎ ነበር።

“ዐይን የለውም አሉ የሰነፍ ልመና፣
ወደአምላክ ሲጸልይ ማታ በልቦና፣
መንገዱ ሳይመታኝ ባቢራ በጭቃ፣
አድርገኝ ይለዋል ላገሬ እንድበቃ፣
እንጦጦ ተኝቼ ሐረር እንድነቃ።“

እናም ታዳጊዎች ስንፍናን ርገሙት፣
ጉልበትህ ይሸመድመድ ዐይንህ ይጥፋ በሉት፣
ሌት ከቀን ተማሩ በርትታችሁ አጥኑ፣
ለሀገራችሁ ኩራት መጠሪያ እንድትሆኑ።

[ምንጭ፡- መነሻ ሐሳብ፤ ከበደ ሚካኤል። (1933)። የእውቀት ብልጭታ፤ ከመጠነኛ ለውጥ ጋር የተወሰደ]

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ገጣሚው “ሶስቱም ፍሬ ቢሶች” ያላቸውን ነገሮች ዘርዝሩ።

ለ. ምክር ያቀረበልን ሰው በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ይመስላችኋል?

ሐ. ስንፍናን መርገም ትክክል ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

መ. ግጥሙ የተጻፈበት ዓላማ ምንድን ነው?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ባለፀጋ	ይሸመድመድ	የማይሻ	ልቦና	መጠሪያ

መጻፍ

ግጥሞቹን አሚልታችሁ ጻፉ።

ጎበዝ እረስ እረስ ማረስ ያስከብራል።

በየደረሱበት የልብ _____።

በዚህ አንድ በዚያ አንድ ሰላሣ ቢወራ፣

አርሳለሁ መርሬ ዝናብም _____።

በዘመናዊ ማረሻ ካልገማመሱት፣

እልፍኝ አይሞቅም _____።

በዚህ መቶ ወቂ በዚያ መቶ ወቂ፣

የኮምባይነር ባለቤት _____።

ማሳህን እንዲሁ አረም ከሚበላው፣

ፀረአረም አርግበት _____።

4.2.5 ክለሳ

ሰዋስው

ሀ. ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ የተውሳከግስ ዓይነቶችን በምሳሌው መሠረት አመልክቱ።

ተውሳከግስ	የጊዜ	የቦታ	የመጠን	የሁኔታ
ቶሎ	✓			
በጣም				
ክፉኛ				
ወደዚያው				
ወዲያው				
ሌሊት				

ለ. በሠንጠረዡ ውስጥ ካሉት ተውሳከግሶች መርጣችሁ አንቀጹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ያለወትሮዬ _____ ነቃሁ። የሆነ ድምፅ የሰማሁ መሰለኝ። ድምፁ ምን እንደሆነና ከየት እንደመጣ ግን አላውቅም። ጆሮዎቼን ነቃ አድርጌ ሳዳምጥ የሆነ ድምፅ _____ ሰማሁ። ድምፁ የሚመጣው ከወደኩሽናው መሰለኝ። ከአልጋዬ _____ ተነሳሁ። በሌሊት ልብሴ እንደሆንኩ በባዶ እግሬ _____ አመራሁ። ፀጉሩና ዒመ የተንጨባረረ ሰው ምግብ አቅርቦ እየበላ ነው። የቲማቲም ድልህ በመሰሉ አይኖቹ ሲያፈጥብኝ _____ ፈራሁ። ከፍርሃቴ የተነሳ ደንብሬ ወደኋላ እሮጣለሁ ስል ከግድግዳው ጋር _____ ተጋጨሁ።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት/ሐረግ የተሟላ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ገፀበረከት	ፊቱን አጥቁሮ	ምርጡን	ምርቃት	ጠመደ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ስንፍናን ርገሙት” የሚለውን ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

4.3.1 ማዳመጥ

ከምንጣሮ እስከጎተራ

ቅድመማዳመጥ

ሀ. ከርዕሱ በመነሳት ስለምንባቡ ሐሳብ ገምቱ።

ለ. በሚከተሉት ቃላት ፍቺ ላይ ርስበርስ ተወያዩ።

ምንጣሮ	ማረም	መጎልጎል	ጎተራ

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በቅድመማዳመጥ ስለምንባቡ የገመታችሁት ትክክል ሆኖ አገኛችሁት? እንዴት?

ለ. በእርሻ ሥራ የቅድመዝግጅት ሥራዎች የተባሉት ምን ምን ናቸው?

ሐ. አረምን ማስወገድ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

መ. በማምረት ሂደት ብክነትን እንዴት መከላከል የሚቻል ይመስላችኋል?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ቅድመዝግጅት	ማከናወኛ	እንዲቀጭጭ
ብክነት	ተባይ	

ቅድመንባብ

ሀ. እናትና መሬትን የሚያመሳስላቸው ነገር ምን እንደሆነ ተናገሩ።

ለ. "እናት መሬት" በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ስለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ያላችሁን ግምት በሹለተኛው አምድ ውስጥ ጻፉ።

ቃል	የተገመተ ፍቺ	ከንባብ በኋላ	ፍንጭሰጪ ቃል/ሐረግ
ይታደል ዘንድ	እድለኛ እንዲሆን		
ማስተዳደር	መምራት		
ከተላቀቀ			
የተጎሳቆሉ			
ስትሰስት			
ትለግሰዋለች			

እናት መሬት

የሰው ልጅ ህልውና ከመሬት ጋር የተያያዘ ነው። የሚመገበውን ምግብ፣ የሚጠጣውን ውኃ የሚያገኘው ከመሬት ነው። ሰው መሬትን ያርሳል፤ እሷ የሰጠችውን ዘር መልሶ መሬት ላይ ይበትናል፤ ያርማል ይኮተኩታል፤ ምርቱን ይሰበስባል። ይህንን የሚያደርገው ለመኖር የሚያስፈልገውን ምግብ ለማግኘት ነው። መሬት በገጿና በማህፀኗ የምትይዘው ውኃ በትነት መልክ ይወጣና ዝናብን ያስገኛል፤ ዝናቡም ምድርን ያርሳታል፤ ቡቃያዎች ያድጋሉ፤ የሰውን ልጅ ይመግባሉ። የመሬት እናትነት ይህ ብቻ ግን አይደለም። ወርቅና አልማዝ የሚገኘው ከመሬት ነው። ነዳጅ፣ ስሚንቶ፣ ብረት፣ ወዘተ የሚመረተውም ከዚችው መሬት ነው።

መሬት በአግባቡ ከተያዘች መልካም መልካሙን ሁሉ ታበቅላለች። ያበቀለችውን ሳትሰስት እየመገበች ታሳድጋለች። አሳድጋም ለፍሬ ታበቃለች። እንስሳትም ያለገደብ ይራባሉ። የሰው ልጅም እንዲሁ ያለምንም ችግርና ሐሣብ ተዝናንቶ ይኖር ዘንድ የሚፈልገውን አትነፍገውም። እስትንፋሱን አስተካክላ ጤናማ ሕይወትን ትለግሰዋለች። ይህቺ እናት የሆነች መሬት አቅሟ ውስን ነው። የሚያልቅ ሃብት አላት፤ የሚታደስ ሃብትም አላት። የሚያልቀውን ሃብቷን በቁጠባና በሥርዓት

መጠቀም ይገባል። መሬት ታዳሽ ሃብቷን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለሰዎች መስጠት የምትችለው ለእሷም እንክብካቤ ሲደረግላት ነው።

የመሬት ለም የሆነው ክፍሏ በነፋስና በጎርፍ እንዳይሸረሸር ማድረግ ይጠበቃል። የአስተራረስ ዘይቤን ማስተካከል፣ እጽዋትን መትከልና መንከባከብ፣ ልቅ ግጦሽን ማስወገድ ወዘተ የአፈር መሸርሸርን ያስቀራል። በዘፈቀደ እየደጋገሙ ማረስና የተገኘውን እህልና ጥራጥሬ መዝራት መሬት የምትሰጠውን ጥቅም ዝቅ ያደርጋል። መሬት ረፍት ትፈልጋለች፤ ሰብል በማምረት ያጣቻቸውን ንጥረነገሮች መልሳ እስክታገኝ ድረስ ሳትታረስ መቆየትን ትፈልጋለች። ከዚህ በተጨማሪም የምትፈልገውን ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ ማዳበሪያ ስታገኝም ታገግማለች፤ ለሰብል ምርት መያዝ የሚገባትን ሁሉ ታገኛለች።

እነሆ የሰው ልጅ ከጉስቁልና የተላቀቀ፣ አስደሳችና ጤናማ ኑሮ ይታደል ዘንድ ሕይወቱ የሆነችውን መሬት በውጤታማ መንገድ ማስተዳደር ይኖርበታል። መሬት እንዳትጎሳቆል መጠበቅ፣ ስትጎሳቆልም አስፈላጊውን ህክምና መስጠት ግዴታው ነው።

መሬት የሰው ልጅ ግዛት ነች። ደግሞም የሰውን ልጅ ትገዛለች። ያከበራትን ታከብራለች። ያጎሳቆላትን ታጎሳቁላለች።

[ምንጭ፡- አማርኛ እንደኹለተኛ ቋንቋ፣ የተማሪ መጽሐፍ፣ 6ኛ ክፍል። (2008 ዓ.ም)።.ገጽ 127፤ ከማሻሻያ ጋር የተወሰደ]

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሰው ልጅ መሬት ስትጎሳቆል የሚያክማት እንዴት ነው?

ለ. “መሬት ያከበራትን ታከብራለች፤ ያጎሳቆላትን ታጎሳቁላለች።” የሚለው አገላለጽ መልዕክት ምንድን ነው?

ሐ. መሬት የሰውን ልጅ የምትገዛው እንዴት ነው? ሀሳባችሁን በምሳሌ ወይም በማስረጃ አብራሩ።

መ. በታሪኩ ውስጥ መሬት በአንስታይ ፆታ የተገለጸችው ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ?

ቃላት

በቅድመንባብ ስለቀረቡት ቃላት ፍቺ እንደገና አስቡ። የመጀመሪያ ግምታችሁ ትክክል ከሆነ ይህን "✓" ምልክት በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ አስፍሩ። ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ግምታችሁን ከቀየራችሁ ደግሞ አዲሱን ፍቺ በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ ጻፉ። የቃሉን ፍቺ ለመረዳት ያገዛችሁን ቃል በመለየት በአራተኛው ዓምድ ውስጥ ጻፉ።

ቃል	የተገመተ ፍቺ	ከንባብ በኋላ	ፍንጭሰጪ ቃል/ሐረግ
ይታደል ዘንድ	እድለኛ እንዲሆን	እንዲኖረው	አስደሳችና ጤናማ ኑሮ
ማሰተዳደር	መምራት	መጠቀም፣ መንከባከብ	መሬትን በውጤታማ መንገድ
ከተላቀቀ			
የተጎሳቆሉ			
ሳትሰስት			
ትለግሰዋለች			

መጻፍ

በሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩ መሠረት በእናትና በመሬት መካከል ስላለው ተመሳስሎና ልዩነት አንቀጽ ጻፉ።



4.3.3 ማዳመጥ

ከምንጣሮ እስከጎተራ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "ከምንጣሮ እስከጎተራ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

   ሀ. በምርት ወቅት ብክነትን እንዴት መቀነስ ይቻላል?

   ለ. ምርትን ለብልሽት የሚዳርጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው? እንዴት መከላከል ይቻላል?

2. በማዳመጥ ሂደት በሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩ መሠረት የያዛችሁትን ማስታወሻ በመጠቀም በእርሻ ሥራ ስለምርት አመራረት ሂደት ንግግር አድርጉ።

ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸው ቃላት ከአውዳዊ ፍቻቸው ውጪ በሚኖራቸው ትርጉም ዓረፍተነገር ጻፉ።

ሀ. እህሉን <u>ተባይ</u> በላው።

ለ. ብርቱካኑ <u>በስሏል</u>።

ሐ. አርሶአደሩ የማሽላውን ማሣ <u>በማረም</u> ላይ ነው።

መ. የማሣውን አፈር ለፀሐይ ለማጋለጥ <u>የስንጠቃ</u> ሥራ ይሠራል።

አቀላጥፎ ማንበብ

"እናት መሬት" የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ቅድመንባብ

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አንደኛውንና ኹለተኛውን አምዶች አሟልታችሁ ጻፉ፤ ሦስተኛውን አምድ ደግሞ ምንባቡን አንብባችሁ እንደጨረሳችሁ አሟሉ።

ስለአርሶአደር የማውቀው	ስለአርሶአደር ማወቅ የምፈልገው	ስለአርሶአደር ያወቅኩት

አርሶአደር

አርሶአደር ዓይነት ዓይነት አለው። ምስጉን አርሶአደር አለ፤ ሰነፍ አርሶአደር አለ። ምስጉን አርሶአደር የተሰጠውን ማሳ አቀላጥፎ በማረስ ጥራትና ብዛት ያለው ሰብል ያመርታል። ከማሳው ውጪም ሥራ የፈታውን መሬት በተጨማሪ በማረስ ምርታማ እንዲሆን ያደርገዋል። የሚያመርተው ምርት ከእጅ ወደአፍ ብቻ ሳይሆን ተረፍረፍ ብሎ ለልጆች መማሪያ፣ ለቤተሰቦቹ መታከሚያ፣ ለዘመዶቹ መደገፊያ እስከመሆን ይደርሳል።

ሰነፍ አርሶአደር የእርሻ ሥራን ፈጽሞ ይጠላል። ወይም የአካባቢ ሁኔታዎችን እንደምክንያት በመውሰድ ችልተኝነት ያበዛል። በአካባቢ ሁኔታዎች የሚሰንፍ አርሶአደር በሰበብ አስባቡ በማውደልደል፣ ጠበል ጣዲቅ ወይም ምጽዋት ያለበትን በማነፍነፍ አብዛኛውን ጊዜውን ይፈጃል። አንዳንዱ ደግሞ በዓል እየቆጠረ የወሩን ሰላሳ ቀናት በሙሉ በዓል አክባሪ በመምሰል ያለ ቁምነገር ጊዜውን ያሳልፋል። ግማሽ ጎኑ ነጋዴ፣ ግማሽ ጎኑ የሰፈር ነገረፈጅ በመሆን የሚሰንፍ አርሶአደርም አለ። አጉል ኩራት ተከምሮበት፣ “አፈር ገፊነት አይሆነኝም“ በሚል የሚያላግጥ ደግሞ ሌላው ዓይነት ሰነፍ አርሶአደር ነው።

ምስጉን አርሶአደር መሬቱን ለም፣ ጠፍ እያለ ባህርይውንና አገልግሎቱን ልቅም አድርጎ ያውቃል። የአየር ንብረትን በትኩረት ይከታተላል። ደመናና ጉም፣ ውርጭና ዝናብ፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የሚያስከትሉትን ጥቅምና ጉዳት ይረዳል፤ መቋቋሚያ ዘዴዎችንም በቅድሚያ ያዘጋጃል።

ምስጉን አርሶአደር በዘር አመራረጥ በቂ ልምድ አለው። ምን ዓይነት የብርዕ እህል፣ የአበባ እህል ወይም የአገዳ እህል በምን ዓይነት ቦታና የአየር ንብረት ተዘርቶ ምን እንደሚያስገኝ ለይቶ ማወቅን ተክኖበታል። ምን ዓይነት የጓሮ

አትክልት፣ ከምን ቦታ፣ በምን ጊዜ ውጤት እንደሚሰጥ ያውቃል። የጭረት፣ የቅባት፣ የቅመም ሰብል ዓይነቶች እንዴት መያዝ እንዳለባቸው በልምድ ወይም በትምህርት ይደርስባቸዋል።

በአጠቃላይ ምስጉን አርሶአደርና ሰነፍ አርሶአደር በአንድ ቀየ የሚኖሩ፣ የተመሳሳይ መሬት ባለቤት የሆኑ፣ ነገርግን በትጋታቸውና በሥራ ወዳድነታቸው የተለያዩ አርሶአደሮች ናቸው። የራሳቸውና የቤተሰቦቻቸው አኗኗር እንዲሁ የተለያየ ነው። የምስጉን አርሶአደር ቤተሰቦች በሰውነታቸው የዳበሩና የጠነከሩ፣ ከእለት ፍጆታ አልፎ ለነገ ጥሪት ያላቸው ናቸው። የሰነፍ አርሶአደር ቤተሰብ ደግሞ በችጋር የተቆራመዱ፣ የከሱና የገረጡ፣ ለነገ የሚሉት ሃብት የሌላቸው ናቸው።

[ምንጭ:- ዳኛቸው ወርቁ። (1977 ዓ.ም)። የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ። ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ምስጉን ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ጥራትና ብዛት ያለው ምርት ለማግኘት የሚያስችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ጥሩ ምርት ለማግኘት የሰብል ዓይነቶችን ማወቅ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

መ. የየጊዜውን የአየር ንብረት መከታተል ምን ጥቅም የሚያስገኝ ይመስላችኋል?

ሠ. በጎበዝ አርሶአደርና በሰነፍ አርሶአደር ቤተሰቦች አኗኗር መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተቃራኒ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ለም	ሀ. ጥቅም ላይ የዋለ
2. አቀላጥፎ	ለ. ቦዘኔ
3. ማውደልደል	ሐ የተትረፈረፈ
4. ሥራ የፈታ	መ. በሥራ መጠመድ
5. ከእጅ ወደአፍ	ሠ. ጠፍ
	ረ. አዝረክርኮ

መጻፍ

የሚከተለውን ሠንጠረዥ መረጃ በመጠቀም የጓሮ አትክልትንና የፍራፍሬ ምርትን ልዩነት በማነፃፀር አንቀጽ ጻፉ።

የጓሮ አትክልት	ፍራፍሬ
▪ እንደጎመን፣ ቃሪያ፣ ሰላጣ፣ ቲማቲም ሽንኩርት... ያሉትን ያካትታሉ። ▪ ለምግብነት ወይም ለገበያ ቶሎ ይደርሳሉ (በወራት)። ▪ ወደገበያ ወጥተው ሲሸጡ ከፍራፍሬ አንፃር ረከስ ይላሉ። ▪ በየጊዜው መዝራትና መንከባከብ ይጠይቃሉ።	▪ እንደብርቱካን፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ፓፓያ፣ አፕል ወዘተ ያሉትን ያካትታሉ። ▪ ለምግብነት ወይም ለገበያ ለመድረስ ረጅም ጊዜ (ዓመታት) ይወስዳሉ። ▪ ወደገበያ ወጥተው ሲሸጡ ከአትክልት አንፃር ውድ ናቸው። ▪ አንዴ ከተተከሉ በኋላ የሚያስፈልጋቸው መንከባከብ ብቻ ነው።

4.3.5 ክለሳ

መጻፍ

ቅንፍን በተገቢው ቦታ በማስገበት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. በባህሉ መሠረት ቢጃማ ድርያ ለብሳ መጣች።

ለ. ተማሪዎች የተውሳከግስ ዓይነቶችን የጊዜ፣ የቦታ፣ የመጠን፣ የሁኔታ ይለያሉ።

ሐ. ሴቷ ቦለቅያ የምትሞቀው ኩርሲ አነስተኛ ወንበር ላይ ተቀምጣ ነው።

መ. በተለያየ የአየር ንብረት ቆላ፣ ደጋ፣ ወይናደጋ ባላቸው አካባበዎች የሚበቅሉ እጽዋት ችግኞችን እያፈላ ያከፋፍላል።

አቀላጥፎ ማንበብ

“አርሶአደር” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብን ተለማመዱ።

ምዕራፍ 5 ጉብኝት

5.1.1 ማዳመጥ

ቱሪዝም በኢትዮጵያ





ቅድመማዳመጥ

ሀ. ሥዕሉንና ርዕሱን ስታስተውሉ የምታዳምጡት ጽሑፍ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. በሚከተሉት ቃል/ሐረጋት ፍቺ ላይ ርስበርስ ተወያዩ።

ቱሪዝም	የቱሪስት ፍሰት
የቱሪስት መስህብ	የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ኢትዮጵያን የብሔረሰቦችና ቋንቋዎች ሙዚየም ለመባል ያበቃት ምንድን ነው?

ለ. ቱሪስቱ ወደሀገራችን በብዛት እንዲጎርፍ ያደረጉ ሀብቶቻችን የትኞቹ ናቸው?

ሐ. ባለፉት ዐምስት ዓመታት የቱሪስት ፍሰቱ እድገት ያሳየው በመቶኛ ምን ያህል ነው?

መ. በ1999 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሆቴሎች፣ የሎጂዎችና የሪዞርቶች ቁጥር ምን ያህል ነበር?

ቃላት

የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ በቃል ግለፁ።

ሚና	ቀልብ	ገፅታ	በመስኩ	ነቅሎ	አንቱታ

5.1.2 አንብቦ መረዳት

አካባቢያችንን እናስተዋውቃችሁ

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. በትምህርትቤታችሁ የሀገርህን እወቅ ክበብ አለ? ዓላማው ምንድን ነው? እናንተስ የክበቡ አባል ናችሁ? ለምን?

ለ. በሀገርህን እወቅ ጉብኝት ተሳትፋችሁ ታውቃላችሁ? ለምን?

አካባቢያችንን እናስተዋውቃችሁ

ወሩ ሰኔ እለቱ ደግሞ ቅዳሜ ነው። በትምህርትቤታችን በሀገርህን እወቅ ክበብ ሥር የተሰባሰብን የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች የዓመቱን ትምህርት መጠናቀቅ ተከትሎ አካባቢያችን ለመጎብኘት ከየቤታችን የተሰባሰብነው ጎህ ሲቀድ ነበር። ቤት ያፈራውን ስንቅ ይዘናል። የክበቡ አስተባባሪ መምህር፣ ፎቶካሜራ አዘጋጅቷል። ሁሉም ተማሪ ለጉብኝቱ አስፈላጊ የሚለውን ሁሉ ይዟል። አመቱን በሙሉ ስናስበውና ስናቅደው የነበረ ጉብኝት ስለሆነ የነበረው ደስታና ጉጉት በቃላት ሊገለጽ የሚቻል አይደለም። ሰላምታውና ወሬው ደምቋል።

“አንድ ጊዜ አዳምጡ!” አሉ መምህሩ እያጨበጨቡ፤ “ዛሬ ዓመቱን በሙሉ ስንዘጋጅበት የነበረውን ጉብኝት እናካሂዳለን። ይህ ጉብኝት መማሪያ ብቻ ሳይሆን መዝናኛም ጭምር ነው። ስለዚህ የምታዩትን ነገር ሁሉ በትኩረት ማጤንና በማስታወሻችሁ ላይ ማስፈር ይኖርባችኋል። እንግዳና መረዳት ያልቻላችሁት ነገር ሲገጥማችሁ ጥያቄ እያነሳችሁ ለመረዳት መሞከር አለባችሁ። አሁን ጉዟችን እንጀምር” ሲሉ ሁሉም ተማሪ በፍጥነት ጉዞውን ጀመረ።

ጉዟችንን ከአካባቢያችን በሰሜን አቅጣጫ ወደሚገኘው በርካታ መስህቦችን ወደያዘው ጫካ አደረግን። በግምት ሰባት ኪሎሜትር የሚረዝመውንና ውጣውረድ የበዛበትን ጉዞ ጧት አራት ሰዓት ላይ አጠናቅቀን መጎብኘት ከምንፈልገው ቦታ ደረስን። ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው። የአእዋፋትና የእንስሳት ድምፅ በብዛት ይሰማል። የአንዳንዶቻችን ልብ በፍርሃት ሳይርድ አልቀረም። ሁሉም ተማሪ አፉን ከፍቶ፣ አይኑን አፍጥጦ ቀጣይ የሚሆነውን በጉጉት ይከታተላል።

ወንዞች በጫካው ውስጥ ለውስጥ እየተንፏፉ ከዛፎችና ከድንጋዮች ጋር ሲፋጩ የሚያሰሙት ድምፅ ልዩ መግነጢሳዊ ኃይል አለው። ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች ከዛፍ ዛፍ የሚያደርጉት ዝላይ ሌላው ትርዒት ነው። ሦስት ወንዞችን ካለፍን በኋላ ግዙፍ ዋሻ ተመለከትን። የዋሻው አፈጣጠር በሁላችንም ዘንድ ግርምትን ፈጥሮብናል። እያንዳንዱ የዋሻው አካል በታዋቂ የኪነህንፃ ባለሙያ የተቀረፀ ይመስላል። ከዋሻው አናት ወደታች የሚወረወረው ፏፏቴ ከድንጋዩ ላይ ሲፈጠፈጥ ቀስተደመና ይፈጥራል።

ይህን ሁሉ እየተዟዟርን ስንመለከት ከቆየን በኋላ እረፍት ወደምናደርገበት ትንሽ ገላጣ ስፍራ አመራን። ከተመለከትነው ውስጥ ያልተረዳነውን ነገር እያነሳን ከመምህራችን ጋር በመሆን ውይይት አደረግን።

ተራ በተራ በዚህ ቦታ ፎቶ ከተነሳን በኋላ ስንቃችንን በጋራ ቀምሰን ወደቀያችን የመልስ ጉዞ ሆነ። እኔም ከቤት ደርሼ የተመለከትኩትን ሁሉ ለወላጆቼ እስክተርክላቸው ቸኩያለሁ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "አፉን ከፍቶ፣ አይኑን አፍጥጦ"፤ የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

ለ. የተማሪዎቹን ልብ ያራደው ምን ነበር?

ሐ. የታሪኩ ቦታና ጊዜ የትና መቼ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

መ. ታሪኩ የፈጠረባችሁን ስሜት እንዴት ትገልጹታላችሁ?

ሠ. ያነበባችሁትን ታሪክ በሥዕል ግለፁ።

ቃላት

የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በሌሎች በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. <u>ጎህ ሲቀድ</u> ሁላችንም ጋደም ጋደም ካልንበት እየተንጠራራን ተነሳን።

ለ. ውጣ ውረድ የበዛበት መንገድ ከፀሐይዋ ጋር ተደማምሮ ሁላችንንም አዳክሞናል።

ሐ. ተራራውን እያረፍን እየተነሳን አጠናቀን ለጥ ካለ ሜዳ ደረስን።

መ. ድንገት የአንበሳ ድምፅ ሲያስገመግም ጉልበታችን በፍርሃት ራደ።

ሠ. ከዋሻው አናት ወደታች የሚወርደው ፏፏቴ ከድንጋዩ ላይ ሲፈጠፈጥ ቀስተደመና ይፈጥራል።

መጻፍ

በሚከተሉት ቃላት የተሟላ ዓረፍተነገር ጻፉ።

ምሣሌ፦ ኤልያስና አባቱ የአባጅፋርን ቤተመንግሥት ለመጎብኘት ወደጅማ ሄዱ።

ሄዱ	ሰማን	ሠራሁ	ደረሰች	ወጡ	ተመለከትን

5.1.3 ማዳመጥ — ቱሪዝም በኢትዮጵያ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "ቱሪዝም በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በ2005 ዓ.ም ከውጪ ቱሪስት የተገኘው ዶላር ምን ያህል ነበር?

ለ. "የተለያዩ እምነት ተከታይ ሕዝቦች ድርና ማግ ሆነው የሚኖሩባት" ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች የሚባሉት እንዴት ያሉት ናቸው? ምሳሌ ስጡ?

መ. ቱሪዝምን በተመለከተ የግል ባለሃብቶችና አስጎብኚ ድርጅቶች ሚና ምን ይመስላችኋል?

ሠ. ኢትዮጵያ ከቱሪዝም መጠቀም ያለባትን ያህል ተጠቅማለች ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

አያሌ	አሻቀበ	ትጋት	ድርና ማግ

አቀላጥፎ ማንበብ

“አካባቢያችንን እናስተዋውቃችሁ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

5.1.4 አንብቦ መረዳት

ቅርሶች

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “ቅርስ” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ቅርስ በስንት ይከፈላል? በምን በምን?

ቅርሶች

“ቅርስ” የሚለው ቃል ሲጠራ በብዙዎቻችን አእምሮ ቀድሞ የሚመጣው የሚታየውና የሚዳሰሰው መስህብ ነው። ቅርስ ማለት ግን ጥንታዊ ህንጻዎችን፣ ታሪካዊ ቁሳቁሶችን፣ መጻሕፍትን፣ መዛግብቶችንና የመሳሰሉትን ብቻ ማለት አይደለም። ቅርስ እንደሃይማኖታዊና ብሔራዊ በዓላት ፌስቲቫሎች፣ ሥነቃሎችና ታሪኮች ያሉ የማይዳሰሱ ሃብቶችንም ያካትታል። የጥምቀት፣ የመውሊድ፣ የመስቀልና የአረፋ ሃይማኖታዊ በዓላት ለዚህ ምሳሌዎች ናቸው። የአድዋና የካራማራ ድሎች፣ የአሸንድዬ ፌስቲቫል፣ የአዊ ፈረሰኞች ማኅበርና የደብረታቦር የቅዱስ መርቆሬዎስ የፈረስ ጉግስ ዝግጅቶች ተጨማሪ ማሳያዎች ይሆናሉ።

ከላይ ከጠቀስናቸው ማሳያዎች በተጨማሪ በሚዳሰሱና በማይዳሰሱ ቅርሶች ሥር የሚካተቱ በርካታ የቅርስ ዓይነቶች አሉ። መስህብነት ያላቸው ወንዞች፣ ሜዳዎችና ፓርኮች ተፈጥሯዊ ቅርሶች ይባላሉ። የዘንገና ሃይቅ፣ የጢስ አባይ ፏፏቴና የጣና ሃይቅ ከዉኃማ የመስህብ አካሎች ይካተታሉ። ከፓርኮች ደግሞ የብዙ ታላላቅ ወንዞች መነሻ የሆነው ጮቄ፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የአልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ ወዘተ እንደምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ተፈጥሯዊ ቅርሶች ከሚባሉት

ደግሞ የኤርታሌ እሳተገሞራ፣ የሶፍዑመር ዋሻ፣ የጢያ ትክልድንጋይ ይጠቀሳሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሰብአዊ ቅርሶች የሚባሉም አሉ። አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ምኒልክና ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከታዋቂ መሪዎችና አርበኞች ተርታ፣ ክቡር ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌና ባለቅኔ ከበደ ሚካኤል ደግሞ ከሥነጥበብ ሰዎች የሚጠቀሱ ሰብዓዊ ቅርሶች ናቸው።

ከዚህ ሌላ ቅርሶች ባላቸው እውቅናም ይለያያሉ። ለምሳሌ የላሊበላ ውቅር አብያተክርስትያናትና የጎንደር ነገሥታት ቤተመንግሥቶች በዓለምአቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸው ቅርሶች ናቸው። ከዚህ የምንረዳው ቁምነገር ቅርሶች በአፈጣጠራቸው፣ በአይነታቸውና ባላቸው እውቅና የሚለያዩ እንደሆነ ነው።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የማይዳሰሱ ቅርሶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው? ተፈጥሯዊ ቅርሶች የሚባሉትስ?

ለ. በኢትዮጵያ በዓለምአቀፍ ቅርስነት የተመዘገቡት የሚዳሰሱ ቅርሶች ማን ማን ናቸው?

ሐ. ሰብአዊ ቅርሶች የሚባሉት ከሌሎች ቅርሶች በምን ይለያሉ?

መ. በኢትዮጵያ ከማይዳሰሱ ቅርሶች የሚመደቡትን ሃይማኖታዊ፣ ብሔራዊ በዓላትና ፌስቲቫሎች ዘርዝሩ።

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ሰብአዊ	ዘርፍ	አርበኛ	ቤተመንግሥት

ሀ. የአክሱም ሐውልት ከታሪካዊ የቅርስ _____ ይመደባል።

ለ. ደጃዝማች በላይ ዘለቀ የወራሪውን የጣሊያንን ጦር በተደጋጋሚ ድል የመቱ ኢትዮጵያዊ _____ ናቸው።

ሐ. በቋንቋ መጠቀም _____ ችሎታ ነው።

መ. የፋሲለደስ _____ በዓለምአቀፍ ቅርስነት ከተመዘገቡ ቅርሶች አንዱ ነው።

መጸፍ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሮቹን በደብተራችሁ አዘጋጁና መረጃዎቹን አሟልታችሁ ጅምሩን አንቀጽ ጨርሳችሁ ጻፉት።



ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔ አሻራ የሆኑ በርካታ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦችን የታደለች ድንቅ ምድር ናት። ከእነዚህ የቱሪስት መስህብ ሀብቶቿ መካከል ታሪካዊ ቅርሶቿ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ። ሀገሪቱ የጥንታዊ ታሪክ ባለቤት እንደመሆኗ ተቆጥረው የማያልቁ ታሪካዊ ቅርሶች ሞልተዋታል። ለአብነት ያህል የአክሱም ሐውልት፣ የፋሲለደስ ቤተመንግሥት...

5.1.5 ክለሳ

መጻፍ

ባለፈው ክፍለጊዜ የጻፋችሁትን አንቀጽ እንደገና ከልሳችሁ ጻፉ።

ቃላት

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።

ቃል	እማሬያዊ ፍቺ	ፍካሬያዊ ፍቺ
ቤት	መኖሪያ፣ መጠለያ	ትዳር፣ ኑሮ
ድንጋይ		
ጦጣ		
አሻራ		
ዛፍ		
ተራራ		

አቀላጥፎ ማንበብ

“ቅርሶች” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

5.2.1 መጻፍ

1. በሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የተወሰኑ ሐሳቦችን በመግደፍ በሦስት ነጠብጣቦች አመልክቱ።

   ምሣሌ፡- “ጅብ የማያውቁት ሀገር ሂዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ።

   “ጅብ የማያውቁት ሀገር ሄዶ...”

   ሀ. “ኹለት እግር አለኝ ተብሎ ኹለት ዛፍ አይወጣም።”

   ለ. “አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሽታለች።”

ሐ. ”በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትም።”

መ. “ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል።”

ሠ. “ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጪት።”

2. ከሚከተለው ታሪክ የተቆራረጡ ሐሳቦችን በሦስት ነጠብጣቦች አመልክቱ።

ምሣሌ፦ “ደ...ደ... ደመላሽ ተው! እንዳ...ትሳሳት! አባትህን እ...እኔ አልገደልኩትም።” አለ ዝናቡ ነጭ ላብ በግንባሩ ቆረር እያለና ሰውነቱ ወባው እንደተነሳበት ሰው እየተርገፈገፈ።

ከማድቤት ስትመለስ ስትተኩሰው የነበረው የባለቤቷ የማዕረግ የወታደራዊ ልብስ ተቃጥሎ እየጨሰ ደረሰች። ፈጣሪ ሲያጋልጣት ደግሞ በዚያችው ቅጽበት ባለቤቷ በሩን ከፍቶ ገባ።

“ምንድን ነው? ምንድን ነው የማየው?” የሚያየውን ማመን አልቻለም።

“ምን መሰለህ አስቹዬ!” አለች እየተንተባተበች።

“ምንድን ነው ያደረግሽው? ያደረግሽውን አውቀሽዋል?”

“ልብሱን እየተኮስኩ” ተንተባተበች።

“ልብሱን!” ንግግሯን ሳያስጨርሳት አንባረቀባት። “ይሄኮ ልብስ አይደለም! ይሄኮ ታሪኬ ነው! ይሄኮ ስንት ነገር ያጣሁበት” በንዴት ሳግ የሚቆራረጠውን ንግግሩን መጨረስ አልቻለም፤ በከንፈሮቹ ዳርና ዳር “ቆበሩን” እየደፈቀ ይንዘፈዘፋል።

5.2.2 አንብቦ መረዳት

ሀገር ማለት

ቅድመንባብ

ከርዕሱ በመነሳት ግጥሙ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ሀገር ማለት

አያት ቅድመአያትሽ ሰላም ሲሆን፣
ከሸዋ አድማስ ማዶ፣ ሽቅጦ ሲያቀና ወረቱን፣
ለእኔና አንቺ መኖሪያ ሲፈቅድ ቤት ንብረቱን።

ጠላት ሲደፍራትም፣ ጦሩን ሰብቆ እየፎከረ፣
ከኦሮሞው ከትግሬው፣ ከአፋር ከወላይታው፣
ከሁሉም የጦቢያ ልጆች፣ አጥንቱን እየማገረ።
ስንት አለ መሰለሽ!
ሀገር ይሉት መግባቢያ፣ ሰንደቅ ይሉት መለያ፣ ሲያቆይልሽ፣
በአንዱ ቋንቋ ብቻ የማትገልጪው በጎጥ የማትገድቢው፣
ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ፣ ውስብስብ ነው ውሉ፣
ሀገር ማለት ምስል ነው በህሊና የምታኖሪው።
ከሁሉም በላይ የኔ ልጅ፣
ተፈጥሮ ከቸረችው በረከት፣ የላቡን ፍሬ የሚበላ፣
ሀገር ማለት ወገን ነው፣ የኔ የምትዪው ከለላ።
ትመኪበት ጥሪት፣ ትደምቂበት ብርሃንሽ፣
የስብዕናሽ ግማሽ ውል፣ ወገን ነው ማህተምሽ።

[ምንጭ:- በድሉ። (2002)። ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ]

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "ከሁሉም የጦቢያ ልጆች፣ አጥንቱን እየማገረ" ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ግጥሙ በማንና ለማን የሚተረክ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

ሐ. እንደገጣሚው አባባል ሀገር ማለት ምንድን ነው?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት/ሐረግ መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

በህሊናው	ጥሪት	እየሸቀጠ	ከለላ	ሰብቆ

ሀ. አባቷ ገበያ ያፈራውን በሃቅ _____ በላቡ የሚተዳደር ሰው ነው።

ለ. አዳኙ ጦሩን _____ በኃይል ወረወረው።

ሐ. የእናቱ ምክር _____ ታትሞ ዘላለም ይኖራል።

መ. ሀገራችን ለሚሰነዘርባት ጥቃት ሁሉ _____ የሚሆኗት ጀግና ልጆች አሏት።

ሠ. ዕድሜ ልኩን ያካበተውን _____ ለልጁ አወረሳት።

መጻፍ

“ሀገር ማለት” የሚለውን ግጥም ዋና ሐሳብ አጠቃላችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

5.2.3 ሰዋስው

1. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በኃላፊ ጊዜ ቅርጽ የቀረቡትን ለይታችሁ በቅርብ ኃላፊ ቅርጽ ጻፏቸው።

   ምሣሌ፡- ቆረጡ → ቆርጠዋል

ይበላል	ሠራ	እየፈጨች	ተናገረ	ሄደ	ትመጣለች
ይመለሳሉ	እየዋኘች	እየነዳ	ቆረጡ	ጋገረች	ወቃ

2. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በቅርብ ኃላፊ ቅርጽ ጻፏቸው።

   ምሣሌ፡- ሕፃኗ ጡት <u>ጠባች</u>።

   ሕፃኗ ጡት <u>ጠብታለች</u>።

   ሀ. ታላቅ ወንድሜ <u>መጣ</u>።

   ለ. እህቴ አበቦቹን ውኃ <u>ታጠጣለች</u>።

   ሐ. በቃሉ ወደሸዋ <u>ይሄዳል</u>።

   መ. የዓመቱን ትምህርት <u>ጨረስን</u>።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ሃገር ማለት” የሚለውን ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

5.2.4 አንብቦ መረዳት

የአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት

ቅድመንባብ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ስለአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት የምታውቁትንና ማወቅ የምትፈልጉትን በመጀመሪያዎቹ ኹለት አምዶች ጻፉ፤ ሦስተኛውን አምድ ደግሞ ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ አሟሉ።

ስለአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት የማውቀው	ስለአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት ማወቅ የምፈልገው	ስለአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት ያወቅኩት

የአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት



አፄ ፋሲለደስ በ1628 ዓ.ም የሀገሪቱን መዲና ጎንደር ላይ መሠረቱ። በ1640ዎቹ መጀመሪያ ቤተመንግሥታቸውን በጎንደር ከተማ እምብርት ላይ አቆሙ። በተለምዶ ፋሲል ግምብ ተብሎ የሚጠራው የአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት በፋሲል ግቢ ውስጥ ካሉ ግምቦች የመጀመሪያውና ትልቁ ነው።

ቤተመንግሥቱ 32 ሜትር ቁመትና 2 ሜትር በ25 ሜትር የሆነ የጎንና ጎን ርዝመት አለው። ሕንፃው ባለሦስት ፎቅ (ወለል) ሲሆን 132 ደረጃዎችና 20 ክፍሎች አሉት። ቤተመንግሥቱ ከጥቁርና ቀይ ጥርብ ድንጋዮች የተሠራ ነው። ግድግዳው ለዓመታት በተቦካ ኖራ የተለሰነ ሲሆን አንድ ሜትር ተኩል ውፍረት አለው። ከቤተመንግሥቱ ጋር ተያይዘው የተሠሩ መታጠቢያቤቶች፣ የእስረኞች ማቆያና የዉኃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች አሉ።

ወደአንደኛው ፎቅ የሚያስወጡ 32 ደረጃዎች አሉ። በዚህ ወለል የእንግዳ መቀበያ፣ ማዕድ ቤቶች፣ በክረምት ጊዜ እሳት ለመሞቅ የሚያለግሉ ክፍሎች አሉ። ክፍሎቹ ውበት ባላቸው ጠንካራ የእንጨት በሮች የተከፋፈሉ ናቸው። ይህ ደረጃ

ሹማምንትና አፈቀላጤዎች አዋጆችንና ትዕዛዞችን ከንጉሡ አንደበት የሚቀበሉበት ነው። ንጉሡ ይህንን አዋጅና ትዕዛዝ የሚያስተላልፉት የአክሊል ቅርጽ ባለው ኹለተኛ ፎቅ ላይ ሆነው ነው። ከቤተመንግሥቱ ጣሪያ ላይ የንጉሡ የቅኝት ማማ ይገኛል። ጫፍ ላይ ሆኖ እስከጣና ሐይቅ ድረስ መመልከት ይቻላል።

ይህንን ታሪካዊና ዓይነግቡ ቤተመንግሥት በያመቱ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የሀገር ውስጥና የውጭ እንግዶች ይጎበኙታል።

[ምንጭ፡- ነባው መዝገብ፤ እውቀት፤ ውክፔዲያ። (2020) ገጽ 1-3]

ድኅረንባብ

የሚከተለትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በፋሲል ግቢ ውስጥ ካሉ ግምቦች የመጀመሪያውና ትልቁ ማን ይባላል?

ለ. የቤተመንግሥቱ ቁመት ምን ያህል ነው? ርዝመቱስ?

ሐ. ከቤተመንግሥቱ ጣሪያ ላይ የሚገኘው የቅኝት ማማ አገልግሎቱ ምንድን ነው?

መ. በ1628 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማን ነበረች? እንዴት አወቃችሁ?

ሠ. ከምንባቡ ያስደነቃችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን?

ቃላት

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።

ቃል	ፍቺ	
	በምንባቡ ውስጥ	ከምንባቡ ውጪ
እምብርት	መሀል	የሰውነት አካል
መዲና		
አቆመ		
አክሊል		
ቅኝት		

መጻፍ

የምታደንቁትን መዚየም፣ ጥብቅ ደን፣ ሐይቅ፣ ፏፏቴ፣ ወይም የተፈጥሮ ዋሻ አንዱን በመጎብኘት መረጃ አሰባስባችሁ የጉብኝት ዘገባ ጻፉ።

5.2.5 ክለሳ

ቃላት

በሚከተለት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡- ወንድም ጋሻ ነው።

ጋሻ	መብራት	ፈንድሻ	ቁልፍ	ርግብ	እንጀራ

ሰዋስው

የሚከተሉትን ጥንድ ዓረፍተነገሮች አጣምራችሁ በሩቅ ኃላፊ ጊዜ ቅርጽ ጻፏቸው።

ምሣሌ፡- ጀሚላ በሚገባ አጠናች። ስለዚህ ፈተናውን አለፈች።

ጀሚላ በሚገባ አጥንታ ነበር፤ ስለዚህ ፈተናውን አለፈች።

ሀ. ዮሐንስ ጉዳት ደረሰበት። ነገርግን ውድድሩን አሸነፈ።

ለ. ከዓመት በፊት ተለያዩ። ነገርግን አሁን ታርቀዋል።

ሐ. ሾፌሩ ስልጠናውን በአግባቡ አልተከታተለም። በመሆኑም ሲያሽከረክር አደጋ ደረሰበት።

መ. ርብቃ በክበቡ ውስጥ በንቃት ተሳተፈች። ስለሆነም ለክበቡ አስተባባሪነት ተመረጠች።

አቀላጥፎ ማንበብ

“የአፄ ፋሲለደስ ቤተመንግሥት” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

5.3.1 ማዳመጥ

ቱሪዝምና ተፈጥሮ

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. የቱሪዝም ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ለ. ቱሪዝም ጉዳቶች ያሉት ይመስላችኋል? ለምን?

ድኅረማዳመጥ

1. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚልታችሁ ጻፉ።



2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

   ሀ. ቱሪዝም ጪስ አልባ ኢንዱስትሪ የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

   ለ. የባህል ወረራ ምን ማለት ነው?

   ሐ. ቱሪዝም የባህል ወረራ የሚያስከትለው እንዴት ነው?

ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ተናገሩ።

ፋይዳ	በውል	አሉታዊ
አወንታዊ	ዓይነተኛ	ሊታወክ

ቅድመንባብ

የማይዳሰሱ የቱሪዝም ሀብቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

የማይዳሰሱ የቱሪዝም መስህቦች

የማይዳሰሱ መስህቦች በአካል ሊታዩና ሊዳሰሱ የማይችሉ፣ በተግባርና በእንቅስቃሴ መገንዘብ የምንችላቸው ቅርሶች ናቸው። ለምሣሌ፣ የጥምቀትና የአረፋ ሃይማኖታዊ በዓላት ዝግጅቶች፣ ሥነቃሎች፣ ቃላዊ ግጥሞች፣ አሸንድዬ፣ የጋብቻ ሥነሥርዓቶች፣ የለቅሶ ሥርዓት፣ አፈታሪኮችና፣ ተረቶች ወዘተ. ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ የማይዳሰሱ መስህቦች መካከል አንድ ተረት እንደምሳሌ እንመልከት፤

ተረት ተረት?

የመሠረት!

በድሮ ጊዜ አንድ አንበሳና ሦስት በሬዎች በጋራ የእርሻ ሥራ ጀመሩ። ብዙ ከብቶችን አረቡ። አንበሳው በሬዎቹን ገድሎ ንብረቱን በሙሉ መጠቅለል ፈለገ። ቀዩንና ጥቁሩን በሬ ጠርቶ "ሽፍቶች ብዙ ጊዜ የሚዘርፉን ነጩ በሬ በቀላሉ ስለሚታይ ስለሆነ፣ ንብረታችንንም ሆነ ራሣችንን ሳያስጨርሰን እንግደለው" አላቸው። በሀሣቡ ተስማሙ፤ ነጩ በሬ በከብት ጥበቃ ላይ እያለ ተጋግዘው ገደሉት። አንበሳውም ሬሳውን ራቅ ወዳለ ቦታ ወስዶ በላው።

ከጥቂት ቀናት በኋላም አንበሳው ቀዩን በሬ ጠርቶ "ሰብላችንን ማታ በጨለማ የሚበላብን ጥቁሩ በሬ ነው፤ እሱን ካልገደልን ሰብላችን ሁሉ መውደሙ ነው" አለው። ቀዩ በሬም በጣም ስለተናደደ "ይህን የሚያደርግ ከሆነማ እንግደለው" አለ። በስምምነታቸው መሠረትም ጥቁሩን በሬ ገደሉት። አንበሳውም ብቻውን የቀረውን አንድ በሬ ከመጤፍ አልቆጠረውም። ትእቢት ልቡን ነፋው። በማግስቱ ከከብቶች የሰባውን እየመረጠ መብላት ጀመረ።

ቀዩ በሬም የከብቶቹን መጥፋት ለአንበሳው ሲነግረው ከትከት ብሎ እየሣቀ "አሁን አሁን ዝም ብሎ ርሀብ ርሀብ ይለኛል፤ በዚህ ምክንያት እኔ ነኝ የበላኋቸው" ብሎ በንቀት መለሰለት። ቀዩ በሬ ይህንን ሲሰማ በጣም ፈራ፤ አንበሳው ለምን እንደከፋፈላቸው አሁን ገባው። በትህትና "ለምን ሳታማክረኝ ትበላለህ አያ አንበሳ?" ሲል ጠየቀው። "አንተስ ብትሆን የኔ አይደለህ፤ አሁን ማን ይደርስልሃል?" ብሎ አንጀቱን ዘርግፎ ገደለው።

ተረቱን መልሱ ----- አፌን በዳቦ አብሱ።

ድኅረንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

   ሀ. የማይዳሰሱ የቱሪዝም ሀብቶች የሚባሉት እንዴት ያሉት ናቸው? በምሳሌ አስደግፋችሁ አብራሩ።

   ለ. በታሪኩ ውስጥ ያስደሰታችሁ ወይም ያሳዘናችሁ ወይም ያናደዳችሁ የትኛው ነው? ለምን?

   ሐ. ከታሪኩ ምን ተማራችሁ?

2. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ስለታሪኩ ድርጊቶች በቅደምተከተል ጻፉ።



ቃላት

የተሰመረባቸውን በተመሳሳይ ቃላት ተክታችሁ ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. ዕድሜ ልኩን ለፍቶ ያካበተውን ንብረት በደቂቃዎች ውስጥ በእሳት አደጋ አጣ።

ለ. አንበሳው፣ በሬዎቹን ገድሎ ንብረቱን በሙሉ መጠቅለል ፈለገ።

ሐ. እዚህ ጫካ ውስጥ በርካቶች ገንዘባቸውን በሸፍታዎች ተዘርፈዋል።

መ. ሰውየው ማስጠንቀቂያውን ከመጤፍ አልቆጠረውም።

ሠ. የፈለገውን ከማድረግ ማንም እንደማያግደው ሲያውቅ ትእቢት ልቡን ወጠረው።

5.3.3 ማዳመጥ

ቱሪዝምና ተፈጥሮ

ቅድመማዳመጥ

“ቱሪዝምና ተፈጥሮ” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ኹለት ተቃራኒ አቋሞች መነሻ በማድረግ በምክንያት ተከራከሩ።

ቱሪዝም ከአሉታዊ ተጽዕኖዎቹ ይልቅ አወንታዊ ተጽዕኖዎቹ ይበልጣሉ።

ቱሪዝም ከአወንታዊ ተጽዕኖዎቹ ይልቅ አሉታዊ ተጽዕኖዎቹ ይበልጣሉ።

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

አወንታዊ	ዘላቂ	ግዙፍ
ሊሰደዱ	እንዲለመ·	

አቀላጥፎ ማንበብ

“የማይዳሰሱ የቱሪዝም መስህቦች” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

5.3.4 አንብቦ መረዳት

የቱሪዝምን ጥቅም የበለጠ ማሳደግ

ቅድመንባብ

ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ የሆነች ይመስላችኋል? እንዴት?

የቱሪዝምን ጥቅም የበለጠ ማሳደግ

ኢትዮጵያ ባላት እምቅ የቱሪስት መስህብ ብዛትና ዓይነት ልክ የሚገባትን ጥቅም ማግኘት ትችል ዘንድ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ተግባራት በጥራትና በፍጥነት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

መስህቦችን በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለሀገር ውስጥና ለዓለምአቀፍ ጎብኝዎች ማስተዋወቅ፣ ለቅርሶች አስፈላጊውን ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግና ወደመስህብ መገኛዎች የሚያደርሱ መንገዶችን ግንባታ በጥራት ማከናወን ይገባል። በዘርፉ የሚሰማራው የሰው ኃይል ዘመኑን የሚመጥን ስልጠና እንዲያገኝ ማድረግም ያስፈልጋል።

መልክአምድራዊ ስምሙነት ያላቸው ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ማሰናዳት ዓብይ ጉዳይ ነው። ቱሪስቶች ምቾት እንዲያገኙ በማድረግ የሀገር ውስጥ ጉብኝት የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎችንና ሎጆችን በመገንባት ለአገልግሎት ማብቃት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሌላው ተጨማሪ ተግባር ነው።

እነዚህ ከፍተኛ መዋዕለንዋይ፣ እውቀት፣ ጊዜና ጉልበት የሚጠይቁ ሥራዎች በመንግሥት ብቻ ሊፈፀሙ አይችሉም። ስለሆነም የግል ዘርፉን በማነቃቃት ወደሥራ ማስገባትና ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ማድረግ ይጠበቃል።

[ምንጭ:- አብክመ ቱሪዝም። (2010 ዓ.ም)። ገጽ 25፤ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ኢትዮጵያን ከቱሪዝም ዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው?

ለ. "መልክዓምድራዊ ስምሙነት ያላቸው"፤ ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ማድረግ ያለባቸው እነማን ናቸው? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

እምቅ	ምቾት	ሊታለፍ	ባለድርሻ አካላት	ማብቃት

መጻፍ

አንድ የምታውቁትን ተረት ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

5.3.5 ክለሳ

መጻፍ

ከሚከተሉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ላይ ሐሳብ እያጎደላችሁ በሦስት ነጠብጣቦች አመልክቱ።

ሀ. “ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ።”

ለ. “በሬ ግዙ ግዙ አንድ አሞሌ ላያግዙ።”

ሐ. “የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ።”

መ. “ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ።”

ሠ. “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው።”

ቃላት

ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟሉና በቃላቱ ፍካሬያዊ ፍቺ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ቃላት	እማሬያዊ ፍቺ	ፍካሬያዊ ፍቺ
መሬት		
ጉሮሮ		
አንበሳ		
ክብት		
ጨለማ		

አቀላጥፎ ማንበብ

“የቱሪዝምን ጥቅም የበለጠ ማሳደግ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 6

ፀረሱስ

6.1.1 ማዳመጥ

የሱስ ተጽዕኖ

ቅድመማዳመጥ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ስለሱስ የምታውቁትንና ማወቅ የምትፈልጉትን በአንደኛውና በኹለተኛው አምዶች ጻፉ፤ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ደግሞ ያወቃችሁትን በሦስተኛው አምድ ጻፉ።

ስለሱስ የማውቀው	ስለሱስ ማወቅ የምፈልገው	ስለሱስ ያወቅኩት

ድኅረማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

   ሀ. ወጣቶች ወደሱስ የሚገቡት እንዴትና ለምን ይመስላችኋል?

   ለ. በአካባቢያችሁ ወጣቶችን ለሱሰኝነት የሚዳርጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ መልሱ።

1. አንድ ሰው ሱስ ይዞታል የሚባለው ምን ሲሆን ነው?

ሀ. እፁን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወስድ

ለ. ያለእፁ ሕይወቱን መምራት ሲያቅተው

ሐ. መዝናናት ባሰኘው ጊዜ እፁን ሲጠቀም

መ. እፁን መጠቀም ማቆም የማይችልበት ደረጃ ሲደርስ

2. ስላዳመጣችሁት ምንባብ አወቃቀር ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ምሳሌያዊ ሐ. ማወዳደር

ለ. ሂደታዊ መ. ምክንያትና ውጤት

3. የጽሑፉ ዋና ሐሳብ ምንድን ነው?

ሀ. የአዕምሮ በሽታ መንስኤዎች

ለ. ለሱሰኝነት የሚያጋልጡ መንስኤዎች

ሐ. የሱሰኝነት ጉዳቶች

መ. በወጣቶች ትምህርት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ችግሮች

ቃላት

ለተሰመረባቸው አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ጀብደኛ ሰዎች ክብርን <u>ለመጎናፀፍ</u> ሲሉ የማያደርጉት የለም።

ለ. ልዕልት ያሰበችውን ለማሳካት <u>ሲሳናት</u> እልህ ይይዛታል።

ሐ. ሱስና አደንዛዥ እፅ የተላላፊ በሽታዎችን <u>ስርጭት</u> ያባብሳሉ።

መ. በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች ራሳቸውን ለመቀየር ያላቸው መነሳሳት <u>ይኮላሻል</u>።

ሠ. ወጣቶች በደምሥር <u>የሚወስዷቸው</u> አደንዛዥ እፆች ለጤና በጣም አደገኛ ናቸው።

ቅድመንባብ

ሱስ በቤተሰብ ውስጥ ምን ዓይነት ችግር የሚያስከትል ይመስላችኋል?

ቤተሰብና ሱስ

አቶ አልታየና ወይዘሮ ወርቅነሽ በትዳር ተጣምረው ባንድ ጎጆ መኖር ከጀመሩ የፊታችን መስከረም ሰላሳ ዓመት ይሞላቸዋል። የአብራካቸው ክፋይ የሆኑ ሦስት ልጆች አሏቸው። በሰላሳ ዓመት የትዳር ሕይወታቸው ከአነስተኛ አለመግባባቶች ውጪ፣ ፀሐይ የሞቀው ግጭት በመካከላቸው ተፈጥሮ አያውቅም። "አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ" ተባብለው በመረዳዳት ኖረዋል። የመጀመሪያ ልጃቸው ገበያነሽ አልታየ ከአንድ ወር በኋላ በመጀመሪያ ዲግሪ ትመረቃለች። ኹለቱ ወንዶች ልጆቻቸው ደግሞ የኹለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው። አቶ አልታየ በባሕር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የቀለም ክፍል ባለሙያ ሲሆኑ፣ ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩትም ከፋብሪካው በሚያገኙት ደመወዝ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአቶ አልታየ ባህርይ መለዋወጥ ጀምሯል። አምሽቶ መግባት፣ መስከር፣ ምግብ ሲቀርብላቸው አቃቂር በማውጣት ማዕዱን መግፋት የሚታዩባቸው እንግዳ ባህርይ ሆነዋል። ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋር ቁጭ ብሎ የመጨዋወት ልምዳቸውን ውኃ በልቶታል። ጎረምሳ ልጆቻቸውን እየሰጉ ነው እንጂ በባለቤታቸው ላይ ዱላ ለመሰንዘርም ይዳዳቸው ጀምሯል።

በተለይም ደመወዝ በተቀበሉ ሰሞን ወደቤት ሳይመለሱ በዚያው የሚያድሩባቸው ቀኖችም አሉ። ለቤተሰባቸው የወር ወጪ መስጠት አቁመዋል። በዚህ ምክንያት ቤተሰቡ ለችግር ተጋለጠ። ችግሩ እየባሰ ሲመጣ ወይዘሮ ወርቅነሽ ከልጆቻቸው ጋር መከሩ። የት ቦታ ምን ሲያደርጉ እንደሚያመሹ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ጀመሩ። በእሳቸው ዕድሜ ላሉ ሰዎች በማይመጥን መጠጥቤት ትዳራቸውን ከፈቱ የሠፈሩ አዛውንት ጋር ሆነው አገኟቸው። እናትና ልጆች በጣም አዘኑ። ወይዘሮ ወርቅነሽ የትዳር አጋራቸውን፣ ልጆች ደግሞ አባታቸውን ከጀመሩት አጉል ሱስ ለመመለስ ቆረጡ።

በአንደኛው ቀን ወይዘሮ ወርቅነሽና ልጆቻቸው፣ አቶ አልታየ ከሚጠጡበት ቤት ገብተው መጠጥ አዘዙ። በአንደኛው ማዕዘን የተቀመጡት አቶ አልታየ የሚያዩትን ማመን አቃታቸው። የጨበጡትን ጠርሙስ ለመወርወርም ቃጣቸው። በደም ፍላት

አይሉት በድንጋጤ ሰውነታቸው እየራደ መጠጥቤቱን ለቅቀው ወደቤታቸው ከነፉ። እነወይዘሮ ወርቅነሽም አምሽተው የሰከሩ መስለው እየተወላገዱ ወደቤት ሲገቡ አቶ አልታየ እንደእንጨት ደርቀው ይመለከቷቸው ነበር። ሁሉም ወደአልጋቸው አመሩ። አቶ አልታየ እስከሌሊቱ አጋማሽ በዓይናቸው እንቅልፍ አልዞረም። የሆነውን ሁሉ ሲያስቡት ዘገነናቸው። ጥፋታቸው ገብቷቸዋል።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ" ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በእናትና በልጅ ውሳኔና ድርጊት ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. እናንተ የአቶ አልታየ ልጅ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

መ. አቶ አልታየ ወደፊት የተለየ ባህርይ የሚያሳዩ ይመስላችኋል? ለምን?

ቃላት

የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

የአብራክ ክፋይ	አቃቂር ማውጣት	በደም ፍላት	ውኃ በልቶታል
ከነፉ	መከሩ	ፀሐይ የሞቀው	

መጻፍ

"ቤተሰብና ሱስ" ከሚለው ምንባብ ከሦስተኛው አንቀጽ በኋላ ያለውን የታሪክ ክፍል በራሳችሁ አገላለጽ በሹለት አንቀጽ ጨርሱት።

6.1.3 ማዳመጥ — የሱስ ተጽዕኖ

ቅድመማዳመጥ

"የሱስ ተጽዕኖ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ

ድኅረማዳመጥ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።



ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ያሉትን ከ"ለ" ክፍል ጋር በማጣመር በምሳሌው መሠረት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ



“ሀ”	“ለ”
1. ድብርት	ሀ. ጥገኛ
2. አደንዛዥ እጽ	ለ. የጤና እክል
3. ሱሰኛነት	ሐ. መጻኢ ዕድል
4. መገለል	መ. ይሸማቀቃሉ
5. ተላላፊ በሽታዎች	ሠ. ህልፈት

አቀላጥፎ ማንበብ

“ቤተሰብና ሱስ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

6.1.4 አንብቦ መረዳት

ቤተሰብና ሱስ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ቤተሰብና ሱስ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።



ለ. በቢጋሩ ስላሰፈራችኋቸው መረጃዎች ተናገሩ።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት በእማሬያዊና በፍካሬያዊ ፍቻቸው ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ

አዲሱ ቤታችን ቀለም ተቀባ።

የወይዘሮ ሸዋዬ ልጅ የቀለም ነገር ይሆንለታል።

ዶሮ	ቀለም	አልጋ	ጎጆ	ዐይን	እናት

መጻፍ

ስለሱሰኞች የምታውቁትን፣ የሰማችሁትን ወይም ያነበባችሁትን ታሪክ በሹለት አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

6.1.5 ክለሳ

መጻፍ

ድርብ ሠረዝንና ነጠላ ሠረዝን በመጠቀም ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. በእናቱም ያዝናል _____ ማንን መውቀስ እንዳለበት አያውቅም _____ በውስጡ የአባት ፍቅር አድሮበታል።

ለ. መኳንንት ከአዲስ አበባ ሲመለስ ለእናቱ _____ ጥበብ ቀሚስ _____ ነጭ ሻሽና ጥለቱ ያማረ ኩታ _____ ለአባቱ _____ ካፖርት _____ ኮፍያ _____ ጫማና ከዘራ _____ ለባለቤቱ _____ አዲስ ፋሽን ቀሚስ ----- የአንገት ሀብልና ባለረጅም ተረከዝ ጫማ ገዛላቸው።

ሐ. ኃይሉ ያቺ የሚገረፍባት አለንጋ ትዝ አለችው _____ ለዚያች አለንጋ ጀርባውን ሲሰጥ ታየው።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ፀሐይ የሞቀው	ተጎናፀፈች	ተሳነው	የአብራክ ክፋይ	መገለል

6.2.1 ማዳመጥ

ከሱስ ነጻ መውጫ መንገዶች

ቅድመማዳመጥ

በሱስ የተያዙ ሰዎች ከሱሳቸው መላቀቅ ይችላሉ፤ ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ራሳችንን ለማወቅ ራሳችንን መጠየቅ የሚገባን ጥያቄዎች ምን ምን ናቸው?

ለ. ከሱስ ነፃ መሆን ምን ምን ጠቀሜታዎች አሉት?

ሐ. ትክክለኛ ጓደኛ መምረጥ ከሱስኝነት ለመራቅ እንዴት ይረዳል?

መ. የምንባቡ ዋና ሐሳብ ምንድን ነው?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ተቃራኒ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ነፃ መውጣት	ሀ. ራስን አለመቆጣጠር
2. መወሰን	ለ. ይከላከላሉ
3. ራስን መምራት	ሐ. የሚናቁ
4. ያጋልጣሉ	መ. መወላወል
5. የሚከበሩ	ሠ. ጥገኛ መሆን

ሰዋስው

የሚከተሉትን ተውላጠስሞች በመጠቀም የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

እኔ	አንቺ	እነሡ	እሱ	እኛ	እሷ

6.2.2 አንብቦ መረዳት

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ራዕይ ምንድን ነው?

ለ. ራዕይ አለኝ ማለት ምን ማለት ነው?

ራዕይ አለኝ



ዛሬ ተማሪ ነኝ ራዕይ ያለኝ ዜጋ፣
ደከመኝን የማላውቅ እውቀትን ፍለጋ፣
ለውጪ ሃገሬ የምከፍለው ዋጋ።
ጠንክሬ ጠጥቼ የእውቀትን ጅረት፣
ላወጣ ወገኔን ከችግር ድህነት ።
እኔ አዲስ ተክል ነኝ ፍሬ የማፈራ፤
ራሴን የማሰልፍ ከጎበዞች ተራ።

የሱሰኛን ፈረስ ጉልበቱን ሰብሬ፤
እታያለሁ ነገ በሥራ ጠንክሬ።
በጥሩ ሥራና በተሻለ ውጤት፣
ወላጅ ወገኖቼን ሁሉን ለማስደሰት፣
ሐሳብ ሰውነቴን ከሱስ ተራ አርቄ፣
እታያለሁ ነገ ፈክቼ ደምቄ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የገጣሚው (የገጣሚዋ) ራዕይ ምንድን ነው? እንዴት አወቃችሁ?

ለ. “አዲስ ተክል ነኝ” ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. ግጥሙ በማን የሚተረክ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

መ. የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

ሠ. ግጥሙ ለምን ዓላማ የተጻፈ ይመስላችኋል? እንዴት አውቃችሁ?

ቃላት

መምህራችሁ ሰሌዳ ላይ ቃላት ይጽፉላችኋል። ቡድኑን ወክለው ፊት ለፊት ለተቀመጡት ለቡድን ጓደኞቻችሁ የቃላቱን ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ በመናገር፣ በሥዕል ወይም በድርጊት በማሳየት የቃላቱን ፍቺ እንዲገምቱ አድርጉ።

መጻፍ

"ራዕይ አለኝ" የሚለውን ግጥም ዋና ሐሳብ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

6.2.3 ማዳመጥ

ከሱስ ነጻ መውጫ መንገዶች

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "ከሱስ ነፃ መውጫ መንገዶች" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ በማስታወስ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉና ንግግር አቅርቡ።

ከሱሰኝነት ነጻ መውጫ መንገዶች					
ራስን ማወቅ					
-	-	-	-	-	-

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ለመላቀቅ የተጠመዱ ይገፋፏቸዋል ራሳቸውን ማወቅ እንቅፋት

ሀ. ሱሰኝነት በሕይወታችን አጥብቀን የምንመኘውን እንዳናሳካ _____ ይሆናል።

ለ. በሱስ _____ ወጣቶች ከገቡበት ሱስ _____ በመጀመሪያ _____ ይኖርባቸዋል።

ሐ. በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች ያሉበት የሱሰኝነት ባህርይ ትክክል ስለሚመስላቸው ሌሎች ጓደኞቻቸውን ወደሱስ እንዲገቡ _____።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ራዕይ አለኝ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

6.2.4 አንብቦ መረዳት

ራዕይ አለኝ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ራዕይ አለኝ“ በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ግጥም ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “የሱሰኛን ፈረስ ጉልበቱን ሰብሬ” ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. ገጣሚው ስለሱስ ያለው አመለካከት ምንድን ነው? እንዴት አወቃችሁ?

ሐ. በግጥሙ ሊተላለፍ በተፈለገው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

መ. በመስመር 10፣ 11፣ 12 እና 13 ላይ የተላለፈው መልዕክት ማንን የሚመለከት ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

ሠ. የእናንተ ራዕይ ምንድን ነው?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ዋጋ	በተሻለ	ደምቄ	ፍሬ	ራዕይ

ሀ. ዓመትበዓል ስለሆነ በሀገር ባህል ልብስ _____ ወደአያቱ ቤት ሄድኩ።

ለ. የእኔ _____ ትውልድን የሚቀርጽ ጥሩ መምህር መሆን ነው።

ሐ. እናትና አባቱን _____ ውጤት ለማስደሰት ትምህርቱን ጠንክሮ መማር ጀምሯል።

መ. ዛሬ ያላግባብ የምናባክነው ጊዜ ነገ _____ ያስከፍለናል።

ሠ. ጠንክሮ የተማረ የኋላ ኋላ _____ ማፍራቱ አይቀርም።

መጻፍ

ስንኞቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. እህል ዉኃ አይሆን ሰውን አይጠግን፣

_____

ለ. አዕምሮን አፍዝዞ ጤናን የሚጎዳ፣

_____

ሐ. ወንድም እህቶቹ እኔ ልምከራችሁ፣

_____

6.2.5 ክለሳ

ሰዋስው

ከሚከተሉት ቃላት መካከል ተውላጠስም በሆኑት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሣሌ፡- ያ ልጅ ጓደኛዬ ነው።

ያ	እነዚህ	እኛ	አንቺ	እኔ	ይህች	እነዚያ	እናንተ	ይህ

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

አርቂ	ዜጋ	ፍለጋ	የማላውቅ	ሰብሬ	ላወጣ

6.3.1 ማዳመጥ — ጫትና መዘዙ

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሰዎች ጫት የሚቅሙት ለምን ይመስላችኋል? ትስማማላችሁ?

ለ. የአካባቢያችሁ ጎብረተሰብ ስለጫት ያለውን አመለካከት ግለጹ።

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በጫት ውስጥ የሚገኘው በአንጎልና ነርቭ ላይ ተፅእኖ የሚያደርሰው ንጥረነገር ምን ይባላል?

ለ. ጫት የሚያስከትላቸውን የጤና ጉዳቶች ዘርዝሩ?

ሐ. ጫት ትውልድ ገዳይ የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

መ. ፀሐፊው "ሰድዶ ማሳደድ" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

ሠ. ጫት ከጥቅሙና ከጉዳቱ የትኛው ይበልጣል? ለምን?

ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍቺ ተናገሩ።

ሀ. ጫት ለምለም ቅጠሉ ወይም <u>ቀንበጡ</u> እየተቀነጠሰ በመቃም ጥቅም ላይ ይውላል።

ለ. ኹለቱ <u>ንጥረነገሮች</u> (ቅመሞች) የአንጎልንና የጀርባ አጥንትን መዋቅር ያነቃቃሉ።

ሐ. ጫት በማንኛውም ሁኔታ ስሜት <u>አነሳሽ</u> ነው።

መ. ሰዎች ጫት ሲቅሙ ለጊዜው ከገጠማቸው <u>የድብርት</u> ወይም የመጫጫን ስሜት ወጥተው ደስታ ሊያገኙ ይችላሉ።

ሠ. ጫት ከሚያስከትላቸው የጤና ችግሮች አንዱ የጨጓራ <u>መቆጣት</u> ነው።

ሰዋስው

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና በምሳሌው መሠረት አመልክቱ።

መጠይቅ ተውላጠስም	ለሰው	ለነገር	ለቦታ	ለጊዜ	ለሁኔታ	ለምክንያት
ማን	✓					
ምን						
ወዴት						
መቼ						
እንዴት						
ለምን						

6.3.2 አንብቦ መረዳት

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ሰዎች ቡናን የሚጠጡት ለምን ይመስላችኋል?

ለ. የቡና ባህላዊ ሥርዓታችን ምን ጠቀሜታ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ? ጉዳቱስ?

ሐ. "የቡና ባህላዊ ሥርዓታችን" የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ስለቃላቱ ፍቺ ግምታችሁን በሹለተኛው ዓምድ ጻፉ።

ቃል	የተገመተ ፍቺ	ከንባብ በኋላ	ፍንጭ ሰጪ ቃል/ሐረግ
ለመትለም			
ተጓዳኝ			
አሉባልታ			
አስታኮ			
መታረም			

የቡና ባህላዊ ሥርዓታችን



የቡና አፈላልና አቀራረብ ሥርዓታችን ጊዜና ዘመናዊነት ያልከለሰው የእንግዳ ተቀባይነታችን መገለጫ፣ የምንኮራበት ባህላችን ነው። በትልልቅ ሆቴሎችና የግብዣ ቦታዎች ላይም ይህ ባህላዊ የቡና ሥርዓት እንግዶችን ለመቀበል በሠፊው ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። ይህም የቡና ባህላዊ ሥርዓቱ ዓለማቀፋዊ እውቅና እንዲያገኝ አድርጓል።

በስፋት ቡናን በመጠቀማችን የተነሳም ከሚመረተው ቡና ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውለው ከፍተኛ መጠን እንደሚኖረው መገመት አያዳግትም። ቡና መዝናኛና ጊዜ ማሳለፊያ ብቻ አይደለም። ቡና አፍልቶ ሰዎችን "ቡና ጠጡ" ብሎ መሰባሰብ ማኅበራዊ ኑሮን ያጠናክራል፤ ለትብብርና ለመተጋገዝ ያነሳሳል፤ ለችግሮች የጋራ መፍትሄ ለመስጠትና ቀጣይ እቅዶችን ለመትለም ጠቃሚ ነው።

ቡና የደከመን ሰውነትና አእምሮን በማነቃቃት ሥራን በቅልጥፍና ለመሥራት የሚረዳውን ያህል፣ መጠን ሲታለፍ ጉዳት እንደሚያስከትልም መገንዘብ ይገባል።

ቡናን በብዛት የመጠጣት ተጓዳኝ ችግሮችን ብዙዎች አይገነዘቡትም። እንደቡና ጠጪው የሰውነት ጥንካሬና የመቋቋም ችሎታ ቢለያይም ከመጠን ያለፈ አጠቃቀም የጎንዮሽ ጉዳቶች ይኖሩታል። በውስጡ ያለውን "ካፌን" የተባለውን ቅመም በከፍተኛ መጠን መጠቀም ጭንቀትንና የእንቅልፍ እጦትን ያስከትላል። ያለመጠን መጠቀሙ እየቆየ ሲሄድ ከባድ ችግሮች ሊያስከትል እንደሚችል መታመን ይኖርበታል።

ከዚህ ሌላ በቡና አፈላልና አቀራረብ ባህላዊ ሥርዓታችን ላይ የሚታዩና ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ። በሰበብ አስባቡ ስኒ መደርደርና በአሉባልታ፣ በሃሜትና በወሬ ጊዜን ማባከን አንዱ ችግር ነው። በተጨማሪም በቡናው ሥርዓት አስታከው የሚፈፀሙ አጉል እምነቶች፣ አምልኮና የጥንቆላ ድርጊቶች መታረም የሚገባቸው ናቸው። የቡናን ጥቅም እያገኙ ጉዳቱን ለማስወገድ የቡና ባህላዊ ሥርዓታችንን ማስተካከል ይገባል።

[ምንጭ፡- አዲስ ሕይወት። (1980)። ገጽ 25-26]

ድህረንባብ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በምንባቡ መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።



ቃላት

በቅድመንባብ ስለቀረቡት ቃላት ፍቺ እንደገና አስቡ። የመጀመሪያው ግምታችሁ ትክክል ከሆነ ይህን "✓" ምልክት በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ አስፍሩ። ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ግምታችሁን ከቀየራችሁ ደግሞ አዲሱን ፍቺ በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ ጻፉ። የቃሉን ፍቺ ለመረዳት ያገዛችሁን ቃል በመለየት በአራተኛው ዓምድ ውስጥ ጻፉ።

መጻፍ

ስለባህላዊ የቡና ሥርዓት ያሚላችሁትን የሐሳብ ማደራጃ ቢጋር በመጠቀም አጭር አንቀጽ ጻፉ፡

6.3.3 ማዳመጥ — ጫትና መዘዙ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "ጫትና መዘዙ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚሉና ንግግር አቅርቡ።



ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ጻፉ።

አፍላጉልበት	ሥርሰደደ	ቀነጠሰ
የሱስ ተገዥ	መግታት	ማኘክ

6.3.4 አንብቦ መረዳት

የቡና ባህላዊ ሥርዓታችን

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “የቡና ባህላዊ ሥርዓታችን” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ደጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የቡና ሥርዓታችን የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

ለ. የቡና ሥርዓታችን በተመለከተ ሊስተካከሉ ስለሚገባቸው ልማዶች ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. ከቡና ባህላዊ ሥርዓታችን የምትወዱትና የምትጠሉት ነገር ምንድን ነው? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ተቃራኒ ፍቺ ጻፉ።

አያዳግትም	እጦት	ተከታይ	በቅልጥፍና	ያልተከለሰ

መጻፍ

በአካባቢያችሁ ሱስ በወጣቶች ላይ እያደረሰ ስላለው ጉዳት በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

6.3.5 ክለሳ

ሰዋስው

በሚከተሉት መጠይቃዊ ተውላጠስምች የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሣሌ፡- የትምህርትቤታችሁ ርዕሰ መምህር ማን ነው/ናት?

ማን	የት	እንዴት	ምን	መቼ	ለምን

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሣሌ፡- ነገ = ተስፋ (ፍካሬያዊ ፍቺ)

ምንም ዓይነት ሁኔታ ነገዬን እንዲያጨልምብኝ አልፈቅድም።

ልብ	ቅመም	አጫሽ	ቅጠል	ነገ	ወጋግራ

አቀላጥፎ ማንበብ

“የቡና ባህላዊ ሥርዓታችን” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 7 የጥላቻ ንግግር

7.1.1 ማዳመጥ

የጥላቻ ንግግር

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. ጥላቻ ምንድን ነው?

ሐ. ከጓደኞችሁ ጋር ተጣልታችሁ ታውቃላችሁ? በምን ምክንያት?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. የጥላቻ ንግግር ምንድን ነው?

ለ. ጥላቻ ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትለው እንዴት ነው?

ሐ. በዘር ፍጅት ተጠቃሽ የምትሆነው ሀገር ማን ናት?

መ. ዩጎዝላቪያ ወደትንንሽ ሀገራት የተበጣጠሰችው በምን ምክንያት ነው?

ሠ. በኃይማኖት ጥላቻ ምክንያት የተከሰተው ምንድን ነው?

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ተመሣሣይ ፍቺ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፦ የተዛነፈ - የተዛባ

ስለሌሎች ሰዎች ያለን <u>የተዛባ</u> አመለካከት ለግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል።

የተዛነፈ	ሰለባ	ዘግናኝ	ፍጅት

ዘር አይመረጥም

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ዘር አይመረጥም ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ሰዎች ማንነታቸውን መርጠው የሚወለዱ ይመስላችኋል? ለምን?

ዘር አይመረጥም

አቶ መሐመድና ወይዘሮ ዘይነብ ትውልዳቸው በአንድ ትንሽ የገጠር መንደር ውስጥ ነው። በዚሁ አካባቢ ትዳር መሥርተው ለዐምስት ዓመታት በአንድ ጣራ ሥር ኖረዋል። በዚሁ የትዳር ዘመናቸው በመደጋገፍ እየኖሩ እያለ ያላሰቡት ድርቅና ርሀብ ዱብዳ ወረደባቸው። ሰማይ የልግስና ጠሉን ነፈገ። ምድርም በረከቷን መስጠት አቆመች። ከብቶች ይግጡት ጨሌ፣ ይጎነጩት ጠብታ ዉኃ ጠፋ። ከእጅ ወደአፍ ከሆነው ግብርናቸው ያጠራቀሙት ትንሽ እህል ቀስ በቀስ ተመናመነ።

የአካባቢው ሰው አንዳንድ እያለ ቀዬውን ለቆ በመሄዱ፣ ጎረቤቶቻቸውና ዘመዶቻቸው በአካባቢው የሉም። አቶ መሐመድም ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ዘይነብ ጋር በመምከር በርሀብ ከማለቃቸው በፊት የተረፈቻቸውን እህል ስንቅ ቋጥረው፣ ሕፃን ልጃቸውን ይዘው ወደሌላ የኢትዮጵያ አካባቢ በመሄድ በመረጡት ቀበሌ ጎጆ ቀልሰው መኖር ጀመሩ።

በቀበሌው 30 ዓመታት ኖረዋል። በትውልድ አካባቢያቸው ሳሉ ከወለዷት ጦይባ በተጨማሪ አራት ልጆችን ወልደዋል። ሀብት ንብረትም አፍርተዋል። የመጀመሪያ ልጃቸው ጦይባ በአካባቢው ተወላጅ የሆነውን መንሱርን አግብታ ኹለት ልጆችን ወልዳለች። በትዳሯም ደስተኛ ናት። ባሏም ከነፍሱ አስበልጦ ይወዳታል። ጦይባ የባሏን፣ መንሱር ደግሞ የሚስቱን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አቀላጥፈው ይናገራሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአካባቢው ሰላም መደፍረስ ጀምሯል። የቀየው ሰውም ጭንቀት ውስጥ ገብቷል። በውጭ አገራት የሚሰሙት የዘር ፖለቲካና የጥላቻ ንግግር በአካባቢያቸው ማንጎበብ ጀምሯል። ጥቂት ሳይቆይ ቤት ለቤትና በአደባባይ ማንነትንና ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር ዘመቻ ተጧጧፈ። ቀጥሎም "አካባቢያችንን ልቀቁ" የሚል ዛቻና ማስፈራሪያ ተከተለ።

ይህንን በጥሞና ያስተዋለው የአካባቢው ማኅበረሰብ በጉዳዩ ላይ ለመምከር ቀጠሮ ያዘ። የአቶ መሐመድ ቤተሰብም የምክሩ አካል ነበር። "አብረን ተዛምደን ዘመናትን

የተሻገርን የአንድ ሀገር ሰዎች ነን። ከሞት በስተቀር ሊለያየን የሚችል አንዳች ኃይል የለም። ማንም ከዚህኛው ዘር በዚህ ቦታ ልወለድ ብሎ መርጦ የተወለደ የለም። ዘር አይመረጥም፤ ሁላችንም ሰዎች ነን። ስለሆነም ጠላት በመካከላችን ገብቶ እንዲለያየን ከቶውንም ዕድል አንሰጠውም። በተባበረ ክንዳችን የጠላትን ሴራ እንመክታለን" የመጨረሻ መሃላቸው ነበር።

ጥላቻ የተጠናወተው ቡድን አካባቢውን የጥላቻ ዘር መዝሪያ ምቹ ማሳ ሊያደርገው ደጋግሞ ሞከረ፤ አልቻለም። በጎብረተሰቡ የተባበረ ክንድ አካባቢው እስከዛሬ ድረስ ልዩ ልዩ ጫናዎችን ተቋቁሞ ሰዎች ያለ ልዩነት በመከባበር፣ በመረዳዳት፣ በመቻቻልና በሰላም መኖር የሚችሉበት ሥፍራ ሆኗል።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "የጥላቻ ዘር መዝሪያ ምቹ ማሳ" ሊያደርገው፤ የሚለው ሐረግ ምንን የሚገልጽ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

ለ. የጥላቻ ንግግር መንስኤዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ሐ. የአካባቢው ማኅበረሰብ በመመካከር ችግሩን ባይፈታው ኖሮ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

መ. የጥላቻ ንግግርን እንዴት መከላከል ይቻላል ትላላችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ስንቅ

ሐ. ተበከለ

ለ. ከእጅ ወደአፍ

መ. ልግስና

መጻፍ

የተሰመረባቸውን ቃል/ሐረጋት በተመሳሳያቸው በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፏቸው።

ሀ. በትውልድ ቀያቸው ትዳር መሥርተው <u>በአንድ ጣራ ሥር</u> ኖረዋል።

ለ. ከብቶች ይግጡት ጨሌ፣ ይጮነጩት <u>ጠብታ ዉኃ</u> ጠፋ።

ሐ. በአካባቢያቸው <u>ማንገርበብ</u> ጀምሯል።

7.1.3 ማዳመጥ

የጥላቻ ንግግር

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “የጥላቻ ንግግር” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከጥላቻ ንግግር የጸዳ አካባቢን ለመፍጠር ከትምህርትቤት ማኅበረሰብ ምን ይጠበቃል?

ለ. የጥላቻን የከፋ ጉዳት ለመቀነስ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ሐ. የጥላቻ ንግግር ዋነኛ ምንጭ ምንድን ነው?

መ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት የቃላት ቢጋር አዘጋጁ።

ምሳሌ



የተዛባ	ጥፋት	ተበጣጠሰ	ጎደሎ	ፈሷል

አቀላጥፎ ማንበብ

“ዘር አይመረጥም” በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

7.1.4 አንብቦ መረዳት

ዘር አይመረጥም

ቅድመንባብ

“ዘር አይመረጥም” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ መልዕክት አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ድርቅና ርሀቡ “ዱብዳ” የተባለው ለምንድን ነው?

ለ. የአራተኛውና የዐምስተኛው አንቀጽ ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. የምንባቡን ዋና መልዕክት በራሳችሁ አባባል አጠቃላችሁ ጻፉ።

ቃላት

ሰንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና ዋናውን ቃል ከቅጥያው ለይታችሁ ጻፉ።

ቃል	ዋና ቃል	ቅጥያ
ዘመናቸው	ዘመን	-ኣቸው
ልጃቸው		
አካባቢያችን		
ሰዎች		
አገራት		

መጻፍ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ “ዘር አይመረጥም!” በሚለው ምንባብ መሠረት መረጃዎችን አሟልታችሁ ጻፉ።

መቼት (መቼና የት)	ጊዜ	ቦታ
ገፀባህርያት		
ችግሮች		
ሴራ/ድርጊቶች		
ልቀት/ውጤት		

7.1.5 ክለሳ

መጻፍ

“የጓደኝነት መሠረት ፍቅር ነው።” በሚል መነሻ ሐሳብ ባለኹለት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

7.2.1 ማዳመጥ — ሕግና የጥላቻ ንግግር

ቅድመማዳመጥ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ርዕሱንና ሥዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. ሕግ ምንድን ነው?

ሐ. ሐሰተኛ መረጃ ምንድን ነው?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ

ሀ. ሕግ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

ለ. በኢትዮጵያ መንግሥት የወጣው ሕግ የምን ሕግ ነው?

ሐ. በትምህርትቤታችሁ ተማሪዎችን በተመለከተ የወጣ ሕግ አለ?

መ. ሕግን ተላልፎ መሥራት ምን ሊያስከትል ይችላል?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተቃራኒ ከ"ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. መብት	ሀ. መደበቅ
2. መግለጽ	ለ. እውነተኛ
3. ሐሰተኛ	ሐ. የሚያሰባስብ
4. የሚያሰራጭ	መ. ግዴታ
5. ህትመት	ሠ. የሚያስተላልፍ
	ረ. ቃላዊ

7.2.2 አንብቦ መረዳት

ማኅበራዊ ሚዲያ

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

ሀ. ማኅበራዊ ሚዲያ ምንድን ነው?

ለ. የማኅበራዊ ሚዲያ ጥቅም ምን ይመስላችኋል?

ማኅበራዊ ሚዲያ

ማኅበራዊ ሚዲያ ዓለምን ወደ አንድ መንደርነት ከቀየሩ የቴክኖሎጅ ውጤቶች አንዱና ዋነኛው ነው። የተለመዱ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ትዊተር፣ ኢንስታግራም ወዘተ ናቸው። እነዚህ የግንኙነት ዘዴዎች ከየትኛውም የዓለም ጫፍ ያሉ ሰዎችን በማገናኘት ሕይወትን ቀላል አድርገዋል። ማኅበራዊ

ሚዲያ እንደስሙ ለዘርፈ ብዙ ማኅበራዊ ተግባራት እየዋለ ይገኛል። አፈጣጠሩም የሰውን ልጅ የመረጃ ልውውጥ ለማዘመንና ማኅበራዊ ትስስርን ለማጠናከር ነው። ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ሚዲያው ዓለማዊ መረጃዎችን ወደአንድ ቋት በማምጣት ማንኛውም ሰው ከዚህ የመረጃ ቋት የሚፈልገውንና የሚችለውን ያህል በመውሰድ መጠቀም በማስቻሉ ነው።

ይሁንእንጂ ይህ የመረጃ አውታር የልዩነት ሐሳብን አቻችሎ ጤናማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውል ሲገባ፣ በአብዛኛው እየሆነ ያለው ግን የዚህ ግልባጭ ነው። ሚዲያውን ጤናማ በሆነ መልኩ የሚጠቀሙበት አያሌ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል በተቃራኒው ለአፍራሽ ዓላማቸው መጠቀሚያ ያደረጉት ሰዎች ቁጥርም የሚናቅ አይደለም። ሐሳባቸውን፣ የፖለቲካ አቋማቸውን፣ ግላዊ እምነታቸውን እንዲያንጸባርቁ ሚዲያው የፈጠረላቸውን ምቹ መደላድል እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የግል የጥፋት አጀንዳቸውን ያራምዳሉ።

በዚህ ምክንያት የሰው ልጆችን ማኅበራዊ እሴቶች የሚንዱ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስተጋብሮችን የሚያናጉ፣ በጥላቻ የተሞሉ መረጃዎችን በየሰከንዱ ማስተናገድ እየተለመደ የመጣ ጉዳይ ሆኗል። አንዱ ብሔር በሌላው ላይ እንዲነሳ፣ አንዱ ወገን በሌላው ወገን ላይ ጦርነት እንዲከፍት፣ የአንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ተለይቶ እንዲፈናቀል ለማድረግ ወዘተ መሠረት የሌለው የውሸት መረጃ ያሰራጫሉ። በዚህ ሳቢያ ንጹሃን ተገድለዋል፣ ተሰደዋል፣ ቤት ንብረታቸው ወድሟል። ከዚህ በላይ ለዘመናት ተቻችለው በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ጥላቻን በመዝራት የማይሽር የቂም በቀል ጠባሳ ተክለዋል።

በማኅበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ መረጃዎችን የሚከታተሉ ሰዎችም ምርቱን ከግርድ ከመለየት ይልቅ ለዚህ የጥላቻ አስተሳሰብ የመገዛት ሁኔታዎች በስፋት ይታያሉ። በመሠረቱ በማኅበራዊ ሚዲያ በጽሑፍ፣ በምስልና በድምፅ የሚለቀቁ ነገሮችን ሁሉ እውነት ነው ብሎ ከማመን በፊት በሰከነ አእምሮ መርምሮ እውነተኛና ጠቃሚ መረጃዎችን መለየት ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። መረጃ፣ በሰጭና በተቀባይ መካከል የሚደረግ መስተጋብር ነው። መስተጋብሩ የሰመረ የሚሆነው ግን መረጃ ሰጪው ተዓማኒ መረጃ ማቅረብ ሲችል ነው። የመረጃ ተዓማኒነቱ የሚለካው ደግሞ የመረጃ አቅራቢው አካል ከተሳሳቱ የአመለካከት ቅራኔዎች ወጥቶ ገንቢ መልእክቶችን በማስተላለፍ ማኅበራዊና ሀገራዊ ኃላፊነቱን በትክክል መወጣት ሲችልና የመረጃ ተቀባዩም ያገኘውን ከማግበስበስ ይልቅ ጠቃሚውንና ትክክለኛውን ብቻ ለይቶ መጠቀም ሲችል ነው።

[ምንጭ:- መነሻ ሐሳብ፤ ሰሜን ወሎ ዞን ማስታወቂያ መምሪያ ድረገጽ። (2017)]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ማኅበራዊ ሚዲያ ዓለምን ወደአንድ መንደርነት የቀየራት እንዴት ነው?

ለ. “ምቹ መደላድል” የተባለው ምን ይመስላችኋል?

ሐ. ማኅበራዊ ሚዲያዎችን መጠቀም የሚያስገኛቸው ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

መ. ተገቢ ያልሆነ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም በዓለማችን እያስከተለ ያለውን ጉዳት በማስረጃ አስደግፋችሁ ግለጹ።

ሠ. በምንባቡ ሐሳቦች ትስማማላችሁ? ለምን?

ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የተሰመረባቸውን በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተኩ።

ምሳሌ፡- የማኅበራዊ ሚዲያ መረጃዎች በአንድ <u>ቋት</u> ይገኛሉ። (ማከማቻ)

ሀ. <u>መሠረት</u> የሌለው የውሸት መረጃ ያሰራጫሉ።

ለ. የመረጃ ተቀባዩም ያገኘውን <u>ከማግበስበስ</u> ይልቅ . . .

ሐ. <u>ለአፍራሽ</u> ዓላማቸው መጠቀሚያ ያደረጉት ሰዎች . . .

መ. እየሆነ ያለው የዚህ <u>ግልባጭ</u> ነው።

ሠ. ማኅበራዊ እሴቶችን <u>የሚንዱ</u> ናቸው።

መጻፍ

የቃለአጋኖ ሥርዓተነጥብን በተገቢ ቦታ በመጠቀም ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. ጐሽ በጣም ጥሩ አድርገህ ነው ያጠብከው።

ለ. እሰይ ልጄ በሰላም ተመለሰችልኝ።

ሐ. “አስቀምጠው” አለና በድንገት አንባረቀበት።

መ. “ዘራፍ የኢትዮድያ ጀግና ሞት የማይፈራ” አለና ወደውጊያው መሃል ዘሎ ገባ።

7.2.3 ማዳመጥ

ሕግና የጥላቻ ንግግር

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ሕግና የጥላቻ ንግግር”፤ በሚል ርእስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. የአዋጁ ዓላማ ምንድን ነው?

ለ. በአዋጁ የተከለከሉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ሐ. በትምህርትቤታችሁ ምን ዓይነት ሕግ መውጣት አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ በቃል ተናገሩ።

እንዳይጋፉ	ተላልፎ	አዋጅ	መቻቻል	መድሎ	ተጠያቂ ማድረግ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ማኅበራዊ ሚዲያ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

7.2.4 አንብቦ መረዳት

ማኅበራዊ ሚዲያ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ማኅበራዊ ሚዲያ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. መረጃ በሚያሰራጩና በሚቀበሉ ሰዎች መካከል ምን ዓይነት ትስስር አለ?

ለ. ጽሑፉ በምን ዓይነት ስሜት የተጻፈ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?

ሐ. በጽሑፉ ተወቃሽ የሆነ ሰው ያለ ይመስላችኋል? እሱ ማን ነው?

መ. የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝነው መቼ ነው?

ሠ. ከጽሑፉ ምን ተማራችሁ?

መጻፍ

“ማኅበራዊ ሚዲያ” የሚለውን ምንባብ ዋና ሐሳብ ከዐምስት እስከሰባት በሚደርሱ ዓረፍተነገሮች አጠቃላችሁ ጻፉ።

7.2.5 ክለሳ

መጻፍ

በ7.2.4 የጻፋችሁትን ማጠቃለያ አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሰዋስው

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ቅጽሎችን ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሐሰተኛ መረጃ ማሰራጨት ተገቢ አይደለም።

ሀ. ምንጊዜም እውነተኛ መረጃን ለማግኘት ጥረት ማድረግ አለብን።

ለ. አልጣሽ በጣም ቀጭን ልጅ ናት።

ሐ. ተማሪዎች የትምህርትቤታቸውን አጥር በትልልቅ ድንጋይ ካቡ።

መ. ጥቁር ልብስ የሐዘን ምልክት ነው።

ሠ. የካቲት 23 ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ቀን ነው።

ረ. ካሣሁን አመለኛ በቅሎ ገዛ።

7.3.1 ማዳመጥ

መታረም አለበት

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ተናገሩ።

መናኛ	አጎንቁሎ	እኩይ	ደረጀ	ይሰልባል

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. የአንድ ሀገር ልጆች ወገን ለይተው እስከመጠፋፋት የደረሱት በምን ምክንያት ነው?

ለ. “ጥላቻ የማሰብ ኃይልን ይሰልባል” ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. የጥላቻ ተገዢ የሚሆኑ ሰዎች እንዴት ዓይነት ባህርያት ያሏቸው ናቸው?

መ. በጊዜ መታረም አለበት የተባለው ምንድን ነው? ትስማማላችሁ? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ሥር የሰደደ

ለ. መሬት ይዞ

ሐ. ነፍስ አስከመጠፋፋት

መ. የተመረዘ

ሰዋስው

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉና በቃላቱ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡- <u>ሆዳም</u> ሰው ከምግብ በስተቀር ስለሌላ ነገር አያስብም።



7.3.2 አንብቦ መረዳት

ጥላቻ ይቁም

ቅድመንባብ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ርስበርስ ተወያዩ።

ሀ. ጥላቻን ማስቆም ይቻላል? እንዴት?

ለ. ጥላቻ እንዴት ሊስፋፋ ይችላል ትላላችሁ?

ጥላቻ ይቁም

ከአንዱ ጫፍ ወደሌላው የዓለም ዳርቻ የዘለቁ የጥላቻ ንግግሮች ያሳረፉት ጥቁር ጠባሳ በየምዕራፉ አሳዛኝ ታሪኮችን እየጣሉ አልፈዋል። የጥላቻ ንግግር ከአካላዊ ጉዳት በተጨማሪ ሥነልቦናዊ ጉዳትም ያስከትላል። በተለይ በልጆች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው። ልጆች (ታዳጊዎች) የማኅበራዊ ድረገፆች ተጠቃሚ በመሆናቸው የጥላቻ ንግግርን እየሰሙና እያነበቡ ያድጋሉ። በዚህ ምክንያት ለበርካታ የጥላቻ ወንጀሎች ተጠቂ እየሆኑ መምጣታቸው አይቀርም።

አዲሱ ትውልድ በዚህ እኩይ ተግባር አእምሮው ተመርዞ ካደገ ደግሞ ውጤቱ ምን ያህል የከፋ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። መልካም እሴትን በማሳወቅ ፈንታ ጥላቻን፣ አድመኝነትን፣ ንቀትን፣ ግለኝነትን ወዘተ ካስተማርናቸው ነገ ከነገወዲያ የዘራነውን ክፉ ዘር፣ የጥላቻን ውጤቶች እንሰበስባለን።

ስለዚህ ተተኪው አዲስ ትውልድ በመልካም ሥነምግባር ታንጾ የተሻለ ሀገር እንዲገነባ ወላጅ፣ ቤተሰብና ማኅበረሰብ ትውልድን የመቅረጽ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። በተለያዩ ሚዲያዎች የሚሰራጩ መልእክቶችን እውነተኛነት ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው ማስገንዘብ ይገባል። ሀሰተኛ መረጃዎችን ከማሰራጨት እንዲቆጠቡ በመምከርና ይህንን የመሰለ ተግባር የሚፈጽሙ ጓደኞቻቸውን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማድረግ የዜግነት ሃላፊነታቸው መሆኑን ጭምር ማሳወቅ ያስፈልጋል። በዚህ መንገድ ለወገን ተቆርቋሪ ስብእና ያላቸው እንዲሆኑ አድርጎ ማሳደግ ነገ ሰላም ያለው ሕይወት እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል።

ጥላቻን ብቻ ሳይሆን እያደገ የመጣውን ጥላቻን በጥላቻ የመመለስ ክፉ ባህርይ መግታት የሚቻለው ይህ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ የከፋና ዘግናኝ ውጤት ከማስከተሉ በፊት ቁጭ ብሎ አስቦ ጥላቻ የሚቆምበትን ስልት መንደፍ ለነገ የማይባል አጣዳፊ ሥራ ነው።

[መነሻ ሐሳብ፤ በድሉ ዋቅጅራ ፌስቡክ ገጽ (2019)]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. የጥላቻ ንግግሮች ምን ምን ጉዳቶች ያስከትላሉ?

ለ. ሕፃናት የጥላቻ ንግግሮችን እየሰሙና እያነበቡ የሚያድጉት ከየት ነው?

ሐ. ጥላቻን በጥላቻ መመለስ የሚቻል ይመስላችኋል? ለምን?

መ. የጥላቻ ንግግር ዓለማቀፋዊ ገጽታ የሚይዘው እንዴት ነው?

ሠ. ከጓደኞቻችሁ አንዱ የጥላቻ ንግግር ሲናገር ብትሰሙ ምን ትሉታላችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ፍቺ ስጡ።

የዓለም ዳርቻ	ጥቁር ጠባሳ	እየጣሉ	ያሳረፉት

መጻፍ

ምንባቡን መሠረት በማድረግ ስለጥላቻ ንግግር መጥፎ ገጽታ ኹለት አንቀጽ ጻፉ።

7.3.3 ማዳመጥ — መታረም አለበት

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “መታረም አለበት” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “የጥላቻ ፖለቲካና የጥላቻ ንግግር ባለንበት ዘመን አብቦ ፍሬ አፍርቷል።” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ጥላቻ ሚዛናዊነትን የሚያሳጣው እንዴት ነው?

ሐ. “በጊዜ ሊታረም ይገባዋል” በሚል አጽንኦት የተሰጠው ጉዳይ ምንድን ነው? ለምን?

መ. የጥላቻ ንግግርን እንዴት ማስወገድ የሚቻል ይመስላችኋል?

ቃላት

በዓረፍተነገሮቹ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ይህ ለዘመናት ሥር እየሰደደና እየደረጀ የመጣ እኩይ ምግባር መስተካከል አለበት።

ለ. የማሰብ ኃይልን ይሰልባል።

ሐ. ... ለፍትህና ለነፃነት የሚከፈልን ዋጋ ሳይቀር አሳንሶ ያያል።

መ. እንደሰው መናገር ካልቻልን የጥላቻ ባሪያ እንሆናለን።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ጥላቻ ይቁም” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

7.3.4 አንብቦ መረዳት

ጥላቻ ይቁም

ቅድመንባብ

በዚህ ሳምንት በኹለተኛው ክፍለጊዜ “ጥላቻ ይቁም” በሚል ርእስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የጥላቻ ንግግር ምን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል?

ለ. ማኅበራዊ ድረገፆች በታዳጊ ሕፃናት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ምንድን ነው?

ሐ. የጥላቻ ንግግሮችን እየሰሙ ያደጉ ሕፃናት ወደፊት ሊያደርሱ የሚችሉትን የከፋ ችግር እንዴት መከላከል ይቻላል?

መ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚልታችሁ ጻፉ።



ቃላት

በ“ሀ” ክፍል ላሉት ቃላት ተመሳሳይ ከ“ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ሽፍጥ	ሀ. ማጣጣል
2. በቀል	ለ. ሴረኛነት
3. ቁርሾ	ሐ. ጥላቻ
4. ማንቋሸሽ	መ. ጥቃት መመለስ
5. አድመኝነት	ሠ. ተንኮል
	ረ. ቂም
	ሰ. ማበላሸት

መጻፍ

በሚከተለው ዓረፍተነገር መነሻ አንቀጽ ጻፉ።

ትምህርትቤቶች የጥላቻ ንግግርን አስከፊነት በማስተማር ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት ማስቀረት ይችላሉ።

7.3.5 ክለሳ

መጻፍ

ባለፈው ክፍለጊዜ የጥላቻ ንግግር ወደፊት ስለሚያደርሳቸው ችግሮች የጻፋችሁትን አንቀጽ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሰዋስው

በሚከተሉት ቃላት የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ጥበበኛ	ፖለቲከኛ	ዳገታማ
ሐቀኛ	ከዳተኛ	በርሃማ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ጥላቻ ይቁም” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 8 ኤች አይ ቪ/ኤድስ

8.1.1 ማዳመጥ — ኤች አይ ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ

ቅድመማዳመጥ

ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል ገምቱ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ በይበልጥ እያጠቃ ያለው የትኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ነው? ለምን ይመስላችኋል?

ለ. በኤች አይ ቪ/ኤድስ እና በአማካይ በሕይወት የመኖሪያ ዕድሜ መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?

ሐ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያደርሳቸውን ጉዳቶች እንዴት መቀነስ የሚቻል ይመስላችኋል?

ቃላት

የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ተናገሩ።

ራዕይ	ወረርሽኝ	ፈርጀብዙ
ጉዳት	ባለድርሻ	ቀውስ

8.1.2 አንብቦ መረዳት

ይህን ታውቁ ኖሯል?

ቅድመንባብ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ የምታውቁትን በመጀመሪያው አምድ፣ ማወቅ የምትፈልጉትን በኹለተኛው አምድ፣ አንብባችሁ ስትጨርሱ ያወቃችሁትን ደግሞ በሦስተኛው አምድ ጻፉ።

ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ የማውቀው	ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ ማወቅ የምፈልገው	ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ ያወቅኩት

ይህን ታውቁ ኖሯል?

ብዙ ሰዎች ኤች አይ ቪና ኤድስ አንድ እንደሆኑ አድርገው ሲናገሩና ሲጽፉ ይስተዋላል። በመሰረቱ ኹለቱ ቃሎች ለየቅል ናቸው። ትርጉማቸውም እንዲሁ የተለያየ ነው።

ኤች አይ ቪ በሰዎች ውስጥ የሚገኘውን በሽታ ተከላካይ ህዋስ የሚያጠቃ ቫይረስ ነው። ቫይረሱ የሰዎችን በሽታን የመከላከል ወይም የመቋቋም አቅም ያዳክማል። በደም ውስጥ ሲሰራጭ በሽታን ለመከላከል የሚያስችሉ ህዋሳትን ያጠቃል። ተፈጥሯዊ በሽታን የመከላከል ኃይላቸውን ያዳክማል። ጥቃቱን ሊገታ ወይም ሊያስቆም የሚችል መከላከያ መድኃኒት መውሰድ ካልተቻለ ሰውነት ለማንኛውም ዓይነት በሽታ በቀላሉ ይጋለጣል። በዚህ ምክንያት በቫይረሱ የተያዙ ሰዎችን በማዳከም እስከሞት ሊያደርሳቸው ይችላል። ኤድስ የሚባለው ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ወይም ደረጃ ነው። በሽታው እዚህ ሁኔታ ላይ የሚደርሰው አራት ደረጃዎችን በማለፍ ነው።

ደረጃ አንድ፡- የኤች አይ ቪ መደላደያ ይባላል። አንድ ሰው ለኤች አይ ቪ ከተጋለጠ በኋላ ኤች አይ ቪ የሚገኝበት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ 12 ሳምንታት መጠበቅ ይኖርበታል። ምክንያቱም ሰውነታችን በደማችን ውስጥ ለገባው የኤች አይ ቪ ቫይረስ ምላሽ የሚሰጡ ጸረ-በሽታ ህዋሳትን ለማመንጨት 12 ሳምንታት ስለሚፈጅበት ነው። ይህ የ12 ሳምንታት ጊዜ "የኤች አይ ቪ መደላደያ ወቅት" ተብሎ ይጠራል። አንድ ሰው ለኤች አይ ቪ ከተጋለጠ በኋላ 12

ሳምንታት ሳያልፈው ተመርምሮ ውጤቱ ኔጌቲቭ/ነጻ ቢሆን ኤች አይ ቪ በሰውነቱ ውስጥ ላለመኖሩ ማረጋገጫ አይሆንም። ስለዚህ ምርመራውን በሚያደርግበት ጊዜ ለቫይረሱ ከተጋለጠ 12 ሳምንታት ላይሞላው ስለሚችል ውጤቱ ኔጌቲቭ/ነጻ ከሆነ ምርመራውን እንደገና ከ12 ሳምንታት በኋላ ማከናወን አለበት።

ደረጃ ኹለት፡- አንድ ሰው ለኤች አይ ቪ ከተጋለጠ በኋላ የመደላደያ ወቅቱ አልፎም ብዙም የበሽታ ምልክቶች ሳያሳይ ረዥም ጊዜ ሊቆይ ይችላል። ሆኖም ሰውነት በመጠኑ የመቀነስ፣ የሳምባ ምች፣ የጥፍር ላይ ፈንገስ፣ የቆዳ ሽፍታ የመሳሰሉ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ይህ ወቅት እንደግለሰቡ/ቧ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ ሊረዝም ወይም ሊያጥር ይችላል።

ደረጃ ሦስት፡- የተጓዳኝ በሽታዎች መታያ ወቅት የሚባለው ነው። የሰውነት በሽታን የመቋቋም አቅም እየተዳከመ በሄደ ቁጥር ግለሰቡ/ቧ ለተጓዳኝ ህመሞች ይጋለጣል/ትጋለጣለች። ሰውነታችን በኤች አይ ቪ ሲዳከም በእነዚህ ተጓዳኝ በሽታዎች በቀላሉ ይጠቃል። በስፋት ከሚታወቁት ተጓዳኝ በሽታዎች ውስጥ ቲቢ፣ የአፍ ቁስለት፣ ከአንድ ወር በላይ የሚቆይ የማያቋርጥ ተቅማጥና ትኩሳት ይገኙበታል። ከዚህም በተጨማሪ ከባድ የሆነ የክብደት መቀነስ ሊያጋጥምም ይችላል።

ደረጃ አራት፡- የኤድስ ጠቋሚ ህመሞች መከሰቻ ወቅት ነው። ኤች አይ ቪ የሰውነትን በሽታ የመከላከል ሥርዓት እያዳከመ ሲሄድ ቫይረሱ የሚገኝበት ሰው ጤና ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመሄድ ወደ ኤድስ ታማሚነት ይሸጋገራል። አንድ ሰው የህክምና ምርመራ ተደርጎለት የኤድስ ታማሚ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በፀረ-ኤች አይ ቪ ህክምና እገዛ ለብዙ አመታት መኖር ይችላል። የፀረ-ኤች አይ ቪ ህክምና የቫይረሱን መራባት በመቀነስ ብዙዎቹን ተጓዳኝ በሽታዎችና ህመሞች መከላከልና ማከም የሚያስችል ነው።

[ምንጭ፡- የአፍላ ዕድሜ ወጣቶች ፆታ አዘል ሥነተዋልዶና ጤና መመሪያ። (1995)። ገጽ 145-152፤ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ኤች አይ ቪ ምን ማለት ነው?

ለ. በኤች አይ ቪ እና በኤድስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. ከኤድስ እንዴት መጠበቅ የሚቻል ይመስላችኋል?

መ. በኤች አይ ቪ የተያዙ ሰዎች ጤነኛ ሆነው ሕይወታቸውን መምራት የሚችሉ ይመስላችኋል? እንዴት?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ለየቅል	የሚያጠቃ	ሊገታው	መቋቋም

ሀ. አንድ ሰው ጠንክሮ ከሰራ ድህነትን ከማሸነፍ _____ የሚችል ነገር የለም።

ለ. መንፈሰጠንካራ በመሆኗ ከሰዎች የሚሰነዘርባትን ነቀፋ _____ አይከብዳትም።

ሐ. ሙሉሰውና ደጉ ምንም እንኳ ወንድማማቾች ቢሆኑም በባህርያቸው ግን ፍጹም _____ ናቸው።

መ. ቀን እንደጎደለበት አይቶ ጎረቤቱን _____ ክፉ ሰው ነው።

መጻፍ

“ይህን ታውቁ ኖሯል” የሚለውን ምንባብ አጠቃላችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

8.1.3 ማዳመጥ

ኤች አይ ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ ”ኤች አይ ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ“ በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ ወጣቱንና ጎልማሳውን የጎበረተሰብ ክፍል ይበልጥ የሚያጠቃው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ያስከትላል፤ የሚባለው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የኤች አይ ቪን ስርጭት በመቆጣጠር ረገድ ከሚከተሉት ባለድርሻዎች ምን ይጠበቃል?

ከመንግሥት	ከእያንዳንዱ ግለሰብ	መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች
ከኅብረተሰቡ	ከጤና ተቋማት	

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ያስተጓጉላል	ለህልፈት	የሰው ሃብት በማልማት
እንዲመክን	የጀርባ አጥንት	

ሀ. በሽታው በገጠሩ አካባቢ መስፋፋቱ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ _____ የሆነው ግብርና ምርታማነቱ እንዲቀንስና በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረገው ሃገራዊ ጥረት _____ ምክንያት ይሆናል።

ለ. በዚህም _____ የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት እየተደረገ ያለውን ጥረት _____ ።

ሐ. ወሳኝ የልማት ኃይል የሆነውን ወጣቱንና ጎልማሳውን የኅብረተሰብ ክፍል በማጥቃት _____ ይዳርጋል።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ይህን ታውቁ ኖሯል?” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

8.1.4 አንብቦ መረዳት

ይህን ታውቁ ኖሯል?

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ይህን ታውቁ ኖሯል” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ኤች አይ ቪ ቫይረስ በተለይ የሚያጠቃው የትኛውን የሰውነታችንን ክፍል ነው?

ለ. “በኤች አይ ቪ መያዝ ማለት በኤድስ መያዝ ማለት አይደለም።” የሚለው ሐሳብ ምን ማለት ይመስላችኋል? በሀሳቡ ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. የኤች አይ ቪ መድኃኒት መውሰድ ከቫይረሱ ነጻ የሚያደርግ ይመስላችኋል? ለምን?

መ. ከምንባቡ የተማራችሁት ቁምነገር ምንድን ነው?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት ቢጋር አዘጋጁ።

ምሳሌ



ሲሰራጭ	ማከም	እየተዳከመ	ታማሚ

መጻፍ

የቢጋሩን መረጃዎች በመጠቀም ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ የተሟላ ድርሰት ጻፉ።



8.1.5 ክለሳ

መጻፍ

በ8.1.4 የጻፋችሁትን ድርሰት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉት።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

መቋቋም	ተፈጥሯዊ	የጀርባ አጥንት
ያስተንፍላል	የሚያጠቃ	

8.2.1 ማዳመጥ

የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ምልክቶች

ቅድመማዳመጥ

በሚከተሉት ሐረጋት/ቃል ፍቺ ላይ ርስበርስ ተወያዩ።

ነጭ የደም ሴል	ካንሰር	ሲዲፎር ሊንፎካይትስ

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ሰዎች ኤች አይ ቪ ቫይረስ እንዳለባቸው የሚታወቀው እንዴት ነው?

ለ. በኤች አይ ቪ/ኤድስ የተያዙ ሰዎች የበሽታው ምልክቶች የሚታዩባቸው መቼ ነው?

ሐ. የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።

ተላላፊ በሽታዎች	ማገርሸት	አቅም	የአዕምሮ መታወክ	መከሰት

ሰዋስው

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የተሰመረባቸው ቃላት ተሻጋሪ ወይም ኢተሻጋሪ ግስ መሆናቸውን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. ሰላም እንጀራ በወጥ <u>በላች</u>።

ለ. በረዶው <u>ቀለጠ</u>።

ሐ. ሕፃኑ መጽሐፉን <u>ቀደደው</u>።

መ. ኡስማን ወተት <u>ጠጣ</u>።

ሠ. መኪናው መሀል መንገድ ላይ <u>ቆመ</u>።

ረ. የአያቴ ውሻ <u>ሞተ</u>።

8.2.2 አንብቦ መረዳት

ደብሪቱ

ቅድመንባብ

ሀ. ሥዕሉንና ርዕሱን በማስተዋል የምታነቡት ታሪክ ስለምን እንደሚሆን ገምቱ።

ለ. የሚከተሉትን ቃላት/ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ	ጤናነክ	ባዮጋዝ	ዘመናዊ ምድጃ

ደብሪቱ



“ነገርን ነገር ያነሳዋል” እንዲሉ ዛሬ ደግሞ የቀበሌያችን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ስለሆነችው ደብሪቱ ላውጋችሁ። ደብሪቱ አንቱ የተባለች ታታሪ የጤና ባለሙያ ናት። ሙሉ ጊዜዋን በሙያዋ ሰዎችን በመርዳት ታሳልፋለች። ደከመኝ ሰለቸኝ ባህርይዎቿ አይደሉም። ካንዱ መንደር ወደሌላው በእግሯ እየተጓዘች በራሷ አቅም የሚረዱትን ህመምተኞች ትረዳለች። በጠና የታመሙ ሰዎች ሲያጋጥሟት ደግሞ ወደጤና ተቋም እንዲሄዱ ታደርጋለች። አርሶአደሩ ማድረግ ስለሚገባው ቅድመጥንቃቄ ታስተምራለች። የአካባቢያቸውንና የቤታቸውን ዕዳት እንዲጠብቁ ትመክራለች። እነዚህን የመሰሉ ተግባሮች የየዕለት ሥራዎቿ ናቸው።

ደብሪቱ በተለይም በትምህርትቤቶች በመገኘት ለመምህራንና ለተማሪዎች የምታቀርባቸው ጤናነክ ትምህርቶችና ስልጠናዎች አካባቢው ላይ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋጿቸው ከፍተኛ ነው። በስልጠናዎቿ ኤች አይ ቪ ላለባቸው ሰዎች በሚደረግ ድጋፍ ላይ ትኩረት ትሰጣለች።

በዚህ ያላሰለሰ ጥረቷ አርሶአደሮች የከብቶቻቸውን በረት ከመኖሪያቤታቸው ለይተዋል። በጪስ ምክንያት የሚመጣ የዓይን በሽታን ለመከላከል ባዮጋዝንና ዘመናዊ ምድጃን መጠቀም ጀምረዋል። የወባ መራቢያ ኩሬዎችን ደፍነዋል። ከኤች አይ ቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የሚሰጡት ድጋፍም በዓይነትና በመጠን ጨምሯል። ህመም ሲሰማ ወደጤና ተቋም የመሄድ ልምዱም ዳብሯል። በዚህ ምክንያት የታማሚዎች ቁጥር በእጅጉ ቀንሷል። በአካባቢው ጉልህ ለውጥ መታየት ጀምሯል።

ዛሬ ለደብሪቱ ጥረት ዋጋ ለመስጠት የአካባቢው አርሶአደሮች ተሰባስበዋል። አመለካከታቸውን ለቀየረችውና አካባቢያቸው እንዲሰለጥን ላደረገችው ጀግና ሴት ሽልማትና እውቅና ለመስጠት እየመከሩ ነው።

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. "ቅድመጥንቃቄ" ምን ማለት ነው?

ለ. ደብሪቱ ምን ዓይነት ሰው ናት?

ሐ. ደብሪቱ ኩሬዎች እንዲደፈኑ ያስደረገችው ለምንድን ነው?

መ. ደብሪቱ ለአርሶአደሩ በምትሰጣቸው ስልጠናዎች ያመጣቻቸው ለውጦች ምን ምን ናቸው?

ቃላት

የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በተመሳሳያቸው በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. መልካም ነገር ለሠሩ ሰዎች <u>ዋጋ መስጠት</u> ሌሎችም መልካም እንዲሠሩ ያነሳሳል።

ለ. ደብሪቱ <u>አንቱታን</u> ያተረፈች ታታሪ የጤና ባለሙያ ናት።

ሐ. <u>በጠና</u> የታመሙ ሲያጋጥሟት ደግሞ ወደጤና <u>ተቋም</u> እንዲሄዱ ታደርጋለች።

መ. በዚህ <u>ያላሰለሰ</u> ጥረቷ አርሶአደሮች የከብቶቻቸውን በረት ከመኖሪያቤታቸው ለይተዋል።

መጻፍ

"ደብሪቱ" የሚለውን ምንባብ አጠቃላችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

8.2.3 ማዳመጥ — የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ምልክቶች

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ምልክቶች" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ኤች አይ ቪ የሰውነታችንን በሽታ የመከላከል አቅም የሚያዳክመው እንዴት ነው?

ለ. በኤች አይ ቪ የተያዘ ሰው ሁሉ የበሽታው ምልክቶች የሚታዩበት ይመስላችኋል? ለምን?

ሐ. ለኤች አይ ቪ/ ኤድስ በሽታ ምልክቶች የሚሆኑ ተላላፊ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? በሽታዎቹ ህክምና ያላቸው ይመስላችኋል? እንዴት?

መ. እናንተ በደብሪቱ ቦታ ብትሆኑ ምን አስተዋጽኦ ታበረክቱ ነበር?

ቃላት

በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቺ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ተላላፊ በሽታዎች	የማይተላለፉ በሽታዎች	ትኩሳት
አገረሸበት	በተደጋጋሚ	

አቀላጥፎ ማንበብ

“ደብሪቱ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ፡

8.2.4 አንብቦ መረዳት

ደብሪቱ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ደብሪቱ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ሰዎች” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ደብሪቱ ለስልጠናዎቹ የተለየ ትኩረት የምትሰጠው ለምንድን ነው?

ሐ. ደብሪቱ አርሶአደሮቹ በሚሰጧት ሽልማትና እውቅና ምን የሚሰማት ይመስላችኋል?

መ. ይህን ታሪክ ስታነቡ ምን ስሜት ፈጠረባችሁ? ለምን?

ቃላት

በ“ሀ” ክፍል ላሉት ቃላት/ሐረግ ተቃራኒ ከ“ለ” መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ያላሰለሰ	ሀ. ሰነፍ
2. በጥቂቱ	ለ. ዳብሯል
3. ታታሪ	ሐ. የተቆራረጠ
4. ጉልህ	መ. ኢምንት
5. ቀንሷል	ሠ. በጠና
	ረ. የተናቀች
	ሰ. የተከበረች

መጻፍ

ከሚከተሉት ርዕሰጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ ተራኪ አንቀጽ ጻፉ።

የቡና አፈላል	ባለፈው ሳምንት
የልብስ አስተጣጠብ	ጉዟችን

8.2.5 ክለሳ

መጻፍ

በ8.2.4 የጻፋችሁትን አንቀጽ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ክለሳችሁ እንደገና ጻፉት።

ሰዋስው

ከሚከተሉት ቃላት ተሻጋሪ ግስ በሆኑት ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሣሌ፡- ልብስ ሰፊው የጣቃ ጨርቅ ቀደደ።

ቀደደ	ቆረጠ	ተኛ	ጻፈ	ገዛ	ሆነ
ሄደ	ጮኸ	ሰበረ	ዳኸ	ወረደ	ቆመ

8.3.1 ማዳመጥ

የኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች

ቅድመማዳመጥ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ስለኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች የምታውቁትንና ማወቅ የምትፈልጉትን በአንደኛውና በኹለተኛው አምዶች፣ ያወቃችሁትን ደግሞ ካዳመጣችሁት በኋላ በሦስተኛው አምድ ጻፉ።

ስለኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች የማውቀው	ስለኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች ለማወቅ የምፈልገው	ስለኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች ያወቅኩት

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በ2017 ዓ.ም ከኤች አይ ቪ ጋር በተያያዘ የሞቱ ሰዎች ቁጥር ምን ያህል ነበር?

ለ. ኤች አይ ቪን በተመለከተ የተዛቡ አመለካከቶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ናቸው?

መ. አንድ ሰው ደም እየፈሰሰው ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ? ለምን?

ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።

ሕይወታቸው አልፏል	የተዛቡ አመለካከቶች	መበጣት
መተላለፊያ መንገዶች	የደም ንክኪ	መነቀስ

8.3.2 አንብቦ መረዳት

ከሳሽና ተከሳሽ

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ቃላት/ሐረግ ፍቺ ተናገሩ።

የመጥሪያ ወረቀት	መሀል ዳኛ	ተከሳሽ	ችሎት	ከሳሽ

ከሳሽና ተከሳሽ

ከዕለታት አንድ ቀን ኤድስን ከሰነው፣
የመጥሪያ ወረቀት በእጁ አድርሰነው፣
እሱም አልቀረብን፣
ጥሪውን አክብሮ በጊዜው መጣልን።
ችሎት ተሰየመ፣
ከሳሽ ተከሳሹ ባንድነት ታደመ።

“ከሳሽ ምን ትጠብቃለህ!?”
“በላ ተናገራ ምን እንዳደረገህ!”
አሉ መሀል ዳኛ ትንሽ ጮክ ብለው፣
ዙሪያ ገባውን ሰው አንድ አፍታ ገርምመው።

የከሳሽ ተወካይ እኔ ስለነበርኩ፣
ድምፄን አለስልሼ ንግግሬን ጀመርኩ።
ይኽውልዎ ክቡር ዳኛ በጥሞና ይስሙኝ፣
ይህ ኤድስ የሚሉት በጣም ክፉ ጨካኝ፣

ወዳጅ ዘመዶቼን ባንዴ ጨረሰብኝ፣
ኧረ የዚህ ኤድስ ጥፋቱ ብዙ ነው፣
አያልቅም ተወርቶ መጨረሻም የለው፣
እናም ክቡር ዳኛ ሁሉንም ወክዬ፣
ኤድስን ከስሻለሁ ይቀጣልኝ ብዬ።

“በላ አንተም ተናገር” አሉት መሃል ዳኛው፣
ጠቋሚ ጣታቸውን ወደሱ ቀስረው።

ኤድስ በዚህ ጊዜ በቅጽበት ተነስቶ፣
ንግግር ጀመረ እጅግ ተቆጥቶ፣
በደሌን በዝርዝር ምንም ሳታደምጡ፣
በኔ ላይ ለመፍረድ ሰዎች አትሩጡ፣
ምንም ሳልላቸው ሰዎች ራሳቸው፣
ደረሱብኝ እንጂ አልደረስኩባቸው።

“እሱስ ትክክል ነው” አሉ ዋና ዳኛ፣
የሰው ልጅ ራሱ አርፎ ቢቀመጥ፣
አንዱ ካንዱ ቢማር ያለልክ ባይቀብጥ፣
መች ያገኘው ነበር የኤዲሱ ጣጣ፣
ደግሞስ በሱ ብሶ እሱን ሊከስ መጣ!?

ፍርድ ሰጥቻለሁ!
አድምጡኝ ተከሳሽ ከሳሽም በሞላ፣
ከዚህ ችሎት ጊዜ ከዛሬ በኋላ፣
ፋይሉ እንዲዘጋ የበሽታው ጣጣ፣
ኤድስ ወደሰው አይሂድ፣ ሰው ወደኤድስ አይምጣ።

(ምንጭ:- አብክመ ባቱማ። (1997)። መቅረዝ። ገጽ 77-180፤ ለማስተማር እንዲስማማ ለውጥ ተደርጐ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በዚህ ታሪክ ውስጥ ከሳሽ ማን ነው? ተከሳሽስ?

ለ. “ኤድስ ወደሰው አይሂድ፣ ሰው ወደኤድስ አይምጣ”፤ የሚለው መልዕክት ለማን የተነገረ ይመስላችኋል?

ሐ. የዳኛው ፍርድ ትክክል ነው ትላላችሁ? ለምን?

ቃላት

በ”ሀ” ክፍል ላሉት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ከ”ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ችሎት ተሰየመ	ሀ. በትህትና
2. ገርምመው	ለ. በትኩረት
3. ድምፄን አለስልሼ	ሐ. ጉዳዩ እንዲቋጭ
4. በጥሞና	መ. ተመልክተው
5. ፋይሉ እንዲዘጋ	ሠ. የዳኝነት ሂደቱ ተጀመረ

መጻፍ

የግጥሙን ሐሳብ በአንድ አንቀጽ አጠቃላችሁ ጻፉ።

8.3.3 ማዳመጥ — የኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “የኤች አይ ቪ መተላለፊያዎች” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ኤች አይ ቪ የማይተላለፍባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ኤች አይ ቪ አፍሪካ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋና የከፋ ጉዳት እያደረሰ ያለው ለምን ይመስላችኋል?

ቃላት

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሚልታችሁ ጻፉ።

ቃል	እማሬያዊ ፍቺ	ፍካሬያዊ ፍቺ
እንባ		
ላብ		
ዓለም		
ደም		
ምላጭ		
መርፌ		

አቀላጥፎ ማንበብ

“ከሳሽና ተከሳሽ” የሚለውን ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

8.3.4 አንብቦ መረዳት

ከሳሽና ተከሳሽ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ከሳሽና ተከሳሽ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ግጥም ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

   ሀ. የከሳሽ የክስ ጭብጥ ምንድን ነው? በክሱ ትስማማላችሁ? ለምን?

   ለ. ተከሳሽ ያቀረበው የመከላከያ ሐሳብስ ምንድን ነበር? ትስማማላችሁ? ለምን?

2. በግጥሙ መሠረት የከሳሽን ወይም የተከሳሽን ጠበቃ ወክላችሁ በክፍል ውስጥ ተከራከሩ።

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቺ ጻፉ።

ከሳሽ	አንድ አፍታ	በቅጽበት	አክብሮት	ጨካኝ

መጻፍ

ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ አንድ ግጥም ጻፉ።

8.3.5 ክለሳ

መጻፍ

በ8.3.4 ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ የጻፋችሁትን ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ክልሳችሁ እንደገና በመጻፍ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሰዋስው

ኢተሻጋሪ የሆኑትን ግሶች ብቻ መርጣችሁ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ሳበ	ገፋ	አነበበ	አወራ	ተነፈሰ	አየ
ተነሳ	ከተፈ	ወጣ	አጠበ	ለበሰ	መታ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ከሳሽና ተከሳሽ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 9 ባህላዊ ልማዶች

9.1.1 ማዳመጥ — ባህልና ልማድ

ቅድመማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።

ደቦ	እምነት	ግማ መፈልፈል	ኪነጥበብ	ደም መመለስ

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ባህል ምንድን ነው?

ለ. የባህልና የልማድ ግንኙነት ምንድን ነው?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ አሟልታችሁ ጻፉ።



ለ. ባህል ምንድን ነው? ምን ምን ነገሮችን ያካትታል?

ሐ. ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶች ለማኅበረሰቡ የሚያበረክቱት ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

ደቦ	እቁብ	ሁለንተናዊ እድገት	እድር	የማኅበረሰብ ሃብት

9.1.2 አንብቦ መረዳት

ቀሚሷ እንጂ እሷ አትጠለፍም

ቅድመንባብ

ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ስጡ።

ልጃገረድ	ድንግል	ጠለፋ

“ቀሚሷ እንጂ እሷ አትጠለፍም”

የቆየው የዋግኽምራ ሕብረተሰብ፣ ማንኛዋም ያላገባች ሴት ድንግል ስለመሆኗ ያምናል። ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣው፣ ዋግኽምራዎች ስለልጃገረድ ያላቸው ግንዛቤ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የልጃገረድነት ክብር ለሷ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቿና ለዘመዶቿም ይተርፋል። ከዚያም አልፎ የመላው ማኅበረሰብ ክብር ተደርጎ ይቆጠራል። ኅብረተሰቡ ለልጃገረድ የሚሰጠው ክብር ከቃል በላይ በተግባር ይገለፃል። ለዚህም በዋግ ምድር ልጃገረድ የማትጠለፍ መሆኑ ታላቅ ምሳሌ ነው።

ዋግኽምራ ውስጥ “አንዲት ልጃገረድ ተጠለፈች” የሚባል ወሬ ቢሰማ፣ “ይሁን” ተብሎ የሚታለፍ ጉዳይ አይሆንም። ለልጃገረዷ የቁም ሞት፣ ለቤተዘመድ ደግሞ አንገት የሚያስደፋ፣ ጥርስ የሚያስነክስ ቁጭት ይፈጥራል። በተከበረ ባህሉ ላይ የተሰነዘረ ክፉ ጦር ነውና ማኅበረሰቡን እንደእግር እሳት ያቃጥለዋል። በድርጊት ፈፃሚው ላይ ሁሉም እጁን ከማንሳት ወደኋላ አይልም።

ስለዚህም በዋግኽምራዎች ዘንድ መጥለፍ ይቅርና ማሰቡም የማኅበረሰቡን የጨዋነት ደንብ ተላልፎ የመገኘት ወንጀል ነው። ወግና ልማዱ የሚፈቅደው ተዋዶ፣ “ልጅህን

ለልጇ” ተባብሎ በሀገር ሽማግሌ አማካይነት መተጫጨትንና መጋባትን ብቻ ነው። ልኮና ተላልኮ አልሆን ቢል ለመጥለፍ ማሰብ ነውረኛ ያስብላል። ልጃገረዲቱ እንዴት በቁሟ ትሞታለች? እንዴት ቤተሰብና ዘመድ የውርደት ቋጥኝ ይሸከማል? እንዴት ባህሉ አድፎ መላ ማኅበረሰቡ ይዋረዳል? ይህ ነው በዋግኽምራዎች ልቦና ውስጥ ሰርፆ ያለው ግንዛቤ። ስለዚህ ለእጮኝነት ጠይቆ ያልተሳካለት ወደሌላ ሄዶ ይጠይቃል። ልጃገረዷ ከታጨች ጠያቂ ወደቤተሰቧ አይመጣም። ለመታጨቷ ምልክት አንገቷ ላይ ማርዳ ታጠልቃለች። በዚህም የተነሳ በዋግ ምድር “ቀሚሷ እንጂ ልጃገረዷ አትጠለፍም” ይባላል።

[ምንጭ፦ መዝሙር ፈንቴ። (2003 ዓ.ም) ሻዳይ፣ ወንዝ አይፈራ። ገጽ 84-85፤ ለማስተማር እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በዋግኽምራ ማኅበረሰብ አንዲት የታጨች ልጃገረድ በምን ትለያለች?

ለ. “በተከበረ ባህሉ ላይ የተሰነዘረ ክፉ ጦር ነውና...” ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. የአንዲት ልጃገረድን ክብር መንካት ከራሷ አልፎ የቤተሰቧ፣ ከቤተሰቧም አልፎ የመላውን ማኅበረሰብ ክብር እንደመንካት የሚቆጠረው ለምን ይመስላችኋል?

ቃላት

በ”ሀ” ክፍል ላሉት ሐረጋት ፍቺ ከ”ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ወደኋላ አይልም	ሀ. ከባድ ህመም
2. የቁም ሞት	ለ. የሚያስቆጭ
3. አንገት የሚያስደፋ	ሐ. እርምጃ ለመውሰድ
4. ጥርስ የሚያስነክስ	መ. ዕድል ለመውሰድ
5. እጁን ለማንሳት	ሠ. የሚያሳፍር
	ረ. አያመነታም
	ሰ. ውርደት

መጻፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች እያዳመጣችሁ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በትክክል ጻፉ።

9.1.3 ማዳመጥ — ባህልና ልማድ

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "ባህልና ልማድ" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. "በጎብረተሰቡ ውስጥ የሚከወኑ ባህሎች ለሁለንተናዊ እድገት አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል" ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በማኅበረሰቡ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት አስረጂ የሚሆን ነገር ምንድን ነው?

ሐ. በጎብረተሰቡ ተቀባይነት ያለው ባህል ሁሉ ጠቃሚ ነው ማለት ይቻላል? እንዴት?

መ. "የተንዛዛ ድግስ መደገስ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው።" በሚለው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ቃላት

ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው <u>የሚያመዝን</u> ልማዶች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ይባላሉ።

ለ. ኢትዮጵያ የተለያየ <u>እምነት</u> ተከታዮች ተከባብረው የሚኖሩባት ሀገር ናት።

ሐ. የማኅበረሰቡን <u>ወግ</u> በጠበቀ የሠርግ ሥነሥርዓት ተጋቡ።

መ. ጠቃሚ <u>ልማዶችን</u> መጠበቅ ለማኅበረሰብ ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ነው።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ቀሚሷ እንጅ እሷ አትጠለፍም” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

9.1.4 አንብቦ መረዳት

ቀሚሷ እንጂ እሷ አትጠለፍም

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ቀሚሷ እንጂ እሷ አትጠለፍም” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በዋግኽምራ ልጃገረዶች ትዳር የሚመሰርቱት እንዴት ነው? ትስማማላችሁ? ለምን?

ለ. “ይሁን ተብሎ የሚታለፍ ጉዳይ አይሆንም።” ማለት ምን ማለት ነው?

ሐ. ስለጠለፋ ድርጊት የእናንተ አቋም ምንድን ነው?

መ. ከምንባቡ የተደነቃችሁበት ነገር ምንድን ነው? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ነውረኛ	ልጅህን ለልጄ	ሲወርድ ሲዋረድ
የሀገር ሽማግሌ	መተጫጨት	

መጻፍ

የትምህርትቤታችሁን የአንድ ሳምንት የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ዜና ጻፉ

9.1.5 ክለሳ

መጻፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች እያዳመጣችሁ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በትክክል ጻፉ።

ቃላት

በሚከተሉት ሐረጋት/ቃል የተሟሉ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

የቁም ሞት	አንገት የሚያስደፋ	ነውረኛ

9.2.1 ማዳመጥ

ሰማይ ቢቀደድ ሽማግሌ ይሰፋዋል

ቅድመማዳመጥ



ሀ. ከርዕሱና ከሥዕሉ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ በቃል ተናገሩ።

ሽምግልና	ቁርሾ	ግጭት	ደም ማድረቅ

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. “ሰማይ ቢቀደድ ሽማግሌ ይሰፋዋል” የሚለው አባባል ለምን ዓላማ የተነገረ ይመስላችኋል?

ለ. ሽምግልና ለምን ይጠቅማል?

ሐ. ሽምግልና የሚጠይቃቸው ብቃቶች ምን ምን ናቸው?

መ. ከሽምግልና ተጠቃሚ ለመሆን ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ? ለምን?

ቃላት

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና በሚከተሉት ቃላት አሟልታችሁ ጻፉ።

ተበዳይ	ቂም	በዳይ	እንዲበተን	ተባብሶ
ለዝቦ	ጠብ	ይቅርታ	እንዳይፈርስ	ሰላም

ቃል	ተመሳሳይ	ተቃራኒ
ተጎጂ	ተበዳይ	በዳይ
ግጭት		
ተካሮ		
ቁርሾ		
እንዳይበተን		

9.2.2 አንብቦ መረዳት

ያለዕድሜ ጋብቻ

ቅድመንባብ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና ስለያለዕድሜ ጋብቻ የምታውቁትን በአንደኛው አምድ፣ ማወቅ የምትፈልጉትን በኹለተኛው አምድ፣ ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ያወቃችሁትን ደግሞ በሦስተኛው አምድ አስፍሩ።

ስለያለዕድሜ ጋብቻ የማውቀው	ስለያለዕድሜ ጋብቻ ማወቅ የምፈልገው	ስለያለዕድሜ ጋብቻ ያወቅኩት

ያለዕድሜ ጋብቻ

ያለዕድሜ ጋብቻ ማለት ዕድሜ ለጋብቻ ሳይደርስ ወይም 18 ዓመት ሳይሞላ ትዳር መመስረት ማለት ነው። ይህም ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ይመደባል። ለዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተጋላጭ የሆኑ ሴት ልጆች በጤናቸው፣ በማኅበራዊ ኑሯቸውና በሥነልቦናቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል።

ያለዕድሜ ጋብቻ የመጀመሪያው ጉዳት በጤና ላይ የሚያስከትለው ችግር ነው። ያለዕድሜ ጋብቻ በልጅነት ማርገዝን ስለሚያስከትል፣ ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች አሉ። ልጅቷ በወሊድ ጊዜ የተራዘመ ምጥ ሊያጋጥማትና ችግሩ ከባሰም ለሞት ልትዳረግ ትችላለች። አካሏ ከመዳበሩ በፊት የግብረስጋ ግንኙነት እንድትፈጽም ስለምትገደድ በመራቢያ አካሎቿና በማህፀኗ ላይ ጉዳት ይደርስባታል። ለፌስቱላ ጉዳት ልትጋለጥም ትችላለች። ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኛው የጽንስ መጨናገፍ ያጋጥማታል።

ኹለተኛው ያለዕድሜ ጋብቻ ጉዳት በማኅበራዊ ኑሮ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ነው። ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ሴት ልጆች ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ምክንያት ይሆናል። በልጅነት የሚመሰርቱት ትዳር በአብዛኛው አይፀናም። ትዳርን መፍታት ደግሞ በአካባቢው ማኅበረሰብ መገለልን ያስከትላል። ይህንን መገለል በመሸሽ ወደሌላ ቦታ ልትኮበልል ትችላለች። ልጅቷ መውለድ ብትችል እንኳ የአብራኳ የሚገኙ ልጆችን ለመንከባከብ አቅምና ብስለት ያንሳታል። በዚህ ምክንያት ሳትወድ በግድ የባሏ ጥገኛ ትሆናለች።

የመጨረሻውና ሦስተኛው ያለዕድሜ ጋብቻ ጉዳት በሥነልቦና ላይ የሚያመጣው ቀውስ ነው። በቤተሰብ ምርጫና ፍላጎት ተገደው ያለዕድሜያቸው የሚያገቡ ሴቶች በአብዛኛው ደስተኛ ላልሆነና ችግር ላልተለየው የጋብቻ ሕይወት ይዳረጋሉ። የጋብቻ ኃላፊነት ለመሸከም ይቸገራሉ። ይህ ዓይነት ችግር ያለባት ኮረዳ ለተለያዩ ጭንቀቶችና ሥነልቦናዊ ጉዳቶች ትዳረጋለች። ከባሏ ጋር በፀባይ ያለመስማማት ሁኔታ ስለሚኖር ከትዳር ሸሽታ ወደሴተኛ አዳሪነትና ጎዳና ተዳዳሪነት ልትገባ ትችላለች። ይህ ደግሞ በጤናዋና በሥነልቦናዋ ላይ የባሰ ቀውስ ያስከትልባታል።

[ምንጭ:- የሥነሕዝብ ትምህርት። (1998)። ገጽ 193፤ ለማስተማሪያነት እንዲስማማ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድኅረንባብ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጁና በምንባቡ መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።



ቃላት

የተሰመረባቸውን በተመሳሳይ ቃላት በመተካት ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. በፍቅር ላይ ያልተመሠረተ ትዳር አይፀናም።

ለ. ዕድሜዋ አሥራስምንት ዓመት ያልሞላት ኮረዳ መማር እንጂ መዳር የለባትም።

ሐ. የትኛዋም እናት ከአብራኳ በተገኙ ልጆቿ ላይ የሚጨክን አንጀት አይኖራትም።

መ. ያለዕድሜዋ የተዳረች ሴት ልጅ የትዳር ኃላፊነትን መሸከም ስለሚከብዳት ለተለያዩ ሥነልቦናዊ ጫናዎች ልትዳረግ ትችላለች።

መጻፍ

በሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩ ያሰፈራችኋቸውን ሐሳቦች መነሻ በማድረግ ስለያለዕድሜ ጋብቻ ጉዳቶች አንድ አንቀጽ ጻፉ።

9.2.3 ማዳመጥ

ሰማይ ቢቀደድ ሸማግሌ ይሰፋዋል

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ሰማይ ቢቀደድ ሸማግሌ ይሰፋዋል” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

   ሀ. “ተጎጂ ወገን እንዲካስ ይደረጋል” ማለት ምን ማለት ነው?

   ለ. የግጭት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

2. ከባህላዊው ሽምግልናና ከዘመናዊው የፍትህ ሥርዓት የትኛው ይሻላል? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ሐረጋት/ዓረፍተነገር ፍቺ ስጡ።

ቁርሿቸው የሚሸረው	ቤተሰብ እንዳይበተን
ችግሮቻቸውን በሽምግልና ይፈታሉ።	በጎ ባህላዊ እሴት

አቀላጥፎ ማንበብ

“ያለዕድሜ ጋብቻ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

9.2.4 አንብቦ መረዳት

ያለዕድሜ ጋብቻ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ ”ያለዕድሜ ጋብቻ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድጎረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ያለዕድሜ ጋብቻ ምን ማለት ነው?

ለ. በልጅነት ማርገዝ ምን ምን ጉዳቶችን ሊያስከትል ይችላል?

ሐ. አንዲት ልጃገረድ ለጋብቻ ብቁ የምትሆነው መቼ ነው?

መ. በሕፃንነት የሚመሠርቱት ትዳር በአብዛኛው የማይፀናው ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. በምንባቡ ለተገለጹት ችግሮች የተጠቆሙ መፍትሄዎች ምንድን ናቸው? ትስማማላችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ሐረጋት/ቃል ፍቺ ጻፉ።

መኮብለል	የመራቢያ አካል	ማኅበራዊ ኑሮ
ትዳርን መፍታት	የጽንስ መጨንገፍ	

መጻፍ

ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል መደረግ ስላለባቸው ጉዳዮች አንድ አጭር አንቀጽ ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

9.2.5 ክለሳ

መጻፍ

“ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት በሚል የጻፋችሁትን አንቀጽ መምህራችሁ በሚሰጡት መመሪያ መሠረት ክልሳችሁ እንደገና ጻፉት።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት/ሐረግ የተሟሉ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

ቁርሾ	አይፀናም	ግጭት	ማኅበራዊ ኑሮ

ሰዋስው

ግሶቹን ወደኃላፊ ጊዜ ቅርጽ ቀይራችሁ ዓረፍተነገር መሥርቱባቸው።

ሲስተካከል	እያቃጠለ	ይወጣል	ይመጣል	እየተከለ	ሊሠራ

9.3.1 ማዳመጥ

የአውራምባ ማኅበረሰብ ጠቃሚ ባህሎች

ቅድመማዳመጥ

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና ስለአውራምባ ማኅበረሰብ የምታውቁትን በመጀመሪያው አምድ፣ ለማወቅ የምትፈልጉትን በኹለተኛው አምድ፣ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ ያወቃችሁትን ደግሞ በሦስተኛው አምድ አስፍሩ።

ስለአውራምባ ማኅበረሰብ የማውቀው	ስለአውራምባ ማኅበረሰብ ማወቅ የምፈልገው	ስለአውራምባ ማህበረሰብ ያወቅኩት

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ/ተግብሩ።

ሀ. የአውራምባ ማኅበረሰብ የተለዩ ባህርያት ምንድን ናቸው? ለምን ይመስላችኋል?

ለ. እምነቱን ፍቅር፣ ሐይማኖቱን ሥራ ያደረገ ማኅበረሰብ ነው፤ ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. ኋላቀር አስተሳሰቦች የተባሉት ምን ምን ናቸው? ለምን?

መ. ከሚከተሉት መከራከሪያ ሐሳቦች አንዱን ደግፋችሁ በቡድን ተከራከሩ።

- የወንድና የሴት የሚባል የሥራ ክፍፍል አስፈላጊ ነው።
- የወንድና የሴት የሚባል የሥራ ክፍፍል አስፈላጊ አይደለም።

ሠ. ስለምታደንቁት ባህል በክፍል ውስጥ ንግግር ለማቅረብ መረጃ አሠባስቡ።

ቃላት

ለሚከተሉት ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

የሥራ ባህል	ኋላቀር አስተሳሰቦች
የአኗኗር ዘይቤ	መልካም ሥነምግባር
ፍትህ አጓደለብኝ	

9.3.2 አንብቦ መረዳት

ድንቄም እልልታ

ቅድመንባብ

ርዕሱን በማንበብ ግጥሙ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ድንቄም እልልታ

ሐዘን ግፍና በደል - ዕጣ ፈንታሽ ሆኖ፣

ያለገልጋይ ተጥለሽ - የጣር ድምፅሽ ታፍኖ፣

ታዋይው ሰሚ የለ - ብሶትሽ ውስጥሽ ተቀብሮ፣

እንደውቃቢ ዳንግሌ በግ - እጅና እግርሽ ፊጢኝ ታስሮ፣

በግርዛት ልማድ ጣጣ - በስለት ተብጠልጥለሽ፣

አካልሽ ተቦድሶ - በቁስል ተንሰፍስፈሽ፣

እንባሽ እየኮለለ - “እሰይ” “እልል” ተባለ?

ምንኛ ተቀልዷል - ድንቄም እልልታ የለ!

ይህ አልበቃ ብሏቸው - አካልሽ እንኳ ሳይዘና፣

ጋሜ ሳዱላሽ ሳይጠፋ - ራስ ሳይጠና ጉተና፣

ዕቃቃሽን በትነው - አሻንጉሊትሽን አፍርሰው፣

ጨዋታሽን ሳትጠግቢ - በቤት በዳሪ አፍነው፣

ክቡር ገላሽን አርክሰው - ንጽህናሽን ገሰው፣

ጠላቱን እንደሰየፈ - በደምሽ ታጥበው ጨቅይተው፣

- ፀጋሽን መሬት አፍስሰው፣

የጭካኔ ስብስብ ጩኸት - “ዕልል” አሉ መልሰው?

[ምንጭ፤ ውዳላት ገዳሙ። (1996፤83)]

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “ድንቁም እልልታ የለ!” የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

ለ. ባለታሪኳ በየትኛው የዕድሜ ክልል ላይ የምትገኝ ይመስላችኋል?

ሐ. ግጥሙ ለምን ዓላማ የተጻፈ ይመስላችኋል?

መ. ግጥሙ በምን ዓይነት ስሜት የተጻፈ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

ሠ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ጎጂ ልማዶች በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ።

ቃላት

ለሚከተሉት ሐረጋት/ቃል ፍቺ ጻፉ።

ብሶትሽ ውስጥሽ ተቀብሮ	ተብጠልጥለሽ
አካልሽ እንኳ ሳይዘና	እንባሽ እየኮለለ
ንፅህናሽን ገሰው	

መጻፍ

“ድንቁም እልልታ” የሚለውን ግጥም ወደዝርው ለውጣችሁ በትረካ ስልት ጻፉት።

9.3.3 ማዳመጥ

የአውራምባ ማኅበረሰብ ጠቃሚ ባህሎች

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “የአውራምባ ማኅበረሰብ ጠቃሚ ባህሎች” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ታሪክ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ/ተግብሩ።

ሀ. የአውራምባ ማኅበረሰብ አለመግባባቶችን የሚፈታው እንዴት ነው?

ለ. ሰዎች በፆታ እንጂ በሥራ ልዩነት የላቸውም፤ በሚለው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. ስለምታደንቁት ባህል ቀደም ሲል ያሰባሰባችሁትን መረጃ በመጠቀም ንግግር አድርጉ።

ቃላት

የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቺ ተናገሩ።

ሀ. ኑሯቸውን ለማሻሻልና <u>ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር</u> ሌት ተቀን ይሠራሉ።

ለ. ለለውጥና ለሥራ <u>ማነቆ</u> የሆኑ ኋላቀር አስተሳሰቦችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጽናት ይታገሏቸዋል እንጂ በጭራሽ <u>ለማስታመም አይሞክሩም</u>።

ሐ. በሐሰት መመስከርን፣ ሥርቆትን፣ ውሸት መናገርን፣ አመንዝራነትን፣ ነፍስ ማጥፋትንና የመሳሰሉትን ኀጢዓቶች ወይም ሐራሞች ብለው <u>ፈርጀዋቸዋል</u>።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ድንቁም እልልታ“ በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፎ ማንበብ ተለማመዱ።

9.3.4 አንብቦ መረዳት

ድንቁም እልልታ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ድንቁም እልልታ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ግጥም ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. “ጋሜ ሳዱላሽ ሳይጠፋ” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ሰዎቹ እልል ያሉት ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የግጥሙን ስሜት ትጋራላችሁ? ለምን?

መ. የሴት ልጅ ግርዛት ጠቃሚ ልማድ ይመስላችኋል? ለምን?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ታስሮ	የጣር	ግፍ	“ራስ ሳይጠና ጉተና”	እጣፈንታ

ሀ. የተፈነከተው ጭንቅላቱን ያለማደንዘዣ ሲሰፉት _____ ድምፅ አሰማ።

ለ. _____ እንዲሉ ትምህርቷን ከስድስተኛ ክፍል አቋርጠው ለማታውቀው ሰው ዳሯት።

ሐ. እጆቹን የፊጥኝ _____ ወንበር ላይ ተቀምጧል።

መ. _____ ሆነና ከኹለት አመታት መለያየት በኋላ አንድ ላይ መኖር ጀምረዋል።

መጻፍ

በሚከተለው ደብዳቤ መሠረት ለወላጆቻችሁ ወይም ለመምህራችሁ፣ ለጓደኞችሁ ወይም ለክበብ አስተባባሪያችሁ ወዘተ የአድናቆት ደብዳቤ ጻፉ።

የአድናቆት ደብዳቤ

ለውድ ርዕሰመምህር፣

የ6ኛ “ሀ” ክፍል ተማሪ የሆነችው የተማሪ ትዕግስት እናት ነኝ። በትምህርትቤቱ ዓመታዊ ክብረበዓል ላይ ተገኝቼ ነበር። ከጧት ጀምሮ እዚያው ነበርኩ። ይህን ደብዳቤ የጻፍኩትም ቀና ድጋፍና ትብብር ሲያደርጉ ለነበሩት ለሁሉም መምህራን ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ ነው። ለሁሉም ተማሪ ይጠነቀቁ ነበር፤ ሁሉም ነገር በሚገባ የተቀናጀ ነበር። ስለተማሪዎቹ አለባበስና ለትዕይንቱ ዝግጁ ስለመሆናቸው ይጨነቁ ነበር። በትዕይንቱ መጨረሻም ለህጻናቱ ስለሚደረገው ጥንቃቄ በውል ተረድቻለሁ።

በቤት ውስጥ በጣም ዝምተኛ የሆነችው ልጄ እንደዚያ ስትዘምርና ስትደንስ በማየቴ በጣም ተደንቄያለሁ። የዚህም ምክንያቱ የመምህራን ታታሪነትና ሥራ ወዳድነት ስለመሆኑ ተገንዝቤያለሁ። ልጄ በዚህ ትምህርትቤት በእንደዚህ ዓይነቱ የመምህራን ክትትልና ድጋፍ ለስኬት እንደምትበቃም እርግጠኛ ሆኛለሁ። ስለጥረታችሁና ስለጥንቃቄያችሁ አድናቆቴን መግለጽ እወዳለሁ።

ከመልካም ምኞት ጋር፤

አክባሪዎ፣

ወይዘሮ ብርቁ ታፈሰ

9.3.5 ክለሳ

መጻፍ

በ8.3.4 የጻፋችሁትን የአድናቆት ደብዳቤ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት እንደገና ክለሳችሁ ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

የሥራ ባህል መልካም ሥነምግባር ኋላቀር አስተሳሰቦች እጣፈንታ ማነቆ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ድንቁም እልልታ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ምዕራፍ 10 ሴቶችን ማብቃት

10.1.1 ማዳመጥ

ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን የሚከበረው መቼ ነው?

ለ. የሴቶች ቀን የሚከበረው ለምን ይመስላችኋል? ትስማማላችሁ?

ድኅረማዳመጥ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጁና "ማርች 8" ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን ሆኖ እንዲከበር ያለፈባቸውን ታሪካዊ ሂደቶች አሚልታችሁ በመጻፍ በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ።

1 → 2 → 3 → 4

ቃላት

የሚከተሉትን ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።

ፆታዊ ስብጥር	የሥራ ማቆም አድማ	ሚዛናዊ ያልሆነ
የመምረጥና የመመረጥ መብት	የተሻለ የሥራ ሁኔታ	

10.1.2 አንብቦ መረዳት

ሴቶችን ማብቃት

ቅድመንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. “ሴቶችን ማብቃት” ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. ሴቶችን ከወንዶች በተለየ ማብቃት የሚያስፈልገው ለምን ይመስላችኋል?

ሴቶችን ማብቃት

ሴቶች በቤታቸው፣ በአካባቢያቸውና በሀገር ደረጃ ወሳኝ ሚና አላቸው። ሴቶች የማይሳተፉበትና ተጠቃሚ የማይሆኑበት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መርሀግብር ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ሴቶች የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ስለሆኑ ነው። ሴቶች ባልተሳተፉበት በግማሽ እውቀትና በግማሽ ጉልበት ግብን ለማሳካት መሞከር ከንቱ ድካም ይሆናል።

ሴቶች የማኅበረሰቡ የጀርባ አጥንቶች ናቸው። የቤተሰብም ሆነ የሀገር እድገት አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው ያደርጋሉ። ይሁንእንጂ ሴቶች ለብዙ ዘመናት በልዩ ልዩ ማኅበራዊና ባህላዊ ተጽዕኖዎች ሥር የኖሩ በመሆናቸው የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ሳያበረክቱ ቆይተዋል። ስለሆነም የሴቶችን አቅም በመገንባት በልዩ ልዩ መስኮች ያላቸውን ተሳትፎ ከፍ ማድረግ ይገባል። ይህ ሲሆን ነው የተሟላ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚረጋገጠው።

ሴቶች አቅማቸው ጎልብቶ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ማድረግ እንዲችሉ ደግሞ በትምህርት ዘርፍ ተሳትፏቸውን ማጎልበት ዐብይ መፍትሄ ነው። ያለባቸውን የሥራ ጫና በመቀነስና እንደያለዕድሜ ጋብቻ ያሉ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በማስወገድ በትምህርታቸው እንዲገፉና ከወንድሞቻቸው እኩል የሥራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው

ማድረግ ያስፈልጋል። በሥራ ዓለም በሚሰማሩበት ወቅትም ከሴትነት ተፈጥሯዊ ባህርያቸው ጋር የሚጣጣም ምቹ የሥራ አካባቢ ሊፈጠርላቸው ይገባል።

[ምንጭ:- የኢትዮጵያ ሥነሕዝብና ጤና ጥናት። (2011)። ገጽ 3-4፤ የተወሰነ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ]

ድጎረንባብ

የአንቀጾቹን ቁጥር ከሚያስተላልፉት ዋና ሐሳብ ጋር በምንባቡ መሠረት አዛምዱ።

አንቀጽ 1	ሀ. ሴቶችን ለማብቃት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች
አንቀጽ 2	ለ. ሴቶች በማኅበረሰብ ውስጥ ያላቸው ሚና
አንቀጽ 3	ሐ. ሴቶች በልዩ ልዩ መስኮች ያላቸው አስተዋጽኦ ውስንነት

ቃላት

ለሚከተሉት ሐረጋት ፍቺ ጻፉ።

የሥርዓተፆታ እኩልነት	የሥራ ተሳትፎ	ምቹ የሥራ አካባቢ
የሴቶችን አቅም መገንባት	የሥራ ጫና	

መጻፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች እያዳመጣችሁ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በትክክል ጻፉ።

10.1.3 ማዳመጥ

ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድጎረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. በአሜሪካ ኒዮርክ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሴት ሠራተኞች ሰልፍ ያደረጉት ለምን ዓላማ ነበር? ትስማማላችሁ? ለምን?

ለ. “ማርች 8” ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን ሆኖ እንዲከበር የተመረጠበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሐ. “ሴቶችን ማብቃት” እና “ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን” በሚሉት ሹለት ምንባቦች ያለው ተመሳስሎ ምንድን ነው?

መ. በአሁኑ ጊዜ የሥርዓተፆታ እኩልነት ተከብሯል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ሲነፃፀር	የተጠነሰሰው	ተደራጀ	ማቋቋም	ሰልፍ

ሀ. ድርጅቱን የመመስረት ሐሳብ _____ የተማሪዎችን ንቅናቄ ተከትሎ ነበር።

ለ. ሴቶች የሚከፈላቸው ከወንዶች ጋር _____ በእጅጉ አነስተኛ ነበር።

ሐ. የሠራተኛ ማኅበር የማቋቋም እንቅስቃሴው በ _____ ሁኔታ ቀጠለ።

መ. የኪነጥበብ ክበባትን በትምህርትቤቶች _____ ዘርፈብዙ ጥቅም አለው።

ሠ. ሴት ሠራተኞች አነስተኛ የደመወዝ ክፍያንና ለጤና ምቹ ያልሆኑ የሥራ ሁኔታዎችን በመቃወም _____ አደረጉ።

አቀላጥፎ ማንበብ

“ሴቶችን ማብቃት” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

10.1.4 አንብቦ መረዳት

ሴቶችን ማብቃት

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ሴቶችን ማብቃት” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ሴቶችን ማብቃት ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ሴቶች የማይሳተፉበትና ተጠቃሚ የማይሆኑበት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውጤታማ የማይሆነው ለምንድን ነው?

ሐ. ሴቶች በሚኖሩበት ማኅበረሰብ የሚጠበቅባቸውን ያህል አስተዋጽኦ እንዳያበረክቱ ተጽዕኖ ያደረገባቸው ምንድን ነው?

መ. የሴቶችን ሙሉ አቅም በሁሉም ዘርፍ ለመጠቀም ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ቃላት

በ”ሀ” ክፍል ላሉት ቃላት ተመሳሳይ ከ”ለ” ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ።

“ሀ”	“ለ”
1. ውጤታማ	ሀ. ጫና
2. ግብ	ለ. ማረጋገጥ
3. መስኮች	ሐ. ስኬታማ
4. ማስፈን	መ. ዓላማ
5. ተጽዕኖ	ሠ. ዳብሮ
	ረ. ዘርፎች

መጻፍ

“ሴቶችን ማብቃት” የሚለውን ምንባብ ሐሳብ አጠቃላችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

10.1.5 ክለሳ

መጻፍ

ነጠላ ትዕምርተጥቅስን (‘ ’) በተገቢ ቦታ በመጠቀም የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች እንደገና ጻፉ።

ሀ. “እማማ አልጣሽ ደህና አደሩ! እማዬ ኑ ቡና ጠጡ ብላለች” ብሎ መልሳቸውን ሳይጠብቅ ሲሮጥ እንደመጣ፣ ሲሮጥ ተመለሰ።

ለ. “ስሙኝ ወይዘሮ ፋናዬ! መጽሐፉም ቢሆን አፈር ነህና ወደአፈር ትመለሳለህ ነው የሚለው፤ ስለዚህ ሐዘን ማብዛት አያስፈልግም፤ መበርታት ነው የሚሻለው” አሉ መምሬ ግርማ።

ሐ. “እኔ ግን ሰዎች ፈልገው ክፉ የሚሆኑ አይመስለኝም። ሰዎች በተፈጥሯቸው ጥሩዎች ናቸው በሚለው የአና ፍራንክሊን አባባል እስማማለሁ” አለች ውይይቱን የመቀጠል ጉጉት እየታየባት።

ቃላት

በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት የተሟሉ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

የሥራ ጫና	ሲነሣፀር	የሥርዓተያታ እኩልነት	የተደራጀ	ተጽዕኖ

ሰዋስው

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢዎችን ጻፉ።

ዓረፍተነገር	ቀጥተኛ ተሳቢ	ኢቀጥተኛ ተሳቢ
ሰውየው ለልጁ ደብተር ገዛለት።	ደብተር	ለልጁ
ሰይድ ለእህቱ ምስጢር ነገራት።		
እስከዳር ለልጇ ልብስ ገዛች።		
ሰብስቤ ለሚስቱ ሃብቱን አወረሳት።		
ጴጥሮስ ለልጁ ተረት አነበበለት።		

10.2.1 ማዳመጥ

ሴት ቅኔ ናት፤ ሴት ረቂቅ ናት

ቅድመማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ከርዕሱ በመነሳት ስለምንባቡ ሐሳብ ገምቱ።

ለ. “ሴት ቅኔ ናት” ሲባል ምን ማለት ነው?

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. “ወንዶች፤ ሴቶችን የሚረዷቸው ከራሳቸው ስሜትና የግንዛቤ አድማስ አንፃር ነው” ሲባል ምን ማለት ነው? ትስማማላችሁ? ለምን?

ለ. ጠቢባን ሴትን እንዴት እንደገለጿት ተናገሩ? እናንተስ በሐሳቡ ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. “ወንድ ልጅ ከሴት ጋር እኩል ነህ፤ መባሉ የንግሥና አክሊል እንደተደፋለት ይቆጠራል” በሚለው ሐሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

መ. ምንባቡ ለምን ዓላማ የተጻፈ ይመስላችኋል?

ቃላት

ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ውጫዊ ውበት በውስጣዊ ማንነት ካልታገዘ <u>ስንኩል</u> ነው።

ለ. ከብልህነቷ፣ ከረቂቅነቷ፣ <u>ከመምራት</u> አቅሟ አንፃር ሴት ልጅ የተደረገላትና የተነገረላት ትንሽ ነው።

ሐ. ወንድ ልጅ ከሴት ጋር እኩል ነህ፤ መባሉ የንግስና አክሊል <u>እንደተደፋለት</u> ይቆጠራል።

መ. ወንዶች ሴቶችን ከራሳቸው ስሜትና <u>የግንዛቤ አድማስ</u> አንፃር ለመረዳት መሞከራቸው የሴትን ትክክለኛ <u>ቁመና</u> ሊያሳያቸው አይችልም።

10.2.2 አንብቦ መረዳት

እጅ አልሰጥም

ቅድመንባብ

“እጅ አልሰጥም” የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የቃላቱንና የሐረጋቱን ፍቺ ገምታችሁ በሹለተኛው ዓምድ ጻፉ።

ቃል	የተገመተ ፍቺ	ከንባብ በኋላ	ፍንጭ ሰጪ ቃላት/ሐረግ
እጅ አልሰጥም			
አትታክትም			
መብት			
በመቃወም			
ንቁ			
በድቅድቅ ጨለማ			

እጅ አልሰጥም

የተወለደችው በአንዲት አነስተኛ የገጠር መንደር ነው። ወላጆቿ አርሶአደሮች ናቸው። ስድስት ልጆች አሏቸው፤ የበኩሯ በእምነት ናት። በቤተሰቡ ውስጥ ተሰሚነትና ወሳኝነት ያላቸው አባቷ ፍላጐታቸው እንድትማር ሳይሆን ትዳር ይዛ የልጅ ልጅ እንድታሳያቸው ነበር።

በእምነት የ3ኛ ክፍል ተማሪ እያለች አባቷ ሊድሯት መወሰናቸውን ስትሰማ በድቅድቅ ጨለማ ከቤት ጠፍታ ከተማ ወደሚኖሩት አጎቷ ቤት ኮበለለች። በአጎቷ ቤት እየኖረች ትምህርቷን ቀጠለች። በርካታ መሰናክሎች ቢያጋጥሟትም ሁሉንም ተቋቁማ የ2ኛ ደረጃ ተማሪ ሆነች።

በእምነት ከልጅነት ዕድሜዋ ጀምሮ በአካባቢዋ ያሉ ሴቶች ያለባቸውን ጫና ተመልክታለች። የሚደርስባቸውን ጫና ከራሷ ሕይወት ጋር በማያያዝም በጣም ታዝን ነበር። ይህም በትምህርትቤቷ በተቋቋመው የሥርዓተፆታ ክበብ ውስጥ ለመሳተፍ ሳይገፋፋት አልቀረም። በክበቡ መሳተፏ የሴት ተማሪዎችን ችግር ይበልጥ ለመረዳት መንገድ ከፈተላት። የክበቡ አባላትም የላቀ ተሳትፎዋን በማጤን ከፍተኛ ኃላፊነት ጣሉባት። በእምነት ያጋጠሟትን ችግሮችና የሕይወት ተሞክሮዋን ለአባላቱ ስለምታካፍላቸው በአርአያነት መታየት ጀመረች። የክበቡ አባላት በየሳምንቱ አርብ ከትምህርት በኋላ በመገናኘት ስለሥርዓተፆታ ፖሊሲና ስለሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ በሚያደርጉት ውይይት ንቁ ተሳትፎ ታደርጋለች። ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚደረጉ ውይይቶች ሳትታክት ትሳተፋለች።

በእምነት በ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ጥሩ ውጤት አስመዝግባ ዩኒቨርሲቲ ገባች። የሴቶችን መብት ለማስከበር ባላት ጽኑ ፍላጎት በተመደበችበት ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ለመማር ወሰነች። የሕግ ትምህርቷን እየተከታተለች ጎን ለጎን በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች መማክርት ኮሚቴ አባል ሆና ማገልገል ጀመረች። ይህን አጋጣሚ በመጠቀምም በሴት ተማሪዎች ላይ የሚደርሱ በደሎችን በመቃወም ለመብታቸው ታገለች።

ከዩኒቨርሲቲ እንደተመረቀችም የሴቶች መብት ተሟጋችነት እንቅስቃሴዋን ቀጠለች። በደል ደርሶባቸው ለሚመጡና ጠበቃ ለማቆም ለማይችሉ ሴቶች ነፃ የሕግ አገልግሎት መስጫ ማዕከል አቋቁመች። በዚህም በደላቸውን ደብቀው የኖሩ ሴቶች ፍትህ እንዲያገኙ አደረገች።

በእምነት ለችግሮች "እጅ አልሰጥም" በማለቷ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሴቶችም ተስፋ ሆነች።

(ምንጭ:- አማርኛ እንደአፍመፍቻ ቋንቋ፣ 8ኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ። (2007 ዓ.ም)። ገጽ 186- 188 ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በእምነት በሥርዓተ-ፆታ ክበብ ተሳታፊ የሆነችው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. በእምነት የሥርዓተ-ፆታ ክበብን በኃላፊነት እንድትመራ የተመረጠችው በምን ምክንያት ነው?

ሐ. በእምነት ወደአጎቷ ቤት ባትሄድ ኖሮ ምን ትሆን ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

መ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ? እንዴት ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ?

ቃላት

በቅድመንባብ ስለቀረቡት ቃላት ፍቺ እንደገና አስቡ። የመጀመሪያ ግምታችሁ ትክክል ከሆነ ይህን "✓" ምልክት በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ አስፍሩ። ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ግምታችሁን ከቀየራችሁ ደግሞ አዲሱን ፍቺ በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ ጻፉ። የቃሉን ፍቺ ለመረዳት ያገዛችሁን ቃል በመለየት በአራተኛው ዓምድ ውስጥ ጻፉ።

መጻፍ

"እጅ አልሰጥም" የሚለውን ምንባብ አጠቃላችሁ አጭር አንቀጽ ጻፉ።

10.2.3 ማዳመጥ

ሴት ቅኔ ናት፤ ረቂቅ ናት

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ሴት ቅኔ ናት፤ ረቂቅ ናት” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ሴቶች በአመራርነት የሚኖራቸውን ተሳትፎ ማሳደግ የሚቻለው እንዴት ነው?

ለ. የሴትን ትክክለኛ ማንነት መርምሮ መድረስ ያልተቻለው ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. ስለሴት ልጅ በተገለጸው ሁሉ ትስማማላችሁ? ለምን?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ተናገሩ።

ረቂት	ብልህነት	ፀጋ	ከያንያን

አቀላጥፎ ማንበብ

“እጅ አልሰጥም” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

10.2.4 አንብቦ መረዳት

እጅ አልሰጥም

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “እጅ አልሰጥም” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የበእምነት አባት ለልጃቸው ይመኙት የነበረው ምንድን ነው?

ለ. በእምነት የሕግ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ያቋቋመችው ለምን ዓላማ ነበር? ትስማማላችሁ? ለምን?

ሐ. በእምነትን ለስኬት ያበቃት ምን ነበር?

መ. የሴቶችን ጫና እንዴት መቀነስ የሚቻል ይመስላችኋል?

ቃላት

በ"ሀ" ላሉት ቃላት/ሐረግ ተመሳሳይ ከ"ለ" መርጣችሁ አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ተሰሚነት	ሀ. በማስተዋል
2. መንገድ ከፈተላት	ለ. ጠንካራ
3. በማጤን	ሐ. ተደማጭነት
4. ተሞክሮ	መ. ተግባቢነት
5. ጽኑ	ሠ. አጋጣሚ ፈጠረላት
	ሰ. ልምድ

መጻፍ

ከዚህ በፊት ያነበባችሁትን (የሰማችሁትን) አንድ ተመሳሳይ ታሪክ በሹለት አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

10.2.5 ክለሳ

ሰዋስው

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁና በዓረፍተነገሮቹ ውስጥ ያሉትን ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢዎች ለይችሁ ጻፉ።

ዓረፍተነገር	ቀጥተኛ ተሳቢ	ኢቀጥተኛ ተሳቢ
አብዱ ለእናቱ ቤት ሠራ።		
ውቢት ለጎረቤቷ ብረትድስት አዋሰቻት።		
ዳዊት ለፋጡማ እስክርቢቶ አቀበላት።		
አማርኛ መምህሯ ለተማሪዎቹ ልቦለድ ተረከችላቸው።		
ወይዘሮ ሃናማርያም ለልጃቸው ስንቅ ላኩለት።		

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

በኩር	ፀጋ	ተሞክሮ	መብት	ብልህነት

መጻፍ

ነጠላ ትእምርተጥቅስን (‘ ’) በአግባቡ በመጠቀም ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

ሀ. “ታላቁ የፊዚክስ ሊቅ፣ አልበርት አነስታይን፣ መማር፣ መማር፣ አሁንም መማር! እንዳለው ሁልጊዜም ለመማር፣ ለማወቅ መትጋት አለባችሁ” አሉ መምህሩ።

ለ. “አሄሄ! ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ፣ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ አለ ያገሬ ሰው፤ ሳይሆን ነበር እንጂ መጠንቀቅ አሁን ከሆነ በኋላ መብሰክሰብክ ምን ይፈይዳል!” ሲሏት እናቷ በፀፀት ላይ ንዴት ተጨምሮ የምትሆነውን አሳጣት።

10.3.1 ማዳመጥ — ሴቶችና ትምህርት

ቅድመማዳመጥ

ለሚከተሉት ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

የትምህርት ሥርዓት	የትምህርት ተደራሽነት
የትምህርት ተቋማት	የትምህርት ተሳትፎ መመጣጠን

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. “እናትን ማስተማር መላውን ቤተሰብ ማስተማር ነው”፤ ማለት ምን ማለት ነው? ትስማማላችሁ? ለምን?

ለ. ሴቶች ከወንዶች እኩል በትምህርት ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው? እንዴት ማስወገድ የሚቻል ይመስላችኋል?

ሐ. በመማሪያ ክፍላችሁ የወንድ ተማሪዎች ቁጥር ከሴቶቹ በልጦ ቢታይ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ቃላት

የሚከተሉትን ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።

የትምህርት ዕድል	የመማር አማራጮች
የቤተሰብ ምጣኔ	የትምህርት ተደራሽነት

10.3.2 አንብቦ መረዳት

ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

ቅድመንባብ

ሀ. የሀገር ፕሬዝዳንት ለመሆን ጾታ የሚወስን ይመስላችኋል?

ለ. ወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ ማን ናቸው?

ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ



ወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው። በሊሴ ገብረማርያም ትምህርትቤት የመጀመሪያና የኹለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተምረዋል። አራት ሴት ልጆች ለነበሯቸው ወላጆቻቸው የበኩር ልጅ ናቸው። ገና በአሥራሰባት ዓመታቸው ነፃ የትምህርት ዕድል አግኝተው ወደፈረንሳይ ሀገር በመሄድ በ"ሞንትፔልየር" ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ አጥንተዋል። በሀገረ ፈረንሳይ ለዘጠኝ ዓመት ከቆዩ በኋላ ወደኢትዮጵያ በመመለስ በትምህርት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ሆነው ማገልገል ጀመሩ። ትንሽ ቆይተውም ክፍሉን በበላይነት መርተዋል። ከዚያም ወደውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በመዛወር በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች ሠርተዋል።

ወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ ከአምባሳደር ዮዲት እምሩ ቀጥለው በአምባሳደርነት የተሾሙ ኹለተኛዋ ሴት ኢትዮጵያዊት ናቸው። እ.አ.አ ከ1989-1993 መቀመጫቸውን ሴኔጋል በማድረግ በሴኔጋል፣ በማሊ፣ በኬፕቨርዲ፣ በጊኒቢሳው፣ በጋምቢያና ጊኒ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው የኢትዮጵያ ተወካይነት ሥራቸውን ሠርተዋል። ቀጥሎም እ.አ.አ. ከ1993-2002 በጅቡቲ የኢትዮጵያ አምባሳደርና በ"ኢጋድ" የኢትዮጵያ ተጠሪ ሆነው አገልግለዋል። እ.አ.አ ከ2002-2006 ድረስ ደግሞ በፈረንሳይ የኢትዮጵያ አምባሳደርና በ"ዩኔስኮ" የኢትዮጵያ ተጠሪ ሆነው ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል። እ.አ.አ. ከ2006-2009 በአፍሪካ ህብረትና በተባበሩት

መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የኢትዮጵያ ተጠሪ ሆነው ሠርተዋል።

አምባሳደር ሣህለወርቅ ዘውዴ በአጠቃላይ በተለያዩ ሀገራትና ዓለማቀፋዊ ድርጅቶች የኢትዮጵያ አምባሳደርና ተጠሪ በመሆን ከ20 ዓመታት በላይ የውጭ ጉዳይ መሥሪያቤትን አገልግለዋል። እ.አ.አ. በ2009 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን በመቀላቀል የድርጅቱ በመካከለኛው አፍሪካ "ሪፑብሊክ" የተቀናጀ ሰላም ግንባታ መሪ ሆነው ሠርተዋል። እ.አ.አ. በ2011 በናይሮቢ በአዲስ ለተቋቋመው የተመድ ጽህፈትቤት የመጀመሪያ ጠቅላይ መሪ ሆነው ተሹመው ነበር። በዚያም ለሰባት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ የአፍሪካ ህብረት የተመድ ልዩ ተጠሪ ሆነው አገልግለዋል።

ወይዘሮ ሣህለወርቅ ጥቅምት 15 ቀን 2011 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ሆነው በመሾም የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት እየተወጡ ይገኛሉ። ፕሬዚዳንቷ አማርኛ፣ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው ይናገራሉ። ባለትዳርና የኹለት ወንድ ልጆች እናት ናቸው።

[ምንጭ:- ጎልጉል ድረገጽ ጋዜጣ። (2010)። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የወሰደ]

ድኅረንበብ

የሐሳብ ማደራጃ ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ስለወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልታችሁ አስፍሩ።

የትውልድ ቦታ	
2ኛ ደረጃ ትምህርት	
ከፍተኛ ትምህርት	
ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀጠሩበት መሥሪያቤትና የሥራ ዘርፍ	
በሕይወት ዘመናቸው የተሰማሩባቸው የሥራ ዘርፎችና ዓበይት ክንውኖቻቸው	
በመጨረሻም በሕይወት ዘመናቸው የደረሱበት ስኬትና አሁን ያሉበት ሁኔታ	

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

በማቅናት	የተቀናጀ	አጥንተዋል	ተጠሪ

መጻፍ

ስለምታደንቋት አንዲት ኢትዮጵያዊት ሴት መረጃ አሰባስባችሁ የሕይወት ታሪክ ጻፉ።

10.3.3 ማዳመጥ

ሴቶችና ትምህርት

ቅድመማዳመጥ

ባለፈው ክፍለጊዜ "ሴቶችና ትምህርት" በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ በቃል ተናገሩ።

ድኅረማዳመጥ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. የሕዝብ ቁጥር እድገትን መቆጣጠር ለምን ያስፈልጋል?

ለ. የመማር አማራጮችና የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ እንዴት የሚዛመዱ ይመስላችኋል?

ሐ. የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ተመሳሳይ ከ"ለ" መርጣችሁ አዛመዱ።

"ሀ"	"ለ"
1. ድርሻ	ሀ. ተፎካካሪ
2. ሃቅ	ለ. እኩልነት
3. ተቋዳሽ	ሐ. አስተዋጽኦ
4. ፍትሐዊነት	መ. እውነት
	ሠ. ተሳታፊ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

10.3.4 አንብቦ መረዳት

ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

ቅድመንባብ

ባለፈው ክፍለጊዜ “ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ” በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ድኅረንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ ለቤተሰቦቻቸው ስንተኛ ልጅ ናቸው?

ለ. ወይዘሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀጠሩበት መሥሪያቤት ምን ነበር?

ሐ. በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት አምባሳደር ማን ናቸው?

መ. ከምንባቡ ያስደነቃችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን?

ሠ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ?

ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረግ ፍቺ ስጡ።

ተመድ	አምባሳደር	የሥራ ኃላፊነት	ተሸመው	ርዕሰብሔር

መጻፍ

ስለምታደንቋት አንዲት ኢትዮጵያዊት ሴት የሕይወት ታሪክ የጻፋችሁትን መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ከልሳችሁ እንደገና ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

10.3.5 ክለሳ

ሰዋስው

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።

ሚስት	ቀሚስ	እሱባለው <u>ለሚስቱ ቀሚስ</u> ገዛ።
ማሙሽ	ከረሜላ	
እናት	ብር	
ኢትዮጵያ	እርዳታ	
አርሶአደሮች	ማዳበሪያ	

ቃላት

በሚከተሉት ቃላት የተሟሉ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ተሾመች ፍትሓዊነት ተቋዳሽ በማቅናት ድርሻ

አቀላጥፎ ማንበብ

“ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

ዋቢዎች

መዝሙር ፈንቴ። (2003)። *ሻደይ፤ ወንዝ አይፈሬ*። ባህር ዳር።

ምሕረተሥላሴ መኮንን። (2017)። *ሪፖርተር ጋዜጣ*። አዲስ አበባ

ሞላ ደመቀ። (2005)። *የግብርና ግጥማዊ ሥነቃል*። ባህር ዳር።

ስንታየሁ ሐብታሙ። (2017)። *የግጥም ተሰጥኦ፤ ተሰጥኦ ሚዲያ*።

በርኖስና ባና። (2019)። *የመንዝ ባህላዊ አልባሳት*። ባህር ዳር።

ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን። (2009)። *በአብክመ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም በኦሮሞ ብሔረሰብ አስ/ዞኖች ላይ የተመዘገቡ የኢንታንጅብ ባህላዊ ቅርሶች*። አዲስ አበባ።

በድሉ ዋቅጅራ። (2002)። *የፍካት ናፋቂዎች*። አዲስ አበባ።

በድሉ ዋቅጅራ የፌስቡክ ገጽ። (2019)

ብሔራዊ የሥነሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት። (1998)። *የሥነሕዝብ ትምህርት*። አዲስ አበባ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (1994)። *የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ*። ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ። አዲስ አበባ።

ነጋሪት ጋዜጣ። (2012)። *አዋጅ ቁጥር 1185/2012*። አዲስ አበባ።

ነጻው መዝገብ። (2020)። *እውቀት*። *ውክፔዲያ*።

ኢፌዴሪ ት/ሚ/ርና አብክመ ት/ቢሮ። (2007)። *አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ፤ 6ኛ ክፍል*።

ኢፌዴሪ ት/ሚ/ርና አብክመ ት/ቢሮ። (2007)። *አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ፤ 7ኛ ክፍል*።

ኢፌዴሪ ት/ሚ/ርና አማብክመ ት/ቢሮ። (2007)። *አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ፤ 8ኛ ክፍል*።

አብክመ ባቱማ። (1991። *መቅረዝ*። ባህር ዳር።

አብክመ ቱሪዝም ቢሮ። (2001)። *የአማራ ክልል ተረታተረት ስብስብ*። ባህር ዳር።

አዲስ ሕይወት። (1980)። *የቡና ባህላዊ ሥርአታችንና መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች*። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት። አዲስ አበባ።

አያሌው አራጌ። (2007)። *የቺምቺም ጨዋታ በወልዲያ*። ያልታተመ።

እንዳለ ወርቁ። (2012)። *የሹለት የብር ኖቶች ወግ*። አዲስ አበባ።

ከበደ ሚካኤል። (1933)። *የዕውቀት ብልጭታ*።

ወለላዬ። (2012)። *ኢትዮጵያ ሃገሬ*። ድረ ገጽ።

ውዳላት ገዳሙ (1996)። *እናትና ልጅ*። አዲስ አበባ።

ዘሃበሻ ስፖርት። (2018)። *ካይላ ዊለር*። አዲስ አበባ።

DSW። (1995)። *የአፍላ ዕድሜ ወጣቶች ዎታዘል ሥነተዋልዶና ጤና መመሪያ*። አዲስ አበባ።

ሥነሕዝብ ጽ/ቤት። (2011)። *የኢትዮጵያ የሥነሕዝብ ጤና ጥናት*። አዲስ አበባ።

የኢፌዴሪ ግብርናና እንስሳት ሃብት ልማት ሚኒስቴር። (2010)። *የሰብል አመራረት ፓኬጅ*። አዲስ አበባ።

ፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን። (1993)። *ኦሎምፒክና ኢትዮጵያ*። አዲስ አበባ።